ሕፃናትን ለማርከስ የተፈጠረ ዘማዊ
ገጽ 9

የስንፍና መድኃኒት!
ገጽ 11

ትኩረት ያላገኘው የአዕምሮ እድገት ውስንነት
ገጽ 12





# አዲስ ዘመን

ቅዳሜ

83ኛ ዓመት ቁጥር 194 መጋቢት 14 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





## “ባንኩ ለሚሰነዘርበት የሳይበር ጥቃት አስቀድሞ የመከላከል በቂ አቅም አለው”

### - የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከየትኛውም ወገን ለሚሰነዘርበት የሳይበር ጥቃት አስቀድሞ መከላከል የሚያስችል በቂ አቅም እንዳለው የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር አስታወቀ። በባንኩ የተፈጠረው ክስተት ከሲስተም ማሻሻያ ትግበራ ጋር የተያያዘ እንጂ የሳይበር ጥቃት አለመሆኑንም ገልጿል።

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ላይ መጋቢት 7 ቀን 2016 ዓ.ም የተፈጠረውን ክስተት አስመልክቶ ትናንት ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥቷል።

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ትዕግስት ሃሚድ በዚሁ ወቅት እንዳሉት፤ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከውስጥም ይሁን ከውጭ ለሚቃጡበት የሳይበር ጥቃቶች አስቀድሞ መከላከል የሚያስችል አቅም አለው። ለዚህም በባንኩ አስፈላጊውን የሳይበር ደህንነት ጥንቃቄ እንደሚያደርግ በባንክ ሲስተሞቹ ላይ አስተዳደሩ ያደረገው ፍተሻ ያሳያል።

ከንግድ ባንክና ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በተሠሩት ሥራዎችና በተደረገው የደህንነት ፍተሻና ምርምራ የተፈጠረው የሲስተም ችግር የሳይበር ጥቃት ምክንያት መሆኑን የሚያሳይ ምንም ዓይነት መረጃ አለመገኘቱንም ተናግረዋል።

“ባንኩ ለሚሰነዘርበት ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል


ፎቶ ገበዩ ገብሬ

ወይዘሮ ትዕግስት ሃሚድ

## ውሃን በፍትሐዊነት መጠቀም ሠላምን ለማጽናትና ለመልሶ ግንባታ ወሳኝ ነው

ልጅዓለም ፍቅሬ

አዲስ አበባ፡- በሀገራት መካከል ውሃን በፍትሐዊነትና በእኩልነት መጠቀም ሠላምን ለማጽናት እንዲሁም ለመልሶ ግንባታ ወሳኝ መሆኑ ተገለጸ።

የዓለም የውሃ ቀን “ውሃ ለሠላም” በሚል መሪ ሃሳብ ትናንት ተከብሯል።

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ኢንጂነር

ውሃን በፍትሐዊነት ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

## ቻይና በኢትዮጵያ የቴክኒክና የሙያ ትምህርትን ለማሳደግ የምታደርገውን ድጋፍ አጠናክራ ትቀጥላለች

ታደሠ ብናልፈው

አዲስ አበባ፡- ቻይና በኢትዮጵያ የቴክኒክና የሙያ ትምህርትን ለማሳደግ እያደረገች ያለውን ሁሉን አቀፍ ድጋፍ አጠናክራ ትቀጥላለች ሲሉ የቻይና የሙያና የአዋቂዎች ትምህርት ክፍል ምክትል ዳሬክተር ሊ ዩንግሊን ተናገሩ። ምክትል ዳይሬክተሩ በአዲስ አበባ የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ተቋም የተሠሩ የተለያዩ የፈጠራ ሥራዎችን በትናትናው ዕለት ጎብኝተዋል ።

ጉብኝቱን አስመልክተው ንግግር ያደረጉት የቻይና የሙያና የአዋቂዎች ትምህርት ክፍል ምክትል ዳሬክተር ሊ ዩንግሊን ፤ ቻይና በኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትን ለማሳደግ እያደረገች ያለውን ሁሉን አቀፍ

ቻይና በኢትዮጵያ ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

## “ተገልጋይ ንጉሥ ነው” የሚለው መርሕ የተሻረበት ዘርፍ



ማሕሌት ብዙነህ

በዊልቸር የሚንቀሳቀስ አካል ጉዳተኛ ነው። በሥራው ደግሞ ታታሪ። የመኖሪያ ቤቱ እና የሥራ ቦታው ርቀት ታዲያ የትራንስፖርቱን ዘርፍ አገልግሎት ደጅ ለመጥናት ያስገድደዋል። ከቆሬ ሜክሲኮ፣ ከሜክሲኮም ወደ መገናኛ ከእሁድ ውጪ በየቀኑ ይመላለሳል።

ወደ እነዚህ ሥፍራዎች ያለ ትራንስፖርት አሳብሮ መድረስ አይታሰብም። የከተማ አውቶብሶችም እንደልብ የሚገኙበት ሥፍራ አይደለም። በመሆኑም ወጣት ስንታየሁ አረጋ ታክሲዎችን አዘውትሮ መጠቀም ግድ ይለዋል።

ወጣት ስንታየሁ ከቆሬ መካኒሳ ለመድረስ ሦስት እግር ተሽከርካሪ ከዚያም ታክሲ መጠቀም ግዴታው ነው። ከመካኒሳ ደግሞ ሜክሲኮ፤ ከሜክሲኮም መገናኛ ታክሲዎችን መገልገል ይኖርበታል። ትራንስፖርት የሚጠቀምባቸው አካባቢዎች ደግሞ እንኳን ለአካል ጉዳተኛ ለጉዳት አልባ ሰውም የማይመቹ ናቸው። በተለይ

“ተገልጋይ ንጉሥ ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል







# ኢትዮጵያ የጥራት መሠረተ ልማት ደረጃን ካሟሉ የአፍሪካ ሀገራት መካከል አንዷ ሆነች

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የጥራት መሠረተ ልማት ደረጃን ካሟሉና በጣም የለማና በእጅጉ የአደገ አቅም ያላቸው፤ የብሔራዊ መሠረተ ልማት ተቋም ከገነቡ ስድስት የአፍሪካ ሀገራት መካከል አንዷ መሆኗን የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስታወቀ።

በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የብሔራዊ የጥራት መሠረተ ልማት ማረጋገጫ ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታ አቶ እንዳለው መኮንን ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ እንደተናገሩት፤ "ፓን አፍሪካን ኳሊቲ ኢንፍራስትራክቸር" የተሰኘ ተቋም በየዓመቱ የአፍሪካን የጥራት መሠረተ ልማት ደረጃን በአራት ነጥብ ከፋፍሎ የሚመዝን ሲሆን፤ ተቋሙ በ2023 ባወጣው ሪፖርት ኢትዮጵያ ባከናወነችው ጠንካራ የተቋማት ሥራዎች 3 ነጥብ 4 በማምጣት እንደ አፍሪካ ከተመረጡ ስድስት የለሙና ያደጉ አቅም ያላቸው ሀገራት ውስጥ ተካታለች። የብሔራዊ መሠረተ ልማት ተቋም ከገነቡ ስድስት የአፍሪካ ሀገራት መካከልም አንዷ ሆናለች።

ኢትዮጵያ በጥራት መሠረተ ልማት ልኬት እኤአ በ2014 እና 2017 በነበረ ሪፖርት 2 ነጥብ 4 ወይም በከፊል የለሙ ወይም የጥራት መሠረተ ልማት አገልግሎትን የሚሰጡ ሀገራት ውስጥ የተካተተች እንደነበረች የጠቆሙት ሚኒስቴር ዴኤታው፤ በ2020 እድገቷን ከፍ አድርጋ 3 ነጥብ 2 ላይ የደረሰች ቢሆንም ይህንን ነጥብ ብትይዝም ከከፊል መልማቱ አልተሻገረችም ብለዋል።

በ2023 በተከናወነ ጠንካራ የተቋማት አደረጃጀት ሥራ 3ነጥብ4 በማምጣት እንደ አፍሪካ ከተመረጡ ስድስት የተሻሉ አገልግሎት ሰጪ ሀገራት ውስጥ አንዷ የሆነችው ኢትዮጵያ፤ ይህንን ደረጃ ያገኘችው በሀገር ውስጥ ያለው እንቅስቃሴዋ ብቻ ተመዝኖ ሳይሆን አህጉራዊና ዓለማቀፋዊ ጭምር ታይቶ እንደሆነም ተናግረዋል።

በዚህ የጥራት መሠረተ ልማት ውስጥ ተሳታፊ



አቶ እንዳለው መኮንን

የሚሆኑት 55 ሀገራት እንደሆኑ የጠቆሙት ሚኒስትር ዴኤታው፤ 10 የሚሆኑት ሀገራት የጥራት መሠረተ ልማት የላቸውም፤ አለያም በጣም ጥቂት እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ናቸው፤ 13 የሚሆኑት ደግሞ ውስንነት ያለበት አገልግሎት ያላቸው ናቸው፤ 13 በከፊል ደረጃ ላይ ያሉ ሲሆኑ፤ 13 ተቀባይነት ያላቸው በመጠኑ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ የሚባሉት ናቸው ብለዋል፤ ቀሪዎቹ ስድስቱ ደግሞ ኢትዮጵያን ጨምሮ በጣም የለሙ ከሚባሉት ተርታ የሚመደቡት መሆናቸውን አብራርተዋል።

የጥራት መሠረተ ልማት መረጋገጥ እንደሀገር የሚያስገኘው ጥቅም በርካታ እንደሆነ የጠቆሙት አቶ እንዳለው፤ ተቋማትንና ሀገርን ተወዳዳሪ በማድረግ ጠንካራ ኢኮኖሚን ይገነባል። ከደረጃ በታች የሆነ ምርት ወደሀገር እንዳይገባም በማድረግ የዜጎችን ጤና ይታደጋል። የአካባቢን ደህንነት ከማረጋገጥም አኳያ የማይተካ ሚና ይኖረዋል ብለዋል።

ኢትዮጵያ ውስጥ የተገነባው የጥራት መሠረተ ልማት አቅም ናሙና ልኮ በአንድ ጊዜ ውጤቱን ለማግኘት፤ ለሌሎች ሀገራት የባለሙያ ሥልጠና ለመስጠት፤ ለሀገሪቱ አምራቾች፣ ላኪና አስመጪዎችም ትልቅ እድል የሚፈጥር ነው። ከዚያም አልፎ ለጎረቤት ሀገራት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችልን ሁኔታ ያመቻቻል። በተለይም በደረጃ ከኢትዮጵያ ያነሱ ሀገራትን ለመሳብና ተጠቃሚነትን ለማስፋት ትልቅ አቅም የሚፈጥር እንደሆነም ገልጸዋል።

ሀገር ለላብራቶሪ የምታወጣውን የውጪ ምንዛሪ ከማስቀረት አንጻርም ይህ ደረጃ መፍትሔ ሰጪ እንደሆነ የሚገልጹት አቶ እንዳለው፤ ኢትዮጵያ የዓለም የንግድ ድርጅት አባል ለመሆንም እየሠራች ያለችውን ተግባርም ይህ ደረጃዋን ያፋጥንላታል። በተጨማሪም የኢትዮጵያ ምርት የትኛውም የአፍሪካ መዳረሻ ላይ ተመራጭ እንዲሆንና እንዲላክም ጥሩ መደላደልን የሚፈጥር ነው ብለዋል።

አሁን ደረጃውን የበለጠ ከፍ ለማድረግና አራት ላይ ለመድረስ ጠንካራ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል የሚሉት አቶ እንዳለው፤ በተለይም ከሕጋዊ ሥነልክ አኳያ ከኢትዮጵያ የሥነልክ ኢንስቲትዩት ጋር ተያይዞ የታዩና የተነገሩ ግብረመልሶች ስላሉ እነርሱን ይዞ አቅምን ባጠናከረ መልኩ መሥራትን ይጠይቃል ብለዋል። አሁን የተጀመሩ የማስፋፊያ ሥራዎችም ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸውም አንስተዋል።

በዚህ ዓመት ለማጠናቀቅ በእቅድ የተያዙ በጣም ሰፋፊ መሠረተ ልማቶች መኖራቸውን የጠቆሙት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የላብራቶሪም ሆነ የቢሮ ግንባታን በሚመለከት ከአምስት ቢሊዮን ብር በላይ ተመድቦ እየተሠራ መሆኑንም ጠቅሰዋል።

# ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ ሴቶችን በኢኮኖሚ ተጠቃሚ ማድረግ ያስፈልጋል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የሀገሪቱን ችግሮች ለማቃለል ብሎም ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ ሴቶችን በኢኮኖሚ ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ተገለጸ።

የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት (አዲስ ቻምበር) ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀንን አስመልክቶ "ሴቶች በማኑፋክቸሪንግ" በሚል መሪ ሃሳብ በትናንትናው ዕለት የፓናል ውይይት አካሂዷል።

በወቅቱ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኮሚሽነር ሐና አርዓያሥላሴ እንደገለጹት፤ የሴቶች ተሳትፎ በማኑፋክቸሪንግ እና በግሉ ዘርፍ ውስንነት አለበት። ይህን ውስን ተሳትፎ መጨመር እና ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

አካታች የሆነ የፋይናንስ ዘርፍ አለመኖር ሴቶች በማምረቻው ዘርፍ በስፋት እንዳይሳተፉ እክል እንደሆነ የገለጹት ኮሚሽነር ሐና፤ በተለይም የሴቶችን ተሳትፎ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ማረጋገጥ ሀገሪቷ ለምታደርገው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ወሳኝ እንደሆነ አንስተዋል።

የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ወይዘሮ መሰንበት ሸንቁጤ እንደገለጹት፤ ምክር ቤቱ በግሉ ዘርፍና በመንግሥት መካከል ድልድይ ሆኖ ሲያገለግል ቆይቷል ብለዋል።

ምክር ቤቱ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ አቅምንና የሥራ ፈጠራን በማሳደግ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማድረግ ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር እየሠራ መሆኑን ፕሬዚዳንቷ ገልጸው፤ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፉም ሴቶች እንዲበረታቱ የፖሊሲ ማሻሻያዎች ተደርጎ ወደ ተግባር ተገብቷል ብለዋል።

ወይዘሮ መሰንበት፤ የሴቶችን ሕይወት ለማሻሻልና የሀገሪቱን ችግሮች ለማቃለል እንዲሁም ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ በሴቶች አቅም ላይ ያተኮረ ሥራ መሥራት



ወይዘሮ ሐና አርአያስላሴ



ወ/ሮ መሰንበት ሸንቁጤ

ወሳኝ መሆኑን አንስተዋል።

በተለይም በከተሞች ያለውን የሥራ አጥነት ችግር ለመፍታት የሴቶች ያማከለ ሥራ መሥራት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

ባለፉት ዓመታት በመንግሥትና በሌሎች ተቋማት ሴቶች ወደ አመራርነት እንዲመጡ ከፍተኛ ጥረት ቢደረግም የአመለካከት፣ የተወዳዳሪነት እንዲሁም የገንዘብ አቅርቦት ችግር ሆኖ ቆይቷል ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ በሴቶች የሚመሩ ኩባንያዎችን ያሉባቸውን ችግሮች በዘላቂነት ለመቅረፍ ልዩ ትኩረት የሚሰጥ መንግሥታዊ መዋቅር፣ ቀላል ቢሮክራሲ፣ በቂ የፋይናንስ አቅርቦትና አስቻይ የፖሊሲ አቅጣጫ እንዲኖር ርብርብ ሊደረግ ይገባል ብለዋል።

ምክር ቤቱም በማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ሥራ ፈጣሪ ሴቶችን በማነቃቃት እንዲሁም አቅማቸውም በእውቀት በመገንባት የሕይወትና የሥራ ምርጫቸው የተሻለ እንዲሆን የተለያዩ ሥልጠናዎችን በመስጠት ላይ ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል።



መቅደስ ዳባ (ዶ/ር)

# ኢትዮጵያ የቲቢ በሽታ ስርጭትን በመቀነስ ረገድ ውጤታማ ሥራ አከናውናለች

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የዓለም ጤና ድርጅት የቲቢ በሽታ ስርጭትና የሞት ምጣኔን ለመቀነስ ያስቀመጠውን ግብ በማሳካት ውጤታማ ሥራ ማከናወኗን የጤና ሚኒስቴር ገለጸ።

18ኛው ዓመታዊ የቲቢ በሽታ ምርምር ጉባኤና ዓለም አቀፍ የቲቢ ቀን "በርግጥም የቲቢ በሽታን መግታት እንችላለን!" በሚል መሪ ቃል ትናንት መከበር ጀምሯል።

በወቅቱ የጤና ሚኒስትር መቅደስ ዳባ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ የጤና ድርጅት እ.አ.አ. ከ2015 እስከ 2020 ድረስ የቲቢ በሽታ ስርጭትና የሞት ምጣኔን ለመቀነስ የተቀመጠውን ግብ አሳክታለች።

በዓለም አቀፍ ደረጃ የተቀመጠውን የሞት ምጣኔና ስርጭት መጠን እንዲሁም የበሽታውን የጉዳት መቀነስ የተቻለ ቢሆንም፤ የቲቢ በሽታን ሙሉ በሙሉ ለመግታት የሚደረገው ጥረት አሁንም መቀጠል አለበት ብለዋል።

እንደሚኒስትሯ ገለጻ፤ በተሠሩ ሥራዎች ስኬቶች የታዩ ቢሆንም አሁንም በየቀኑ 54 ሰዎች በበሽታው ይሞታሉ። በበሽታው ተጠቂዎች ላይ የሚደርሰው አድሎና መገለል አልተገታም።

በዚህም ለቀጣይ ሰባት ዓመታት አዲስ ስትራቴጂ ተነድፎ የቲቢ በሽታን ለመግታት እየተሠራ ነው ያሉት ዶክተር መቅደስ፤ የቲቢ በሽታን ብቻ ሳይሆን ሌሎች ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለመግታት ጥረት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

ባለፉት ዓመታት የቲቢ በሽታ ስርጭትን ለመቀነስ በተደረገው እንቅስቃሴ የአየር ንብረት ለውጥ፤ ግጭት እና ኮሮና ቫይረስ ዋነኛ ተግዳሮቶች እንደነበሩ አንስተዋል።

በጤና ሚኒስቴር የበሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር መሪ ሥራ አስፈጻሚ ሕይወት ሶሎሞን (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ የዓለም ጤና ድርጅት በቲቢ በሽታ አዲስ የሚያዙ ሰዎችን ቁጥር በ31 በመቶ እና በበሽታው የሚከሰት የሞት ምጣኔን ደግሞ በ34 በመቶ ለመቀነስ ያስቀመጠውን ግብ ኢትዮጵያ ማሳካት ችላለች።

በኢትዮጵያ በየዓመቱ 156 ሺህ ሰዎች በቲቢ በሽታ ይጠቃሉ ተብሎ ይገመታል ያሉት ዶክተር ሕይወት፤ በተሠሩ ሥራዎች 90 በመቶ የሚሆኑት ላይ በሽታው በምርመራ ልየታ እንደሚገኝ አመላክተዋል።

የቲቢ በሽታ በጊዜ ታክሞ ሊድን የሚችል መሆኑን አስታውሰው፤ በወቅቱ ሕክምና ካለማግኘት የተነሳ በሀገር አቀፍ ደረጃ በየዓመቱ 20 ሺህ ሰዎች በበሽታው ሕይወታቸውን ያጣሉ ሲሉ አስረድተዋል።

የሞት ምጣኔው ከባለፉት ዓመታት ጋር ሲነጻጸር በከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ አሳይቷል። በቀጣይም በሽታውን ለመግታት ባለሙያዎችን የማሠልጠን፣ መድኃኒቶችን የማቅረብ፣ የሕክምና ሂደቱን የማዘመን ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል።

በሀገሪቱ 42 ሺህ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች መኖራቸውን የጠቀሱት መሪ ሥራ አስፈጻሚዋ፤ በባለሙያዎቹ በኩልም የግንዛቤ ሥራና ታማሚዎችን ከማኅበረሰቡ ለይቶ በማውጣት አስፈላጊው የጤና ክብካቤ ሥራ እንደሚሠራ አብራርተዋል።



አቶ ሰለሞን ደስታ

## በኢትዮጵያ የፋይናንስ ተቋማት ቁጥር 117 ደረሰ

### - አጠቃላይ ሀብታቸውም 3 ነጥብ 3 ትሪሊዮን ብር ደርሷል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ በሥራ ላይ ያሉ ፋይናንስ ተቋማት ቁጥር 117 መድረሱን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አስታወቀ። የፋይናንስ ተቋማቱ አጠቃላይ ሀብት ወደ ሦስት ነጥብ ሦስት ትሪሊዮን ብር ማደጉንም ባንኩ ገልጿል፡፡

የኢትዮጵያ የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ የግንዛቤ ፈጠራና ውይይት መድረክ ትናንትና ሲካሄድ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ምክትል ገዥ እና የኢትዮጵያ የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ የቦርድ ሰብሳቢ አቶ ሰለሞን ደስታ እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ የፋይናንስ ዘርፍ በከፍተኛ ደረጃ በማደግ ላይ ይገኛል።

በአሁኑ ወቅት የሚገኙትን 31 የግልና የመንግሥት የንግድ ባንኮችን ጨምሮ በሥራ ላይ ያሉት የፋይናንስ ተቋማት ቁጥር ባለፈው ዓመት ከነበረበት ከ14 በመቶ በላይ ጭማሪ በማሳየት 117 መድረሱን ጠቁሟል።

የፋይናንስ ተቋማቱ አጠቃላይ ሀብታቸውም አምና ከነበረበት በ15 ነጥብ 3 በመቶ ዕድገት አሳይቶ ሦስት ነጥብ ሦስት ትሪሊዮን ብር መድረሱን አስታውቀው፤ ተቀማጭ ገንዘባቸውም የ16 ነጥብ አምስት በመቶ ዕድገት አሳይቶ ሁለት ነጥብ ሦስት ትሪሊዮን ብር መድረሱን አረጋግጠዋል።

ካፒታላቸው ደግሞ ባለፈው ዓመት ከነበረው በ25 በመቶ ጨምሮ 304 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር መድረሱን አመላክተው፤ የመደበኛ ተቀማጭ ሒሳብ ቁጥራቸው በ21 ነጥብ 5 በመቶ ጭማሪ አሳይቶ ወደ 147 ሚሊዮን ከፍ ማለቱን ጠቁመዋል፡፡

የፋይናንስ ዘርፉ ዕድገት ከማሳየቱ ባሻገር በዓለም አቀፍ እንዲሁም በብሔራዊ ባንክ የጤንነት መለኪያ መስፈርት አኳያ ሲታይ በጤናማ ደረጃ ላይ መሆኑን ተናግረው፤ ከአካታችነት አንጻር ስንመለከተውም ዘርፉ ከፍተኛ ለውጥ እያስመዘገበ ነው ብለዋል።

የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ዕድገት ጠንካራ እንዲሆን ባንኮችና አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ገንዘብ ከኅብረተሰቡ በመሰብሰብ በብድር መልክ ወደ ኢኮኖሚው እንዲገባ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ገልጸው፤ ይህን ማሳካት የሚቻለው ገንዘብ አስቀማጮች በፋይናንስ ተቋማት ላይ ያላቸውን መተማመንን ማሳደግ ሲቻልና የፋይናንስ ሥርዓቱ የተረጋጋ ሆኖ መቀጠል ሲችል መሆኑን ተናግረዋል። ለዚህም የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ ወሳኝ ሚና እንዳለው አስረድተዋል።

የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ ወደሥራ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ ተግባራትን ማከናወኑን አስታውሰው፤ ይሁን እንጂ ፈንዱ እንዲጠናከርና የተጣለበትን ኃላፊነት እንዲወጣ ለማስቻል የሁሉንም ባለድርሻ አካላት እገዛ እንደሚጠይቅ ጠቁመዋል፡፡

የኢትዮጵያ የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ደሳለኝ አምባው (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ፈንዱ ከተቋቋመበት መጋቢት 2015 ዓ.ም ጀምሮ የተለያዩ ተግባራትን ማከናወኑን አንስተዋል።

ተቋሙን በሰው ኃይልና በፋይናንስ ለማጠናከር ከሚሠሩ ሥራዎች ጎን ለጎን የማኅበረሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፤ የመድረኩ ዓላማም ለማኅበረሰቡ ፈንዱ ስለሚያከናውናቸው ተግባራት ለማሳወቅና አቅሙን ለመገንባት የሚያስችሉ ግብዓቶችን ለመሰብሰብ ያለመ ነው ብለዋል።

# ሰብዓዊ የውሃ ፍላጐትን ለማመጣጠን በትብብር መሥራት ይገባል

## - በዓለማችን ከሁለት ቢሊዮን ሰዎች በላይ ንጹሕ ውሃ አያገኙም

**አዲሱ ገረመው**



አዲስ አበባ፡- የሁሉንም ሰው ሰብዓዊ የውሃ ፍላጐትና መብት ለማመጣጠን በትብብር መንፈስ መሥራትና ውሃን ለሠላም መጠቀም እንደሚገባ ተገለጸ፡፡

የአፍሪካ የውሃ ማኔጅመንት የልኅቀት ማዕከል ዓለም አቀፉን የውኃ ቀን ምክንያት በማድረግ "ውሃን ለሠላም መጠቀም" በሚል መሪ ሀሳብ ትላንትና ውይይት አካሂዷል፡፡

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት ተወካይ ፕሮፌሰር ታደሰ ፈታሂ በመድረኩ እንደገለጹት፣ በዓለም አቀፍ ነባራዊ ሁኔታ የሕዝብ ቁጥር እየጨመረና የውኃ አጠቃቀሙም እየጨመረ በመምጣቱ ቁልፍ የውሃ እጥረትና የውሃ ጥያቄን እየተፈጠረ ነው። በውሃ ላይ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን ለመከላከል የተፈጥሮ ሀብቶችን በጋራ መንከባከብ ይገባል፡፡

ቀጣይነት ያለው የአየር ንብረት ለውጥ የውሃ ቀውስን ከፍ እንደሚያደርገው የገለጹት ፕሮፌሰር ታደሰ፤ በተለይም የአፍሪካ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ እየጨመረ በመምጣቱ በአሕጉሩ ያሉትን የተፈጥሮ ሀብቶች በመጠበቅና በመንከባከብ ችግሩን መከላከል እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

ውሃ ለዘላቂ ልማት ግቦች ትልቅ ሚና እንዳለው የተናገሩት ፕሮፌሰር ታደሰ፤ የሁሉንም ሰው ሰብዓዊ መብትና ፍላጐት ለማመጣጠን በትብብር መንፈስ ውሃን ለሠላም መጠቀም ይገባል ብለዋል።

ዘላቂነት ያለው የውሃና የንጽሕና አጠባበቅ ሕጎችን በአግባቡ መተግበር፣ የውሃ መሠረተ ልማትና ወጥነት ያለው ኢንቨስትመንትን ማስፋፋትና የቁጥጥር ማዕቀፎችን በመተግበር ረገድ ሀገራት በጋራ መሥራት እንዳለባቸው ጠቅሰዋል፡፡

እንደ ፕሮፌሰር ታደሰ ገለጻ፤ በአሁኑ ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሁለት ቢሊዮን በላይ ሰዎች ንጹሕ ውሃ አያገኙም። ከእነዚህ ዜጎች መካከል ደግሞ አብዛኞቹ በታዳጊ ሀገራት የሚገኙ ናቸው። ይህ በተለይ አፍሪካ በውኃ ችግር ተፅዕኖ ላይ መውደቋን የሚሳይ ነው፡፡

የዓባይ ውኃ ጉዳይ ተመራማሪ ያዕቆብ አርሳኖ (ዶ/ር)፤ የሰው ልጅ የሥልጣኔ አመጣጥ ባሕላዊ፣ ቁሳዊና ሳይንሳዊ ግኝቶች በውኃ ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን ጠቅሰዋል። ስለዚህም ውሃ የቅንጦት ሳይሆን ትክክለኛ የሰው ልጅ ጥያቄ ነው ብለዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ ንጹሕ የመጠጥ ውኃ የሚያገኙት ጥቂቶች ብቻ መሆናቸውን የገለጹት ተመራማሪው፤ ንጹሕና ለኢነርጂ የሚበጅ ጤናማ የሆነ እንዲሁም ዘላቂ ልማት ላይ ለውጥ ሊያመጣ የሚችል የውሃ አጠቃቀም ሊኖር እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

የውሃ ሀብት ላይ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ ትብብርን ማጠናከርና የውሃ ሀብት አጠቃቀምና አስተዳደር ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይገባልም ነው ያሉት፡፡

የውሃ ደህንነት ስጋትን ለመቀነስ እንዲሁም ብሔራዊ ጥቅምና ልማትን ለማስፋፋት ባለሙያዎችን ማብቃት እንደሚገባም ተመራማሪው ገልጸዋል፡፡

በየዓመቱ እኤአ መጋቢት 22 ቀን የዓለም የውኃ ቀን የሚከበርበት ቀን ሲሆን፤ ይህም የዓለም የውሃ ችግርን ለመቅረፍ ለማሰብ ያለመ ነው። በዘንድሮ ዓመትም “ውሃን ለሠላም መጠቀም” በሚል መሪ ሀሳብ ምሑራንና የተለያዩ ሀገራት የውሃ ባለሙያዎች በተገኙበት በአዲስ አበባ ተከብሯል።

# ለአየር ንብረት ለውጥ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ሀገራት ለታዳጊ ሀገራት ድጋፍ ማድረግ ይኖርባቸዋል

**ሞገስ ጸጋዬ**




አዲስ አበባ፡- ለአየር ንብረት ለውጥ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ሀገራት በችግሩ ግንባር ቀደም ተጠቂ ለሚሆኑት ታዳጊ ሀገራት የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ እንደሚኖርባቸው የመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልማትና ክርስቲያናዊ ተራድዖ ኮሚሽን ከመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ጋር በመሆን ከፖሊሲ አውጪዎችና ከባለድርሻ አካላት ጋር በአየር ንብረት ፍትሐዊነት ላይ የምክክር መድረክ አካሂደዋል፡፡

የሁሉም አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ተወካይ ዶክተር ቲናሼ ጉምቦ እንደገለጹት፤ የአየር ንብረት ለውጥ የዓለም ከፍተኛ ችግር ነው። በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት በተለይ በአፍሪካ አሕጉር ከፍተኛ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ቀውስ እየደረሰ ነው።

በመሆኑም በአየር ንብረት ለውጥ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው የበለጸጉ ሀገራት በችግሩ ለተጎዱ የአፍሪካ ሀገራት ለሚሠሯቸው የአረንጓዴ ልማት ሥራዎች ድጋፍ በማድረግ የአየር ንብረት ፍትሐዊነትን ማስፈን ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

ለችግሩ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ሀገራት እንደ አፍሪካ ላሉ ሀገራት ለተለያዩ የልማት ሥራዎች የሚውል የገንዘብ ድጋፍ ሊያደርጉ እንደሚገባ ገልጸው፤ በጉዳዩ ዙሪያ የሚወጡ ፖሊሲዎች በችግሩ ለተጎዱ አካላት መፍትሔ የሚሰጥ መሆን አለበት ብለዋል።

የአየር ንብረት ለውጥ ለአፍሪካ አህጉር ትልቅ ፈተና ሆኗል ያሉት ተወካዩ፤ ችግሩን ለመቅረፍ በተናጠል ሳይሆን የጋራ ትግበራ ያስፈልጋል። አፍሪካ በርካታ የዕምነት ተቋማት ያሉባት አሕጉር በመሆኗ የእምነት መሪዎችም የአየር ንብረት ለውጥን ከመከላከል አንጻር ሚናቸውን ማሳደግ አለባቸው ሲሉም አሳስበዋል።

ደንን በመንከባከብና ስለ ደን ጠቀሜታ ለዕምነት ለተከታዮች በማስተማር የዕምነት ተቋማት በአየር ንብረት ለውጥ ሚናቸውን ማሳደግ እንዳለባቸውም አስገንዝበዋል፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ልማትና ክርስቲያናዊ ተራድዖ ኮሚሽን ምክትል የልማት መምሪያ ኃላፊ ገብረሥላሴ አጽብሐ እንደገለጹት፤ የመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ በኢትዮጵያ ካሉ ቤተክርስቲያንና የልማት ሥራ የሚሠሩ ድርጅቶች ጋር የመሠረቱት የአየር ንብረት ፍትሐዊነት የሚባል ስብስብ መኖሩን ጠቅሰዋል።

በአየር ንብረት ለውጥ ችግር የሚደርስባቸው ደሃ ሀገራት የልማት ሥራዎችን እንዲሠሩና ደንን እንዲንከባከቡ የገንዘብ ድጋፍ እንደሚያስፈልግም ገልጸዋል፡፡

እንደ ገብረሥላሴ ገለጻ፤ በሀገር ውስጥ በአየር ንብረት ለውጥ ችግር የተነሳ የኅብረተሰቡን የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ አልተቻለም። በሌላ በኩል ደኖችን ለእርሻ፣ ለማገዶ እንጨትና ለግንባታ አገልግሎት ጥቅም ማዋል ደግሞ የአየር ንብረት ለውጥ ተጽእኖ እንዲበረታ አድርጓል።

ይህን ለመታደግ በእንጨት ለቀማና በከሰል ማክሰል ጥገኛ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ንብ ማነብ፣ በእንስሳት ማደለብና በፍራፍሬ ልማት እንዲሠማሩ የማድረግ ሥራ ኮሚሽኑ እየሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ ደን ልማት የብሔራዊ የ”ሬድ ፕላስ” ፕሮግራም አስተባባሪ ይተብቱ ሞገስ (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የአየር ንብረት ለውጥ ስጋት እየጨመረ ነው። ይህን በመንግሥት አቅም ብቻ መታደግ ስለማይቻል የእምነት ተቋማት ሚና ከፍተኛ ነው።

የእምነት ተቋማት በሕዝቡ ዘንድ የተደማጭነት ስላላቸው ደንን በመጠበቅ ረገድ ትልቅ ሥራ መሥራት ይቻላሉ ያሉት ዶክተሩ፤ የአየር ንብረት ለውጥ ችግር የተፈጠረው ባደጉ ሀገራት ነው።ችግሩን መቋቋም ያቃተው ደግሞ ደሀ የአፍሪካ ሀገራት ናቸው።አፍሪካ የችግሩ ተሸካሚ በመሆኗ ከአደጉ ሀገራት የአየር ንብረት የፍትሐዊነት ድጋፍ እንደሚያስፈልጋት ገልጸዋል ።

ለአየር ንብረት ለውጥ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው የበለጸጉ ሀገራት ለታዳጊ ሀገራት ከችግሩ ጋር ተስማሚ ሆነ የልማት ሥራዎችን እንዲሠሩ ድጋፍ ማድረግ እንዳላባቸው አመልክተው፤ የሚወጡ ፖሊሲዎች የተጎዱ ሀገራትን ያገናዘቡ መሆን እንዳለባቸው አስረድተዋል።

# አገልግል

የቅዳሜ መጽሔት

የቁስጥ ገጾች



‹‹ ስለ ሀገር መጸለይ ከአንድ እውነተኛ አማኝ የሚጠበቅ ተግባር ነው››

- ኡስታዝ ጀማል በሽር

ገጽ 6



ያልፈዘዘው የሕይወት ንቅሳት

ገጽ 16

የመንገድ መዘጋት ስታክሲዎች ያመቻል!

ገጽ 17

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ኪነጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

አፍሪቃዊቷ መልኅቅ

## ዘመኑን የዋጀ ቴክኖሎጂ ለውጤታማ አገልግሎት !

**ዳንኤል ዘነበ**

በመንግሥት ተቋማት የሚስተዋለው ዝርክርክና ውስብስብ አሠራር ሀገሪቱን ለከፍተኛ ችግር ሲዳርጋት ቆይቷል፡፡ በተለይም ያላትን ውስን ሀብት በአግባቡ መጠቀም የሚያስችል ዘመናዊና ቀልጣፋ ሥርዓት መዘርጋት ባለመቻሉ ሀገሪቱ አጠቃላይ በኢኮኖሚ ልማት ለመራመድ የምታደርገውን ጥረት ወደኋላ እየጎተተ ይገኛል፡፡ ለብልሹ አሠራርና ለምዝበራ በር በመክፈቱ ሀገሪቱ ከድህነት ለመውጣት የምታደርገውን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ የእምቧይ ካብ አድርጎታል ፡፡

አሁን ላይ ግን ምስጋና ለቴክኖሎጂ ይግባውና ዘመኑን የዋጀ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ብልሹ አሠራሮችን ለማስቀረት እዚህም እዚያም የሚደረጉ ጥረቶች አሉ። ከሚደረጉት ጥረቶች መካከልም በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን መጠቀም አንዱ ነው። በተለይም የመንግሥት ተቋማትን አሠራር ለማዘመን ያስችላሉ የተባሉ በርካታ ሥርዓቶች ከውጭ ተቀድተው ተግባራዊ ቢደረጉም በሚፈለገው ልክ ውጤት ማምጣት አልተቻለም ፡፡

ይሁንና አሁን አሁን የተለያዩ የመንግሥት ተቋማት አሠራራቸውን ለማዘመን ፊታቸውን ወደ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ አዙረዋል፡፡ በዚህ ረገድ በአዲስ አበባ ባሕል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ዘመኑን የሚመጥን የኔትወርክ መሠረተ ልማትና የደህንነት (security system) በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡

የቢሮ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ቴዎድሮስ እሸቱ፣ የኔትወርክ መሠረተ ልማቱ እንዲሠራ የመልማት ፍላጎት በማቅረብ አስፈላጊ ጥናት እንዲደረግ ለአዲስ አበባ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ በማቅረብ በሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ሥራው ታምኖበት ተጀምሯል ።


የመሠረተ ልማቱ ዋና ዓላማ ለቢሮው በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት የሚሰጣቸው አገልግሎቶችን ለማዘመን እና ቢሮውን (smart office) በማድረግ ከወረቀት ነፃና ዘመኑን የሚዋጅ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ያለመ መሆኑን አስረድተዋል ፡፡

እንደ እርሳቸው ማብራሪያ፤ የኔትዎርክ መሠረተ ልማቱ በአንድ ማዕከል ቁጥጥር የሚደረግ ሲስተም ሲሆን ደረጃውን የጠበቀ የራሱን የተቋሙ ስያሜን ጨምሮ የፕሮሞሽንና ኮሙኒኬሽን ሥራ የሚሠራባቸው 22 ደረጃቸውን የጠበቁ ስክሪኖች፣ ሦስት መቶ ሰውን ማስጠቀም የሚችሉ የገመድና ገመድ አልባ ኢንተርኔት የኔትወርክ መሠረተ ልማት፣ የአዲስ አበባ ሙዚየምን ጨምሮ ሙሉንም ሕንጻውንና በሕንጻው ዙሪያና በሕንጻው ውስጥ (Indoor and Outdoor) የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ደህንነት የሚጠብቁ ብዛት ያላቸው ካሜራዎች (Security Camera) እና አጠቃላይ ኔትወርኩን የሚቆጣጠሩ ሰርቨሮችን ያካተተና በቢሮው ታሪክ የመጀመሪያው ትልቁ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፕሮጀክት ነው። ይህም ኔትወርኩ የሚጠቀማቸው ሲስተሞችና ግብዓቶች በጣም ዘመናዊ ቴክኖሎጂን ሲሆን የሰርቨር ክፍል፣ ትልልቅ ማቀዝቀዣ ማሽኖች፣ አጠቃላይ የኔትወርክ መሠረተ ልማቱን የሚቆጣጠር ራሱን የቻለ መቆጣጠሪያ ክፍል (control room) ያካተተ እንደሆነና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ከግማሽ ቢሊዮን ብር በላይ ተበጅቶለት እየተሠራ መሆኑን ዳይሬክተሩ አብራርተዋል ፡፡

ፕሮጀክቱ በስምንት ወራት ለማጠናቀቅ በእቅድ ተይዞ እየተሠራ እንደሆነ የሚናገሩት አቶ ቴዎድሮስ፣ በሁለቱም ቢሮዎች ማለትም ከአዲስ አበባ ባሕል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮና ከኤኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ሥራውን ለመከታተል የተዋቀረ ቡድን መኖሩን ገልጸዋል። ቡድኑም በየደረጃው በአመራርና







**የኔትወርክ መሠረተ ልማቱ አጠቃላይ ሥራው በአራት ወራት አፈጻጸሙ 68 በመቶ ደርሷል ፤**

በቴክኒክ ኮሚቴው እየተገመገመ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር እየተደረገበት እንደሚገኝ አመልክተዋል። "አጠቃላይ ሥራው በአራት ወራት አፈጻጸሙ 68 በመቶ የደረሰ ሲሆን፤ ፕሮጀክቱ ሙሉ ለሙሉ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ለማጠናቀቅ ታቅዶ እየተሠራ ነው" ሲሉም ተናግረዋል ፡፡

በመጨረሻም፤ የቢሮው አመራሮች፣ አጠቃላይ ሠራተኞችና ባለድርሻ አካላት ለፕሮጀክቱ ስኬት እስከአሁን ላደረጉት ቀና ድጋፍና ትብብር አመስግነዋል። ፕሮጀክቱን ከዳር ለማድረስ የሚደረገው ድጋፍ ተጠናክሮ እንዲቀጥልና በሥራው ለተሠማሩ ባለሙያዎች ሁለንተናዊ ድጋፍ በማድረግ መሠረተ ልማቱን ከግብ ለማድረስ እንዲሠሩ ዳይሬክተሩ አሳስበዋል ፡፡

እኛም ይህ ፕሮጀክት የቱሪዝም ዘርፉን በዲጂታል ሥርዓት የታገዘ አድርጎ ለጎብኝዎች ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት ከዘርፉ የሚፈለገውን ጥቅም ለማግኘት በእጅጉ የሚረዳ በመሆኑ ይበል የሚያስብል መሆኑን መግለጽ እንወዳለን፡፡

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# ‹‹ ስለ ሀገር መጸለይ ከአንድ እውነተኛ አማኝ የሚጠበቅ ተግባር ነው››

- ኡስታዝ ጀማል በሽር

ስምስም መንግሥቱ

በእድሜው ሳይሆን፤ እየሠራ ባለው ሥራ ከበሬታ የሚሰጠው አንደበተ ርቱዕ ሰው ነው። ለሃይማኖታዊ ሥርዓት መገዛት፣ የተማረውን፣ ያወቀውን፣ ያለውን ለሌሎች ማካፈል ከልጅነቱ የጀመረው በጎ ተግባር ነው። እርሱ በእምነቱ፤ ሌሎችም በእምነታቸው የፀኑ እንዲሆኑ፣ ለወገናቸው እና ለሀገራቸው ቀናኢ እንዲሆኑ እና በጎ ምግባር እንዲኖራቸው በማስተማርና በማንቃት የሚችለውን ሁሉ እያደረገ ይገኛል።

ይህ ሰው ተወልዶ ያደገው አውቶቡስ ተራ ኳስ ሜዳ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነው። ጥሩ የልጅነት ትውስታ እንዳለውም ይናገራል። በአበበ ቢቂላ ኳስ ሜዳ ውስጥ ኳስ በመጫወት ነው ልጅነቱን ያሳለፈው። ከዘመናዊ ትምህርት ጎን ለጎን ሃይማኖታዊ ትምህርትም ይማር ስለነበር በእምነቱ የታነፀ ሰው ለመሆን ችሏል። ይህ ሰው ኡስታዝ ጀማል በሽር ይባላል።

ኡስታዝ ጀማል እንደሚገልጸው፤ ወደ ሃይማኖቱ ለማዘንበሉ በተለይ የወላጅ እናቱ ግፊት ቢኖርም፤ እርሱም ፍላጎቱ ስለነበረው ትኩረቱን ወደ ሃይማኖቱ ሊያደርግ ችሏል። በልጅነቱ በተወሰነ ደረጃ በቁስ ትምህርት ቤት፣ በኋላም የቁርአን ትምህርት በሚሰጥባቸው በአንዱ በመስጅድ ውስጥ ተምሯል።

በሃይማኖቱ ላይ እንዲገፋ የቤተሰብም የእርሱም ፍላጎት ጠንካራ በመሆኑ ሃይማኖቱንም ዘመናዊውንም ትምህርት በአንድ ላይ በሚያስተምር አባድር በሚባል ትምህርት ቤት ውስጥ በመግባት እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ ተማረ። ተወልዶ ባደገበት አካባቢ መስጊዶች መኖራቸው ሃይማኖታዊ ትምህርቱን ለማጠናከር አግዞታል።

የሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በአዲስ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው የተማረው። የከፍተኛ ትምህርት ደግሞ ሳውዲ መዲና እስላሚክ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ሸሪዓ (ሎው ፋክልቲ) በመከታተል በመጀመሪያ ዲግሪ ተመርቋል። ከሳውዲ መዲና ወደ ሀገሩ ከተመለሰ በኋላ ደግሞ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሊንጉስቲክ የትምህርት ክፍል ፊሎሎጂ በሚባል የትምህርት ዘርፍ በሁለተኛ ዲግሪ(ማስተርስ) ተመርቋል። በተጨማሪም በአሜሪካን ሀገር አጫጭር ስልጠናዎችንም በመውሰድ በተለያዩ ዘርፎች ክህሎቱን አዳብሯል።

ኡስታዝ ዘመናዊ ትምህርቱን በዚህ መልክ ቢያጠናቅቅም፣ ነፍሱ ያለው ሃይማኖቱ ላይ በመሆኑ እንቅስቃሴዎቹ ሁሉ ከእምነት ጋር የተያያዘ ነው። በመሆኑም በተለያዩ ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥም ይሳተፋል። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን እንደጨረሰ ነበር በኢትዮጵያ ሙስሊሞች ወጣቶች ድርጅት በመግባት ተሳትፎ ማድረግ የጀመረው። በዚህ ውስጥም ከሃይማኖቱ ጋር በተያያዘ እውቀት ማግኘቱን ይገልጻል።

በዚህ ድርጅት ውስጥ ተሳትፎ ማድረጉም የትምህርት እድል ተጠቃሚ እንዲሆን አስችሎታል። በወቅቱ ከመዲና እስላሚክ ዩኒቨርሲቲ አንድ ልዑክ በድርጅቱ ተገኝቶ የትምህርት እድል እንዲያገኙ ያደርጋል። ኡስታዝ ጀማል ዩኒቨርሲቲው የሰጠውን ፈተና አልፈው የትምህርት እድሉን ካገኙት መካከል አንዱ መሆን እንደቻለ ነው የገለጸው። ያገኘው የትምህርት እድል በቅድስና ከመካ ቀጥሎ በሚጠቀስ ከተማ ውስጥ እንደሆነና ትምህርቱንም ለስድስት ዓመታት እንደተከታተለ ነው ያስረዳው።

ኡስታዝ ጀማል፤ የተማረውንና ያወቀውን ለራሱ ብቻ ሳይሆን፣ ለሌሎችም ማካፈል ያስደስተው ስለነበር ተማሪ እያለ ጭምር ነበር በትምህርት ቤቶች፣ በተለያዩ መድረኮችና በመስጊድም በመገኘት ሌሎችን በማስተማር በጎ የሆነ አገልግሎት ሲሰጥ የበረው። በተለይም በውጭ ሀገር በቆየባቸው ጊዜያቶች ኢትዮጵያውያንን በማሰባሰብ ይንቀሳቀስ ነበር። በተለያዩ ምክንያት አስተማሪ ክፍል ሳይገባ ሲቀር አስተማሪውን ለመተካት ያደርግ የነበረው ጥረት መሠረት እንደሆነለትም ያስታውሳል።

ኡስታዝ ጀማል እንደሚለው በቀድሞው ሥርዓት ወቅት በሙስሊም እምነት ተከታዮች ላይ የተለያዩ ጫናዎች ይደርሱ ነበር። በወቅቱም ድምጻችን ይሰማ በሚል እንቅስቃሴ ይደረግ ነበር። ይሁን እንጂ የወቅቱ መንግሥት የእምነቱን ተከታዮች በእስር በማንገላታት ጫናው እየበረታ ሲመጣ ከጫናው ለማምለጥ ወደ አሜሪካን ሀገር ለመሄድ ተገዷል።

በአሜሪካን ሀገርም የኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ (የኢትዮጵያ ኮሙዩኒቲ) ባቋቋሙት የሰላም ፋውንዴሽን ውስጥ በመቀላቀል ሃይማኖታዊ ትምህርቱ ላይ የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን የሰላም ፋውንዴሽኑ ኢማም በመሆን በተሻለ እንዲንቀሳቀስ በማድረግ አስተዋጽኦ አበርክቷል። መስጊዶች ላይም ኢማም ሆኖ ማህበረሰቡን አገልግሏል።

የኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ በውጭ ሀገር ይደራጅ የሚል ሃሳብ ቀርቦ፤ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በኩል አቡነ አባፋኑኤል የተባሉ አባት ሰብሳቢ ሆነው እርሱ ደግሞ ምክትል ሰብሳቢ ሆኖ በአሜሪካን ሀገር ተመርጠው፤ በዳያስፖራው ማህበረሰብ የተቋቋሙትን አብይ የሆኑ የሃይማኖት ተቋማትን በማሰባሰብና በማደራጀት ጉባኤው ይዞ የተነሳውን ዓላማ ለማሳካት የድርሻውን እየተወጣ ይገኛል።

በተጨማሪም በአሜሪካን ዋሽግተን ዲሲ ቨርጂኒያ ውስጥ የሰላም ፋውንዴሽን ኢማም ሆኖ እያገለገለ ነው። በግሉም የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራ ሲሆን፤ የኪንግስ ኦፍ ዓባይ ሚዲያ ባለቤትና ሥራ አስኪያጅም ነው።

እኛም የረመዳን ጾም ምክንያት በማድረግ ከኡስታዝ ጀማል ጋር ቆይታ ለማድረግ የወደድነው በወጣትነት የእድሜ ክልል ውስጥ ሆኖ ከሼሆዎች ባልተናነሰ በሃይማኖቱ ላይ ባለው እውቀት፣ ሌሎችም ሃይማኖታዊ ጽናት እንዲኖራቸው በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎችና በሚሰጠው ትምህርት፣ አልፎ ተርፎም ለሀገሩ በጎ አሳቢና ተሟጋች በመሆኑ ነው። በተለይም ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታን በተመለከተ በግብጽ በኩል ለሚነሳው ፀብ አጫሪነት የአፀፋ ምላሽ በመስጠት የሚያደርገው እንቅስቃሴ ይጠቀሳል። ስለዚህም ከዚህ ሀገር ወዳድ ዜጋ ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ እነሆ እንላለን። መልካም የንባብ ጊዜ።

**አዲስ ዘመን፤ በዚህ በምንገኝበት ረመዳን የጾም ወቅት ከአማኙ ምን ዓይነት ተግባራት ይጠበቃሉ?**

**ኡስታዝ ጀማል፤** ረመዳን የጾም ጊዜ ማለት ነው። በሃይማኖታችን፣ የእስልምና መገለጫዎች ወይንም የእስልምና ማዕዘናት ተብለው ከሚለዩት አምስት ዋና ዋናዎቹ መሠረቶች መካከል ረመዳን አንዱ ነው። በጌታና በመልእክተኛው መመስከር አንዱ ነው። ቁጥር ሁለት ላይ ስግደት ይቀመጥና በሶስተኛ ደረጃ ምጽዋት ወይንም ዘካ ነው። አንድ ሰው ከገንዘቡ ላይ የሚበቃውን ወጪ ካወጣ በኋላ ተርፎት ከሚያስቀምጠው ገንዘብ ላይ ቀንሶ መስጠት ግዴታ ይኖርበታል። ቀጥሎ ያለው ደግሞ ጾም እና የሀጂ በዓል መፈጸም ነው። ስለዚህ እነዚህ በሃይማኖቱ አምስት እርከን ተብለው ከተያዙት መካከል አንዱ ነው ማለት ነው።

የሃይማኖቱ ድንጋጌ በሌሎቹ መጻሕፍት በኦሪት፣ በወንጌልም ላይ የተሰበኩ የጾም ዓይነቶች ውስጥ አንዱና አዲስም እንዳልሆነ እኛም ያንን ተቀብለን እንደምናስተናግደው ነው ቁርአን መጽሐፍ የሚጠቅስልን። ልክ በእነርሱ ላይ እንደተጻፈው ሁሉ በእናንተም ላይ ተጽፏል ብሎ ነው የሚያስቀምጠው። በዚህ የረመዳን ጾም የሙስሊሙና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እምነት ተከታዮች በአንድ ላይ ጾም መያዛቸው ወይንም መጀመራቸው የዚህን ትርጉም ያያይዘዋል የሚል እምነት አለኝ።

ጾምማለትበትክክለኛውየሃይማኖትትርጉም፤ሰዎችሥጋዊ አካላቸውን በማድከም፣ መንፈሳዊ አቅማቸውን ከፍ የሚያደርጉበት ነው። እራሳቸውን የሚገመግሙበት፣ ለቀጣይ ጊዜ ደግሞ የሚዘጋጁበትና የሚነሳሱበት ሲሆን፣ በተለይም ቁርአን የወረደበት፣ ወይንም ራዕዩ በነብዩ መሐመድ ላይ መገለጽ የጀመረበት ወር ተብሎ ስለሚታሰብ ከቁርአን ጋር ያለን ግንኙነት ከፍ እንዲል ሃይማኖቱ ያስተምራል።

በቁርአኑ ላይ ያለንን አቋም፣ ቁርአኑ ላይ ያሉትን አስተምሮቶች በሙሉ እንድንመረምር፣ ቁርአንን በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ እንድንቀራ፣ በተለይ ደግሞ በማታው ክፍለ ጊዜ ቁርአኑ ሙሉ ለሙሉ እየተቀራ ስግደት የሚከናወንበት ሥርዓት አለ። ቁርአን ወደ 604 ገጾች አሉት። አንድ ሰው ወይንም ኢማም፤ ቁርአኑን እያነበበ ከኋላ ያሉት ሰዎች እየሰሙት የሚከናወንና የቁርአኑ ጊዜ የሚታወስበት ነው። ቁርአኑ የተፃፈው በአረብኛ በመሆኑ በመካከል ላይ የመማማር ሁኔታ ስለሚኖር የቁርአኑ ሃሳብ እንዲታወስ ይደረጋል።

ስለጾም በቁርአን የተደነገገ ነው። ከጠዋት ጎህ ሲቀድ ጀምሮ ፀሐይ እስክትጠልቅ ባለው ጊዜ ከምግብ፣ ከመጠጥና ከግብረ ሥጋ ግንኙነትና ከሌሎችም ከሚከለከሉ ተቆጥቦ መጾም ይጠበቃል። ከቁርአን ጋርም ግንኙነቱን የበለጠ የሚያጠናክርበት የጾም ጊዜ ነው። ሌላው አንድ ሰው በመራቡ ምክንያት በሚሰማው ስሜት የረሃብን አስከፊነትና በዚህ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ምን ያህል እንደተጎዱ የሚረዳበት፣ ለድሆች ምግብ፣ ገንዘብ፣ ያለውን በማካፈል እንዲያሳልፍ ይጠበቃል። ረመዳን ጸሎትና ስግድትም በተለየ ሁኔታ የሚያስፈልግበት ወቅት ነው።

> ሌላው ቢቀር ገቢ እያላቸው ነገር ግን አንዴ የሚያገኙ፣ ሌላ ጊዜ የሚያጡ ከሆኑ፤ ወይንም ደግሞ ገቢ የሚያገኙበት ነገር ተቋርጦ ለምግብ መግዣ የሚያውሉትም ሆነ ለቤት ኪራይ የሚከፍሉት አጥተው በድንገት ኑሮአቸው ላይ ጫና ከተፈጠረ፣ እንዲሁም ለጤና ችግር ተጋልጠው በአስከፊ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ ከወደቁ በዘካ እንድናስባቸው ታዘናል

**አዲስ ዘመን፤ የእምነቱ ተከታዮች የረመዳን ጾምን በተለየ ሁኔታ ሲናፍቁ ይስተዋላል። የተለየ ምክንያት አለው?**

**ኡስታዝ ጀማል፤** እውነት ነው። የሰው ልጅ በተፈጥሮው መልካም መሆንን ይፈልጋል። ነገር ግን በመብላት፣ በመጠጣት ሥጋዊ ፍላጎት በጣም ሲበዛ እነዚህ ነገሮች ከሰይጣን ጋር ተባብሮ ወደማይፈገው ነገር ያስገቡታል ተብሎ ይታሰባል። ከህሊናው ጋር ጠብ ከሚያስገቡት ኢሞራላዊ ድርጊቶች ሁሉ እንዲቆጠብ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል



ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹ ስለ ሀገር መጸለይ ከአንድ እውነተኛ አማኝ...

ከ6ኛው ገጽ የዞረ

ያደርገዋል። ጾም በሚመጣበት ወቅት እነዚህን ሁሉ ክፉ ነገሮች ሰባብሮ ያስቀምጥለታል፤ ሰይጣንም ይታሰራል ይላል ሃይማኖቱ።

በመሆኑም ጾም ከነዚህ ሁሉ በማሳረፍ ልዩና ጥሩ የሆነ ስሜት ይሰጣል። ከጾም ውጭ ባለው እሳቤም ሰዎች በመጀመሪያዎቹ የጾም ጊዜያቶች የረሃብ ስሜት ቢሰማቸውም ነገር ግን በምግብ ጫና ምክንያት ከሚፈጠርባቸው የምግብ ዑደት እረፍት ያገኛሉ። በሁለቱም መንገድ ጾም ተቀባይነት አለው። በነፍስም፣ በሥጋም ደስታ ይገኛል ማለት ነው።

በመንፈሳዊው ከሰዎች ጋር የሚፈጠረው ተግባርም ሌላው ጥቅምና ደስታንም የሚሰጥ ነው። የተጣሉ ይቅር ይባባላሉ፤ በአፍጥር ሰዓትም ይሰባሰባሉ፤ ከጾም በኋላ ሰው በሚበላው ምግብና መጠጥም ይደሰታል። የሚዘጋጀው ምግብ ከአዘቦቱ የተለየ ሆኖ መቅረቡም እንዲሁ ደስታን ይሰጣል። በህብረት ሆኖ በመስገድ ፈጣሪን ማመስገንም ስላለ የረመዳን ጾም በጸሎትም፣ በመመገብም፣ ህብረት የሚበዛበት፣ መተሳሰቡ፣ መዋደዱ፣ ይቅርባይነቱ ጎልቶ የሚታይበት ነው። እነዚህ የረመዳን ጾም እንዲናፈቅና እንዲወደድ ከሚያደርጉት ምክንያቶች ጥቂቶቹ ናቸው።

**አዲስ ዘመን፤ አሁን ላይ ሀገር ውስጥ በተፈጠረው አለመረጋጋትና ጦርነት ምክንያት ጥሩ ኑሮ የነበራቸው በርካታ ወገኖቻችን ተፈናቅለው በመጠለያና በተለያየ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ይኖራሉ። እነዚህ ወገኖች በዚህ የጾም ወቅት በሚፈጸመው ዘካ ከምስኪኑ በተለየ የሚታዩበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል?**

**ኡስታዝ ጀማል፤** ዘካ የሚሰጠው በምክንያት ነው። ለማን ምን ይሰጥ የሚለው ቀደም በቁርአን መጽሐፍ ላይ በግልጽ ተቀምጧል። በቁርአን መጽሐፍ ላይ ለስምንት ዓይነት ሰዎች ነው ዘካ እንዲሰጥ የታዘዘው። ከነዚህ ስምንት ሰዎች አንዱ ስደተኛ (ሙሳፊር) የሚለው ነው። በጦርነት ወይንም በሌላ ችግር ምክንያቶች ቤት ንብረታቸውን ጥለው ከአካባቢያቸው ርቀው በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ያሉት ብቻ ሳይሆኑ፣ በተሻለ ኑሮ ውስጥ የሚገኙ ሀብታሞች እንኳን ሆነው ስንቅ ይዘው ከቤታቸው ወጥተው በመንገድ ላይ ስንቅ ቢያልቅባቸው ለጊዜው ባሉበት ቦታ ሆነው ተቸግረዋልና ለነዚህም ቢሆን ሃይማኖቱ ከሚያዘው የዘካ ገንዘብ ላይ ይገባቸዋል የሚል በቁራን ላይ ተቀምጧል። ስለዚህ ከስምንቱ ግዴታዎች ውስጥ አንዱ ስደተኛን ታሳቢ ያደረገ ነው ማለት ነው።

ሌላው ቢቀር ገቢ እያላቸው ነገር ግን አንዴ የሚያገኙ፣ ሌላ ጊዜ የሚያጡ ከሆኑ፤ ወይንም ደግሞ ገቢ የሚያገኙበት ነገር ተቋርጦ ለምግብ መግዣ የሚያውሉትም ሆነ ለቤት ኪራይ የሚከፍሉት አጥተው በድንገት ኑሮአቸው ላይ ጫና ከተፈጠረ፣ እንዲሁም ለጤና ችግር ተጋልጠው በአስከፊ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ ከወደቁ በዘካ እንድናስባቸው ታዘናል።

**አዲስ ዘመን፤ በዚህ በረመዳን የጾም ወቅት እየተፈፀመ ካለው አንዱ በጎዳና ላይ በህብረት ማፍጠር ነው። ለጎዳና አፍጥር ተብሎ የሚዘጋጀው ምግብ ማግኘት ሳልቻሉ ወገኖች ቢውል የሚል በአንዳንዶች ሃሳብ ይነሳል። በአጠቃላይ ይሄ በሃይማኖታዊ ሥርዓቱ እንዴት ይታያል?**

**ኢስታዝ ጀማል፤** በጋራ ሆኖ ወይንም አብሮ መመገብን በተመለከተ እስልምና ያስቀመጣቸው ልምዶች አሉ። ዋናው መሆን ያለበት አንድ ሰው ምግብን ጨምሮ ገንዘቡንና የመሳሰሉትን ማውጣት ያለበት ወይንም ርዳታ (ሰደቃ) የሚያደርገው ጽድቅ ለማግኘት ከሆነ፤ በጦርነት ወይንም በተለያየ ምክንያት ችግር ውስጥ ለሚገኙ፣ ትክክለኛ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ሲያውለው ነው።

ከምግቦች ሁሉ ተቀባይነት የሌለው ምግብ የሠርግ ምግብ ነው ይባላል። ለምን ቢባል። የማይፈልገው ተጠርቶ የሚጋበዝበት፤ መመገብ የሚፈልገው ደሃ ግን ከበር ላይ እንዲሄድ ስለሚገፈተር ነው። ይህ አባባልም የነብያችን ነው።

በኢትዮጵያ ከጎረቤት፣ ከወዳጅ ዘመድና ቤተሰብ ጋር በቤት ውስጥ ተሰባስቦ አብሮ ማፍጠር፣ መብላት የተለመደና የቆየ ባህል ነው። የጎዳና ላይ አፍጥር መርሃ ግብር ግን ከዚህ የተለየ ነው። ሕግም የለውም። ግን ደግሞ ክልክል ነው የሚልም ነገር የለውም። እንዲህ ያለው ነገር ኢትዮጵያ ውስጥ የተጀመረው በቅርብ ነው። የማይተዋወቅ ሰው ሁሉ የሚታደምበት መሆኑ አዲስ ነገር ነው። በአጋጣሚው አብሮ መብላትን መሠረት ባደረገው



**እውነተኛ ሃይማኖቱን ተቀብሎ የሚጾም ሰው ሊተገብራቸው ከሚገቡና ጾሙንም ከሚደግፋለት አንዱ ሰላማዊ መሆንና ለሰላም መጸለይ ነው። ስለዚህ ሁላችንም አማኞች በጸሎታችን ውስጥ ለሀገራችን ጸሎት ማድረግ ይጠበቅብናል። የጾሙም አካል ነው።**

በእዚህ መርሃ ግብር ላይ እንደሠርጉ ቤት የሚከለከል የለም። አብሮ ለመብላትም አይለምንም። የተዘጋጀው ለሁሉም በመሆኑ በደስታ ሁሉም ይካፈላል። ሁሉንም አካታች ነው።

የጎዳና ላይ አፍጥር መርሃ ግብር መንፈሱ ጥሩ ነው። ግን ደግሞ ከጥቅሙ ጉዳቱ እንዳያመዝን መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ወደ ሕክምና እና ወደተለያዩ አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች የሚሄዱ ሰዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ ይሄን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሌሎችን እንቅስቃሴ በማይገድብ ሁኔታ መከናወን ይኖርበታል። የፀጥታ አስከባሪዎችና ከሌሎችም የመንግሥት አካላት ጋር የተናበበ መሆን ይኖርበታል።

**አዲስ ዘመን፤ የረመዳን ጾምና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የሚጾመው የፋሲካ ጾም በአንድ ቀን መሆኑ ምን ስሜት አለው? እንዲህ ያለ የታሪክ አጋጣሚስ አለ?**

**ኡስታዝ ጀማል፤** ብዙ ጊዜ የሁለቱም እምነት ፆም በቀናት ልዩነት ነው የሚጀመረው። በእኔ እድሜ እንዲህ ያለውን የግጥምጥሞሽ አጋጣሚ ግን አላውቅም። በእኔ እምነት ምናልባት ተከስቶ ነገር ግን አሁን ላይ የማህበረሰቡ ንቃተ ህሊና እየጨመረ መምጣት፣ የተሻለ አብሮነት በመፈጠሩ ያስተዋልነው ነገር ሊሆን ይችላል ብዬ አስባለሁ። የቀን መቁጠሪያ ያመጣው እንደሆነም መዘንጋት የለበትም።

ምናልባት በትንሽ ነገር ፀብ ለማንሳት የሚሞክሩ አንዳንዶች ይሄን አጋጣሚ ላያጎሉት ይችላሉ። ነገር ግን ባገኙት አጋጣሚ አንድነትን ፈጥረው፤ ሰዎችን በመግባባት፣ እርስ በርስም ለመማማር ልባቸው ክፍት የሆኑ ሰዎች ደስተኛ እንደሚሆኑ አምናለሁ። ናቸውም ማለት እችላለሁ። ጻድቅ የሆኑ ቄሶችም ይሁኑ ሼኮች ይህ አጋጣሚ ተአምር ነው። እኛንም ሊያስተምር የመጣ ነው ብለው ሊያነሱ ይችላሉ። እኔም ይህ ዓይነት መንፈስ ነው ውስጤን የሚሰማው።

**አዲስ ዘመን፤ ለሀገር ሰላም አብዝቶ መፀለዩ በተለይም ኢትዮጵያ አሁን ላይ የገጠማት ሰላም ማጣት ወደ መረጋጋት እንዲመለስ ጸሎቱ የበለጠ መሆን አለበት የሚሉ ሰዎች አሉ። የሁለቱ እምነት ተቋማት በተመሳሳይ ጊዜ ጾም መጀመራቸውም ለዚህ መልካም አጋጣሚ እንደሆነም እንዲሁ ያነሳሉ። እዚህ ላይ ምን ሃሳብ አለህ?**

**ኡስታዝ ጀማል፤** በበለጠ ሁኔታ ወይንም ከተለመደ ውጭ በሚለው ሃሳብ አልስማማም። የሚያጋጥመው የችግር ሁኔታ እንደዘመኑ የተለያየ ይሆናል እንጂ ሀገር በተለያየ ጊዜ ችግሮች እያጋጠሟትና እያለፈች ነው አሁን ላይ የደረሰችው። ችግሮችን ነብያቶችም አስተናግደውታል። ጻድቃኖችም እንዲሁ በችግር ውስጥ አልፈዋል። ኢየሱስም ቢሆን መከራን አሳልፏል። መከራን ችግርን ተቀብለው ያሳለፉ ሁሉ አብረዋቸው መጥፎዎች በመኖራቸው ነበር።

ስለዚህ በዚያን ወቅት ያደርጉ ከነበረው ከሆነው አንዱ ለምሳሌ ነብዩ ኢብራሂም (አብረሃምን) ቁርአን መጽሐፍ ላይ ሲጠቅሰው፤ ጌታዬ አለ ይላል። ሀገሬን አማን አድርግልኝ ብሎ ጸለየ ይላል። በጣም ብዙ ቦታ አብረሃም ወይንም ኢብራሂም ከሁሉ ነገር አስቀድሞ ሀገሩን ሰላም እንዲያደርግለት ነው ጌታውን የጠየቀው። ጌታዬ ጌታችን እባክህን መጀመሪያ አማን ስጠን፣ ሰላም ስጠን፣ ጣኦት እንዳናመልክ እራሳችንን ጠብቀን እያለ ይፀልይ ነበር ይላል በቁርአን ውስጥ።

ስለዚህ ለሀገር መፀለይ፣ የምንፀልየው ነገር ደግሞ በፈጣሪ ዘንድ እንዲሰማ ወይንም ተግባራዊ እንዲሆን ፤ እኛም ሰላማዊ ለመሆን የምናደርገው ጥረት ሃይማኖታዊ ነው ከጥንት የጀመረ ነው። አቤልና ቃኤል ላይ ይጀምራል። ቁርአን መጽሐፍ ላይ አቤልና ቃኤልን ይጠቅሳቸዋል።

አንዱ አንዱን ገደለው ይላል። የገደለበትንም ምክንያት ይጠቅሳል። በቅናት የተነሳ ነበር የገደለው ይላል። ስለዚህ የቅናት መንፈስን ከመዋጋት ጀምሮ ነው የፀሎቱ አስፈላጊነት በቁርአኑም ሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተስማሙ ሃሳቦች በብዛት የሚንሸራሸሩት። ስለዚህ የሰው ልጆች ከቅናት መንፈስ ባነሰ፣ የእገሌ ዘር በዚህ ቦታ መኖር የለበትም፣ በሚል የራሱ ባልሆነ ነገር ነው አለመግባባት ውስጥ እየገባ ያለው። ዘር የሰጠን ጌታ ነው። አንድ ሰው ዘር ፈልጎና መርጦ አይወለድም። ይሄ በእኛ እጅ ያለ ጉዳይ አይደለም።

እውነተኛ ሃይማኖቱን ተቀብሎ የሚጾም ሰው ሊተገብራቸው ከሚገቡና ጾሙንም ከሚደግፋለት አንዱ ሰላማዊ መሆንና ለሰላም መጸለይ ነው። ስለዚህ ሁላችንም አማኞች በጸሎታችን ውስጥ ለሀገራችን ጸሎት ማድረግ ይጠበቅብናል። የጾሙም አካል ነው።

**አዲስ ዘመን፤ በጾም ወቅት የነበረው ትህትና፣ የልብ መሰበር ለምንድነው የማይቀጥለው? ለሁሌም ሳይሆን ቀርቶ የሰላም ማጣትና መደፍረስ የሚኖረውና ወንድም በወንድሙ ላይ የሚነሳው ለምንድነው? የሚለው የብዙዎች ጥያቄ ነው። በዚህ ላይ ያንተ አስተያየት ምንድነው?**

**ኡስታዝ ጀማል፤** በእኔ እምነት ጾሙ የሃይማኖታዊ ጾም አልነበረም ማለት ነው። ቀደም ሲል እንዳነሳሁት ጾም ደስታው የሚመነጨው ከሁለት ነገር በመነሳት ነው። አንዳንዱ ከምግብ ጋር ብቻ ያይዘዋል። ሌላው ደግሞ መንፈሳዊ ሁኔታው ደስታ ይሰጠዋል።

ስለዚህ ባሕላዊ የሆነ ጿሚ ወይንም ከምግብ ጋር የተያያዘ ጾም፣ ጾሙ ሲያበቃ ወደ ባሕሉ ይመለሳል ማለት ነው። እንደዚህ ሲሆን ያ ሰው በጣም ይቸገራል ማለት ነው።

ሃይማኖታዊ ሥርዓቱ የሚያዘውን ተከትለው የሚፈጽሙ ሰዎች ግን ሁሌም አንድ ናቸው። አይለወጡም። ጾም ሲመጣ የበለጠ ጠንካራ ነው የሚሆኑት። ይበረታሉ። ጾሙ ሲወጣ አብረው አይወጡም። እያንዳንዳችን አማኞች ይህን ፆም የተቀበልንበት አግባብ ምንድነው? ስሜታችንስ ምንድነው? ብለን እራሳችንን መጠይቅ ይኖርብናል።

**አዲስ ዘመን፤ ተጨማሪ መልዕክት ካለህ?**

**ኡስታዝ ጀማል፤** ጾም፤ ያለፈውን ገምግመን ለሚቀጥለው መልካም ለመሆን የምንዘጋጅበት መሆኑን ተገንዝቦ የሚጾም ሰው ተጠቃሚ ይሆናል። ያተርፍበታል። ጾምን እንደ ወቅት የሚያይ ሰው ግን አንድ ፋሽን መጥቶ እንደሚያልፈው ዓይነት ነው የሚቆጠረው። ስለዚህ እነዚህን ልዩነቶች ማስተዋል ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን፤ በጣም አመሰግናለሁ። መልካም የጾም ጊዜ ይሁንልህ**

**ኡስታዝ ጀማል፤** እኔም አመሰግናለሁ። የሙስሊሙም፣ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮችም በጾማቸው እንዲተጉ፣ መልካም የጾም ጊዜም እንዲሆንላቸውና ጾማቸውም ከፈጣሪ ዘንድ እንዲደርስላቸው እመኛለሁ።

# ቻይና በኢትዮጵያ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ድጋፍ አጠናክራ ትቀጥላለች ብለዋል።

የኢትዮጵያ የቴክኒክና የሙያ ትምህርትን በማሳደግ በእውቀት የተገነባና ቴክኖሎጂን የተላመደ የሰው ኃይል ለማፍራት በትብብር እንደሚሠሩም አመልክተዋል።

የቻይና የኢኮኖሚ እድገት የመጣው ተግባር ተኮር የሆነ የቴክኒክና የሙያ የትምህርት ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረጓ ነው ያሉት ዳሬክተሩ፤ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለማሳደግ በተግባር የተደገፈ ትምህርት መዘርጋት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።


በቴክኖሎጂ፤ በኤሌክትሮኒክስ፣ በማኑፋክቸሪንግና በሌሎች የሙያ ዘርፎች የበለጸገ የሰው ኃይል በኢትዮጵያና በምስራቅ አፍሪካ ለማፍራት ቻይና በትኩረት እየሠራች ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ዳሬክተር ሊ ዩንግሊ አያይዘውም የቻይና መንግሥት በኢትዮጵያ የቴክኒክና የሙያ ትምህርትን ለማሳደግ ብቻ ሳይሆን በሁለቱ ሀገሮች ጠንካራ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ለመፍጠር እየተሠራ ነው ሲሉ ጠቁመዋል።

የሥራ ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ተሻለ በሬቻ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያና ቻይና በትምህርት ዘርፍ በተለይ በቴክኒክና ሙያ ትምህርት መስክ በትብብር እየሠሩ ይገኛሉ ብለዋል።

የቴክኒክና የሙያ ትምህርትን በኢትዮጵያ ለማሳደግና ለማስፋፋት ቻይና በግብዓት፣ በገንዘብ፣ በቴክኒክና በኤሌክትሮኒክ ትምህርት ላይ ትብብር እያደረገች ትገኛለች ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ይህም በእውቀትና በቴክኖሎጂ የታነጸ ትውልድ ለማፍራት እያስቻለ ነው ብለዋል።

የኢንጂነሪንግና የቴክኒክና የሙያ ትምህርትን



በተግባር ለማስተማር፣ ግብዓት ለማሟላት፤ መምህራንን ለማብቃት ሁለቱ ሀገሮች በትብብር እየሠሩ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ኢትዮጵያ ከቻይና ጋር በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ላይ በትብብር መሥራቷ ዓለም ከደረሰበት የቴክኖሎጂ የእድገት ደረጃ ላይ እንድትደርስ የሚያደርጋት መሆኑን ገልጸዋል።

በኢትዮጵያና በቻይና መንግሥት ስምምነት ከሁለት ዓመት በፊት የቴክኒክና የሙያ ትምህርትን ለማሳደግና ለማስፋፋት የሉባን ዓውደ ጥናት እንደተቋቋመ ያወሱት ዶክተር ተሻለ፤ ዓውደ ጥናቱ በአሁኑ ጊዜ የቴክኒክና የሙያ መምህራንና ተማሪዎችን በእውቀት፣ በልምድና በፈጠራ እያበቃ ይገኛል ብለዋል።

ከቴክኒክና የሙያ ትምህርት በተጨማሪ የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስና የባቡር ቴክኖሎጂ ትምህርት ለማስፋፋት ከቻይና ጋር ስምምነት መደረሱን አመልክተው፤ የሁለቱ ሀገሮች የትምህርት የትብብር ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያና ቻይና በቴክኒክና የሙያ ትምህርትን በትብብር ለመስጠት ከሁለት ዓመት በፊት የደረሱትን ስምምነት በማሳደግ በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ፣ በባቡር ቴክኖሎጂ፣ በማኑፋክቸሪንግ በትብብር ለመሥራት በትናትናው ዕለት ስምምነት አድርገዋል።

# “ባንኩ ስሚሰነዘርበት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ባንኩ በሞባይል ሲስተሙ ላይ ባደረገው የማሻሻያ ሥራ ችግሩ መከሰቱ በምርመራ ተለይቷል ያሉት ወይዘሮ ትዕግስት፤ በዚህም ባንኩ የሲስተም ማሻሻያ በሚደረግበት ወቅት ቀደም ብሎ ሌላ ሲስተም ማለትም T24 (ኮር ባንኪንግ ሲስተም) ጥቅም ላይ የዋለ የስሌት ሞጁል ወይም አልጎሪዝም በመውሰድ በሞባይል ባንኪንግ ሲስተሙ ላይ በቀጥታ ለመተግበር በተደረገ ሙከራ ችግሩ መከሰቱን አብራርተዋል።

አስተዳደሩ ባደረገው ምርመራ “የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሲስተም ጃር ፋይልስ ሶርስ ኮድ (JAR Files Source Code) ወስዶ ባደረገው ምርመራ የፕሮግራሚንግ ቅደም ተከተል ወይም ሎጂካል ፍሰቱ የተዛባ ሆኖ አግኝቶታል” ሲሉ ተናግረዋል።

በዚህም ሲስተሙ ገንዘብ የሚያወጡ የባንኩ ደንበኞች ገንዘብ ሲያወጡ መቀነስ የነበረበትን መጠን ሳይቀንስና ባላንስ ለመሥራት ወይም ለማመዛዘን አመቺ ሁኔታ ሳይፈጥር ክፍያ ይፈፅም እንደነበር የምርመራ ውጤቱ ያስረዳል ሲሉ ወይዘሮ ትዕግስት ገልጸዋል።

ከዚህ በመነሳት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ላይ የተከሰተው ችግር የሳይበር ጥቃት ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ለመለየት በተደረገ ጥልቅ የሆነ የመረጃ ቋት ትንታኔ መሠረት ምንም አይነት ከውጭ ወደ ባንኩ ሥርጎ በመግባት ጉዳት ያደረሰ አደጋ አለመኖሩ መረጋገጡን አስታውቀዋል።

በቀጣይም ተጨማሪ ምርመራዎችና የፎረንሲክ ሥራዎችን በማከናወን ውጤቱን ለኅብረተሰቡ እንደሚገለጽ አመልክተዋል።

የባንኩ ደንበኞችም ሆኑ የትኛውም ማኅበረሰብ በተለያዩ የማኅበራዊ ትስስር ገጾች ላይ ባንኩ የሳይበር ጥቃት እንደደረሰበት እየተናፈሰ ያለው ወሬ ምንም አይነት ተጨባጭ መረጃ ላይ ያልተመሠረተ መሆኑን ተገንዝበ አስፈላጊውንና የተለመደውን የባንክ አገልግሎት ካለምንም ስጋት እንዲጠቀሙ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# “ተገልጋይ ንጉሥ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሰልፍ አስከባሪዎች በሌሉበት ጊዜ ለመሳፈር እጅግ እንደሚቸግረው ወጣት ስንታየሁ ይናገራል።

ኢፕድም ወጣቱን ባናገረበት ወቅት ጀሞ ለመሄድ ተራ የያዙ የሜክሲኮ ተሳፋሪዎች ሰልፍ ከሳርቤት ከፍ ብሎ የሚገኘው የአፍሪካ ኅብረት ግቢ ሊደርስ ጥቂት ቀረሽ ሆኖ ነበር የሚታየው። በሌላኛው መስመርም ሰፈራ የሚባል አካባቢ ለመሄድ ትራንስፖርት የሚጠብቁ አገልግሎት ፈላጊዎች እልፍ ሆነው ነው የተደረደሩት።

አናት በሚበሳ ፀሐይም ይሁን አጥንት በሚያሳሳ ቁር አገልግሎቱን ለማግኘት የሚጓጉ የአውቶብስም የታክሲም ትራንስፖርት ፈላጊዎች ቁጥር የትየለሌ ነው። ፀሐይ ከእቶን እሳት በሚልቅ ነዲዷ እየተንቀለቀለችም ይሁን ተስለምልማ ከአድማሷ ስታሽልብ የማያሸልበው የአዲስ አበቤ ነዋሪዎች የየቅፅበት ፍላጎት ነው - ትራንስፖርት።

በመገናኛ፣ በአውቶብስ ተራ፣ ፒያሳ፣ መርካቶ እና ጎሮ በመሳሰሉት ቦታዎችም ተመሳሳይ ነገሮች የተለመዱ ናቸው። ያሰቡበት ቦታ በእግር ቢሄዱ ከሚደርሱበት ጊዜ በላይ ቆሞ መጠበቅን፤ አለመታከትን የተማሩ የትራንስፖርት አገልግሎት ጠባቂ ዜጎች እልፍ አልባ ድርድር ሠርተው ተሰትረው ነው የሚስተዋሉት።

አገልግሎቱን ለረጅም ጊዜ ጠብቆ ማግኘት የሚቻለውም ሰልፍ አክባሪና ሰልፍ አስከባሪ ሲኖር ነው። እነኝህ ከሌሉ ጉልበተኛ በጉልበቱ ተጋፍቶና ተገፈታትሮ መሳፈር የሰርክ ትዕይንት ሆኗል።

ታዲያ ወጣት ስንታየሁ ከሰፈሩ መካኒሳ ቆሬ መገናኛ የሚደርሰው ከገንዘቡ ባሻገር ፍዳውን ከፍሎ ነው። ወደቤቱ ሲመለስም ሆነ ሲሄድ ለታክሲዎች እጥፍና ከዚያ በላይ ለመክፈል ይገደዳል። ይህም የሚሆነው ታክሲው ከተገኘ እና የረዳት አሽከርካሪውን ግልምጫና ስድብ ከቻለ ነው።

ወጣት ስንታየሁ ታክሲዎች በታሪፍ መሠረት እንዲሠሩ፤ የታክሲ ረዳቶች ሰው እንዲያከብሩ እና የትራንስፖርት አገልግሎት አቅራቢዎች በተገቢው ሰዓት ሙሉ ጊዜአቸውን እንዲያገለግሉ ይሻል።

ወይዘሮ አበበች አደራው (ስማቸው የተቀየረ) የጀሞ ሦስት ኮንዶሚኒየም ነዋሪ ናቸው። የሰባት ወር ነፍሰጡር የሆኑት ወይዘሮዋ የሥራ ቦታቸው ሜክሲኮ አካባቢ ነው። መሥሪያ ቤታቸውም የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ አይደለም። በዚህ የተነሳ ታክሲ አልያም አውቶብስ ጠብቆ መምጣትና መሄድ ግድ ብሏቸዋል።

ሰልፍ አክብሮ የሚሰለፍ እና ተራ አስያዥ በሚኖርበት ጊዜ በቀላሉ ከፊት ተሰልፈው አገልግሎት እንደሚያገኙ የሚናገሩት ወይዘሮ አበበች፤ ተራ አስከባሪ በማይኖርበት ጊዜ ግን እስከ ሁለት ሰዓት ድረስ ጠብቀው እንደሚሄዱ ይናገራሉ። ብዙ ጊዜ በታክሲዎች ለመሄድ እንደማይደፍሩም ነው የሚያስረዱት። ለምን ቢባል አገልግሎት አሰጣጣቸው አስቸጋሪ ስለሆነ ባይ ናቸው።

ምንም እንኳ የታክሲ አገልግሎት ሰጪዎችን መንግሥት የነዳጅ ድጎማ ሥርዓት ተጠቃሚ ቢያደርጋቸውም፤ እጥፍና ከእጥፍ በላይ ማስከፈላቸው የተለመደ ነው ይላሉ።

ብዙ ጊዜ ለትራፊክ ፖሊስ ከስሰውም ጉዳዩ እንደ መብት ጥያቄ ሳይሆን እንደ የግል ፀብ ታይቶ ወደ ግልግል እንደሚገባ ያስረዳሉ። የታክሲዎች ፈላጭ ቆራጭነት ስላማረራቸውም አውቶብሶችን እንደ አማራጭ እንደሚጠቀሙ ነው የሚናገሩት።

ወጣት ሰመረ ጎይቶም ሰፈራ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ተከራይቶ የሚኖር የትራንስፖርቱ ዘርፍ ገፈት ቀማሽ ነው። ታክሲዎች የሚያደርሱት እንግልት እንዳማረረው የሚናገረው ይህ ወጣት፤ መሥመር ቆራርጦ መጫን በታክሲዎች የተለመደ ተግባር መሆኑን ይናገራል።

ከተፈቀደው ታሪፍ እጥፍና ከዚያ በላይ ማስከፈል፤ ማመናጨቅ እና ሕዝብ ጭኖ ነዳጅ መቅዳትን የመሳሰሉ በርካታ በደሎች ተገልጋይ ላይ እንደሚያደርሱ ይናገራል።

መካሰሱና መጨቃጨኩ ሲሰለቸኝ በታክሲ ረዳቶች ተመን የተጠየኩትን እየከፈልኩ እና ስድባቸውን ሰምቼ እንዳልሰማሁ እያለፍኩ አገልግሎቱን በተራዘመ ሰዓትም ቢሆን እያገኘሁ ነውም ይላል። ለተቆጣጣሪዎች ለበርካታ ጊዜያት አመልክቶ ምንም ዓይነት ቅጣት ሲቀጡ እንዳላየም ያስረዳል።

ነገሩ እንዴት ነው ሲል ኢፕድ የጠየቃቸው የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ዳዊት ዘለቀ፤ በከተማዋ በትራንስፖርት አገልግሎት ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶች ለመፍታትና አገልግሎቱን ለማሳለጥ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ይናገራሉ።

ከነዚህም ለአካል ጉዳተኞች እና ነፍሰጡሮች አገልግሎቱንም ቅድሚያ እንዲያገኙ የሚያስችል አሠራር ተግባራዊ የማድረግ ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው ይላሉ።

በከተማው የሚገኙ በአውቶብሶች ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የዊልቸል ማስገቢያ ራምፕ ከማዘጋጀት ጀምሮ ለአካል ጉዳተኞች እና ነፍሰጡሮች በቀላሉ የሚጠቀሙበት የተለየ መቀመጫና ቦታ ያለ መሆኑን ያብራራሉ።

ነገር ግን ታክሲዎች ለረጅም ዓመታት ያገለገሉ በመሆናቸው ለአካል ጉዳተኞች የሚሆኑ ተጨማሪ አስቻይ ነገሮች የላቸውም ብለዋል።

ታክሲዎች ከታሪፍ በላይ ያስከፍላሉ የሚለውን ቅሬታ አስመልክቶም በሰጡት ምላሽ፤ የትራንስፖርት አገልግሎት ርቀቱ እና የሚያስከፍለው የገንዘብ መጠን ተገልጋዩ በሚታይ ቦታ ፊት ለፊት እንዲያንጠለጥሉ ወይም እንዲለጥፉ ይገደዳሉ ብለዋል። ይህ የሚለጠፈው ታሪፍም የቢሮው ማኅተም ያረፈበት መሆን እንደሚገባው አቶ ዳዊት ያብራራሉ።

በተጨማሪም ታሪፉን በተለያየ መንገድ ኅብረተሰቡ እንዲያውቀው እንደሚደረግና የተለጠፉት ወረቀቶችም በየተርሚናሉ ቁጥጥር እንደሚደረግባቸው ነው የሚናገሩት።

ከተለጠፈው ታሪፍ በላይ የሚያስከፍሉትን ለተቆጣጣሪዎች በመጠቆም ማስቀጣት ይቻላል ብለዋል።

ከሕገወጥ ጋር ተስማማ ወይም ታረቅ የሚል የቁጥጥር ሠራተኛ ካጋጠመም ሆነ በታክሲ የረዳቶች ሥነምግባር በተመለከተ ለሚገጥም ችግር የአገልግሎት ሰጪዎች ሥነምግባር መመሪያ መሠረት በዲሲፕሊን የሚቀጡ መሆኑንም ተናግረዋል። በመሆኑም ኅብረተሰቡ የሚያጋጥመውን ማንኛውም ሕገወጥ ድርጊት በየተርሚናሉ የሚገኙ የቁጥጥር ሠራተኞች ወይም ለትራፊክ ፖሊስ በማሳወቅ እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን ያብራራሉ።

በከተማው 12 ሺህ የሚጠጉ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች ይገኛሉ ያሉት አቶ ዳዊት፤ ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ ተቆጣጣሪ ሠራተኛ መመደብ እንደማይቻል ያስረዳሉ።

ተገልጋዮች ከነፃ የስልክ መስመር 9417 ዘወትር በሥራ ሰዓት በመደወል መጠቆም የሚቻል መሆኑን ጠቅሰው፤ ይሄ ጉዳይ የተቆጣጣሪ ተግባር ብቻ ሳይሆን የእያንዳንዱ ተገልጋይ ኃላፊነት በመሆኑም እራሱን ከዚህ ሕገወጥ ተግባር መከላከል አለበት ብለዋል።

በየአካባቢው የሚስተዋለውን ረጅም ሰልፍ እና ደቂቃ ለመቀነስም 377 የሚጠጉ ተጨማሪ አውቶብሶች እንዲሁም 20 መካከለኛ የመጫን አቅም ያላቸው በኤሌትሪክ የሚሠሩ አዳዲስ ሚኒ ባሶች አገልግሎት መስጠት መጀመራቸውን ይናገራሉ።

አቶ ዳዊት እንደሚሉት፤ በከተማዋ አሁን ላይ 50 በመቶ በላይ የሚሆነው የትራንስፖርት አገልግሎት በታክሲዎች የሚሸፍን ነው። በቀጣይ ይህንን ቁጥር ወደ ማስ የአውቶብስ ትራንስፖርት ከማሸጋገርም አኳያም ከዘመኑ ጋር የሚሄዱ አውቶብሶች እንዲገቡ ይደረጋል። በዚህም የግሉን ባለሀብት በማሳተፍ የተጣጣመ እና የተቀናጀ ትራንስፖርት ፍሰት ለመፍጠር ይሠራል።

# ውሃን በፍትሐዊነት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሀብታሙ ኢተፋ በተወካያቸው በኩል ባስተላለፉት መልዕክት፤ ውሃን በፍትሐዊነት መጠቀም ሠላምን ለማጽናትና ለመልሶ ግንባታ ወሳኝ ነው።

ኢኒጂነር ሀብታሙ በመልዕክታቸው ውሃ ለሠላምና ለጋራ ብልጽግና ያለው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን ተናግረዋል።

በተጨማሪም የቀኑ መከበር የውሃ ቀውስ ግንዛቤን ለማዳበር እንዲሁም የውሃና የአካባቢ ፅዳትን ለሁሉም ማረጋገጥ የሚለውን ዕቅድ ለማሳካትና ለመደገፍ በማለም መሆኑን አብራርተዋል።

የውሃ ሀብቶችን በፍትሐዊነትና በእኩልነት መጠቀም ያስፈልጋል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ሀገሪቷ በዘርፉ ከፍተኛ ሃብት ያላት መሆኑን አውስተዋል።

75 በመቶ የሚሆኑት ወንዞች ወደ ውጭ የሚፈሱ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ከዚህ አኳያ ኢትዮጵያ የውሃ ሃብትን በፍትሐዊነት መጠቀም እንዲቻል እየሠራች መሆኑን ተናግረዋል።

በሚኒስቴሩ የውሃ ዲፕሎማሲ ዴስክ ኃላፊ ወይዘሮ በልዩ ተኮላ በበኩላቸው፤ የውሃ ሃብትን በጋራ መጠቀም ሠላምና ደህንነትን ለማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑን አብራርተዋል።

ወይዘሮ በልዩ አክለውም፤ የውሃ ሀብቶች በእኩልነትና በፍትሐዊነት ለመጠቀም በውሃ ዲፕሎማሲው ረገድ በትኩረት መሥራት አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመዋል።

የውሃ ዲፕሎማሲው ውጤታማ ከማድረግ አኳያ የሴቶች ሚና ከፍተኛ መሆኑን የገለጹት ወይዘሮ በልዩ፤ የሀገሪቱ አብዛኞቹ ወንዞች ድንበር ተሻጋሪ በመሆናቸው የድርድር አቅም በማጎልበትና የውሃ ልማቱን እውን ለማድረግ በትብብር መሥራት እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል።

በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የሚኒስትሩ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ማሙሻ ኃይሉ በበኩላቸው፤ የዓለም የውሃ ቀን መጋቢት 13 በየዓመቱ የሚከበር መሆኑን ጠቅሰው ውሃ በሰው ልጅ የዕለት ተዕለት ተግባር ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል በመሆኑ ሁሉም በፍትሐዊነትና በእኩልነት መጠቀም እንደሚገባው ተናግረዋል።

እንደ አቶ ማሙሻ ገለጻ፤ ሀገሪቷ ያላትን የውሃ ሀብት አሟጦ ለመጠቀም የውሃ መረጃው ሊኖር ይገባል። በተጨማሪም መረጃዎችን በማጠናከር ግንዛቤ መፍጠር አስፈላጊ ነው።

ውሃ የጸብ መንስኤ ሊሆን አይገባም ያሉት አቶ ማሙሻ፤ የተቀናጀ የውሃ ሃብት አስተዳደር አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል።

ከበዓሉ ጎን ለጎን ውሃ ለሠላምና ለብልጽግና ያለው ፋይዳ፤ በውሃ ሃብት አጠቃቀም ዙሪያ የትብብር አስፈላጊነት እንዲሁም አብሮ መሥራት በሚቻልባቸው ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ መነሻ ሃሳቦች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል።

## ተናጋሪው ዶሴ

# ሕፃናትን ለማርከስ የተፈጠረ ዘማዊ

**አስመረት ብስራት**



ገና በአፍላው የወጣትነት ዘመኗ ነበር የተሳሳተ ግንኙነት ውስጥ የገባችው። በወጣት ልቧ አፈቀረኩሽ ያላትን ሰው ተከትላ ከቤተሰቦቿ ኮበለለች። የተወለደችበትን አካባቢ የተወችለት አጋሯ አንዴ እጁ ካስገባት በኋላ ያሰቃያት ጀመር። እሱ ቁጭ ብሎ እሷ ሰርታ እንድታኖረው ያደርጋል።

በልጅ አቅሟ የቻለችውን በሙሉ እየሠራች ቤታቸውን ለማሟላት ብትጥርም ያገኘችውን ገንዘብ እየተቀበለ በመጠጣት ጊዜውን ያሳልፍ ነበር። ሁሉን ትታ ወደ ቤተሰቧ እንዳትመለስ የወላጆቿን ፍቅር መግፏቷ እነሱን ማሳዘኗ እግሯን ወደ ቤተሰቦቿ ቤት እንዳታነሳ አድርጎ አሰራት።

በዚህ መካከል ነበር እያዞረ ሲጥላት ሕመሟን ለማወቅ ሐኪም ቤት የሄደችው። ሐኪም ቤት ሄዳ የሰማችውን ማመን ያቃታት ወጣት ለተወሰኑ ደቂቃዎች እራሷን ስታ ነበር። ከዛሬ ነገ ሳላስብ ከገባሁበት ትዳር ተገላግዬ ያቋረጥኩትን ትምህርቴን እቀጥላለሁ የምትለው ወጣት የሶስት ወር እርጉዝ መሆኗን ስትሰማ ሰማይ ምድሩ ነበር የዞረባት።

በልጅነት ህልሟ ተምራ ትልቅ ደረጃ መድረስ ቢሆንም በገዛ እጇ ያደናቀፈችውን የስኬት መንገዷን እያሰበች ስታማርር ለከፋ የጤና እክል ተዳረገች። መታመሟን የተመለከተው አቶ ባል ሰጥ ለጥ ብሎ ሚስቱን መንከባከብ ጀመረ። ትንሽ የተስፋ ጭላንጭል ያየችው ወጣት እራሷን እያፅናናች ለወራት በሰላም ኖረች።

ከዛ በኋላ የአንዲት ቆንጆ ሴት ልጅ እናት ሆነች። ልጅቷ እንደተወለደች አካባቢም ተፍ ተፍ ብዬ መጣሁ የሚለው ባል በርከት ያለ ገንዘብ ለቤተሰቡ ማምጣት ጀመረ። ኑሯቸው እየተቀየረ ቢሄድም በአጭር ጊዜ ይህን ሁሉ ገንዘብ የማምጣቱ ነገር አልዋጥልሽ ብሏት ነበር።

ብትጠይቀውም የረባ መልስ ስለማይሰጣት ሳትጠይቅ ለልጇ የሚያስፈልጋትን እያሟላች የተደላደለ የሚባል ሕይወት መምራት ጀመረች።

አንድ ጠዋት ግን የላሰበችው ነገር ተፈጠረ። አመሻሽቶ አንድ የሞላ ሻንጣ ይዞ መጣ፡፡ እንደመጣም ድካም በተጫጫነው ስሜት ተኛ። በጠዋት ተነስታም ለቤተሰቧ ቁርስ ለመሥራት ጓዳ ውስጥ እየተንጎዳጎደች ሳለ በሩ በኃይል ተንኳኳ። በድንጋጤ ተንደርድራ ስትከፍት የፀጥታ ኃይሎች ቤት በመግባት ባለቤቷን ከተኛበት አንጠለጠለው ይዘውት ሄዱ።

ህልም በሚመስል ፍጥነት ሁሉ ነገር ሲከናወን በድንጋጤ አፏን ከፍታ ነበር የተመለከተችው። ነፍሷ መለስ ሲል በድንጋጤ የምታለቅሰውን ልጇን አንስታ አባብላ ቁርስ ማብላት ጀመረች። ወዲያው ደግሞ ፖሊሶቹ ባሏን እያዳፉ ይዘውት በመምጣት በሻንጣ የሞላውን ነገር ይዘው ሄዱ። ያኔ ልጇን አዝላ ተከተለች። ከኋላ ከኋላ በሩጫ የተከተለቻቸው ፖሊሶቹ ሌባ እንደሆነ አረዷት። ለሁለት ዓመታተ ሳይጎልባት ያኖሯት ባሏ ሥራው ስርቆት እንደነበር ስታውቅ ሁሉ ነገር ነው የጨለመባት። ከዛ ያላትን በሙሉ ለቃቅማ ጭና አካባቢ ቀየረች። በአዲሱ ሰፈርም ልጇን አዝላ የተለያዩ ሥራዎችን በተመላላሽነት ትሰራ ጀመረ።

ልጇም አድጋ ትምህርት ቤት ገባች። እሷም ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትል ልጇን ለማሳደግ ያገኘችውን ሥራ በሙሉ ትሠራ ጀመረ። ልጇ አስራ አንድ ዓመት የሞላት የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ሆነች። እያደገች በመሆኑ የተከራየችበት ቤት አካባቢ ልጆች እንዳይተናኮሏት በሚል የምትሰራበት ቦታ በሙሉ ትምህርት በሌላት ሰዓት ይዛት ትሄዳለች።

እናት በተመላላሽ ሠራተኝነት የምትሠራ ቤት ሕፃኗን ይዛት የምትሄድ ከመሆኑም በተጨማሪ እናቷ በሌለችበትም ጊዜም ልጅት በግለሰቡ ቤት ትላላካለች። አንድ እለት ነው ሕፃኗ እናቷ በምትሰራበት ግለሰብ ቤት ውስጥ TV እያየች እንቅልፍ የወሰዳት።

ግለሰቡ ቤቱ ሲገባ ሕፃኗ በተቀመጠችበት እንቅልፍ ወስዷት ሲመለከት ወትሮም ሕፃናትና አቅመ ደካሞችን የማጥቃት ሱሰ የነበረው ሰው በክፉ ዓይኑ ተመለከታት።

### ሕፃኗ ስጦታ

የልጅነት ስጦታዎ ስለሆነች ስጦታ በሚል ስም የምትጠራው ሕፃን ሳቂታ የደስ ደስ ያላት ልጅ ነበረች። ከሁሉ ጋር ቶሎ የምትግባባ ለነገሮች ፈጣን ምላሽ የምትሰጥ ዓይነት ንቅት ያለች ልጅ ነበረች። በትምህርቷ ጎበዝ ስትሆን ስታድግ ሐኪም የመሆን ህልም እንዳላት ሁልጊዜ ስትናገር ትሰማለች።

የሕፃኗ እናት ልጇን ከአጠገቧ የምታርቃት ትምህርት ቤት ስታደርሳት ብቻ ነበር። በተመላላሽ ሠራተኝነት የምትሠራበት ቤት በሙሉ ሕፃኗን ይዛት የምትሄድ ከመሆኑም በተጨማሪ እናቷ በሌለችበትም ስትላላክ ትውል ነበር።

በእለቱም እቃ ለመግዛት ወጣ ስትል ልጇን ፀሐይ እንዳይመታባት የምትሰራለትን ግለሰብ ቤት ቲቪ ከፍታላት ወደ ገበያ ትሄዳለች። ልጅቷም ወደዚህ ወደዚያ ስትላለክ በመቆየቷ ቁጭ ባለችበት ነበር እንቅልፍ የጣላት።

እናቷን መርዳት የሚያስደስታት ሕፃን ስትላላክ ስለዋለች ደክሟት ነበር። ለወትሮው እርሳስና ጣፋጮች የሚሰጣት የእናቷ አሰሪ ከተኛችበት መሬት አንስቷት ወደ መኝታ ክፍሉ ሲያስገባት ያለ ምንም ስጋት ገልበጥ ብላ ነበር ወደ እንቅልፏ የተመለሰችው።

ይህ የዝሙት ልብ ያለው ሰው ግን ምንም ሳያመነታ እናቷ ተመልሳ ሳትመጣበት ልጅቷን ደፈራት። ሀገር ሰላም ብላ የተኛችው ሕፃን ሕመሙን መቋቋም አቅቷት በጩኸት ስታደበላለቀው ነበር እናቷ ወደ ቤት የተመለሰችው።

ልጇን ምን እንዳገኛት በድንጋጤ እየተወላከፈች ለመመልከት ስትሮጥ ሰውየው ጉዳዩን ፈፅሞ ወደ ደጅ ሲወጣ በር ላይ ተገጣጠሙ። ምንም ሳይናገር ወደ ውጭ የሚወጣውን ሰውን አልፋ የልጇን ድምፅ ወደ ሰማችበት መኝታ ቤት ስትመለከት ያየችውን ማመን ነበር የተሳናት።

የልጅነት ልጇን፤ በችግር ተጠብሳ ያሳደገቻት ልጇን፤ ነገ ደርሳ ሰው የደረሰበት ትደርስልኛለች የምትላት ልጇ በደም ተለወሳ በሲቃ እያነባች ተመለከተች። ሁለቴ ማሰብ ሳይጠበቀባት ነበር በአቅራቢያው ያሉ ፖሊሶችን ጠርታ የሆነውን ያሳየቸው። ፖሊሶቹም ልጅቱ በአፋጣኝ የሕክምና ርዳታ ወደ ምታገኝበት አድርሰው ደፋሪውን በቁጥጥር ስር ለማዋል እንቅስቃሴ ጀመሩ።

### ልማደኛው ደፋሪ

አላገባም፤ ሴት የማናገር ድፍረት ኖሮትም አያውቅም። የተማረ ጥሩ ሥራ ያለው ሰው ነው። አንገቱን የደፋ ሰው ቀና ብሎ የማያይ ጨዋ ሰው ነው ይሉታል የሚያውቁት ሁሉ። ነገር ግን ሕፃናት ሴቶችን ነበር በተለየ ሁኔታ የሚቀርበው። ልጆችን ማቀፍ መንከባከብ በሚመስል መልኩ መያዝ ያዘወትራል።

ከዚህ ቀደም አንዲት የ12 ዓመት ሕፃን ልጅ ላይ ባልተገባ ሁኔታ ንከኪ ሲያደርግ የተመለከቱትን ሰዎች ለመሸሽ ነበር ሰፈር የቀየረው። ቀደም ሲልም አንዲት ሕፃን ደፍሮ ማንም ሳያውቅ እንደቀረ ያስታውሳል። ሌሎች ያልተነገሩ በልቡ የያዛቸው ድፍረቶችም አሉት።

ጨዋ መሳዩ ሰው አድብቶ እኩይ ሥራውን ሲሰራ ማንም አይጠረጥረውም ነበር። የልጅቷ እናትም ከሌሎቹ አሰሪዎች በተለየ እሱን ታምነው ነበር። እምነቱን እስካጎደለባት ነሐሴ 12 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ። እሷ አስቸጋሪ ነገር ሲገጥማት ሁሉ እሱ ጋር ልጅቷን ማስቀመጥ ታዘወትር ነበር። እንዲህ አስብቶ አራጅ ከመሆኑ በፊት።

ልዩ ቦታው በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ደመካ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የሚገኝ የግለሰቡ መኖሪያ ቤት ውስጥ ነበር። በግምት ከቀኑ 8፡30 ሲሆን ቲቪ እያየች እንቅልፍ የወሰዳትን ልጅ አስገደዶ ነው የደፈረው። በ1996 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 627/1/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ እድሜዋ 11 ዓመት ከ8 ወር የሆነችን ሕፃን አስገድዶ በመድፈር ወንጀል የፈፀመው ይህ እኩይ ሰው ቤቱ አካባቢ ጭር ያለ ሲመስለው ነበር ቤቱ የገባው።

የሠራውን ሰርቶ አረሳስቶ የመጣውን ሰው ተደብቀው ሲጠበቁ የቆዩት ፖሊሶች በቁጥጥር ስር አውለውታል።

### የፖሊስ ምርመራ

ፖሊስ ተጎጂዋን ሐኪም ቤት ካደረሰ በኋላ ነበር ጊዜ ሳያጠፉ ተጠርጣሪውን በቁጥጥር ስር ለማዋል የተንቀሳቀሰው። በቡድን ተደራጅተው ፍለጋ የጀመሩት የፖሊስ አካላት ግማሽ ቀን ሲፈልጉት ቢውሉም ሊያገኙት አልቻሉም ነበር።

አመሻሽ ላይ የተወሰነ ኃይል ቤቱ አካባቢ አድፍጦ እንዲጠበቅ መድበው ሲጠባበቁ ቆዩ። ሁሉም ነገር ተረስቶልኛል ያለው ተከሳሽም ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ተኩል አካባቢ ሹልክ ብሎ ወደ ቤቱ ሲገባ በቁጥጥር ስር ይውላል።

ፖሊስ የዓይን እማኞችን የሕክምና ማስረጃንም አክሎ ተከሳሽ ዮሴፍ ሙህዬ የተባለው ግለሰብ ነሐሴ 12 ቀን 2014 ዓ.ም በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ደመካ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በግምት ከቀኑ 8፡30 ሲሆን በ1996 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 627/1/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ እድሜዋ 11 ዓመት ከ8 ወር የሆነችን ሕፃን አስገድዶ በመድፈር ወንጀል ክሰ አቅርቦበታል።

### የዓቃቤ ሕግ ክስ ዝርዝር

ዓቃቤ ሕግም ፖሊስ አጠናቀሮ የላከለትን ማስረጃ በመያዝ ተጠርጣሪው ላይ ክስ መስርቶበታል። የክስ ዝርዝሩ እንደሚያስረዳው የሕፃኗ እናት በተከሳሽ ቤት በተመላላሽ ሠራተኝነት የምትሰራ ሲሆን ሕፃኗን ይዛት የምትሄድ ከመሆኑም በተጨማሪ እናቷ በሌለችበትም ጊዜም በግለሰቡ ቤት ትላላካለች። በእለቱም በተከሳሽ ቤት ውስጥ TV እያየች በተኛችበት በግምት ከቀኑ 8፡30 ሰዓት አካባቢ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈጸመባት እና ክብረ ንጽህናዋ እንዲገረሰስ ያደረገ በመሆኑ ዓቃቤ ሕግ በ1996 የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 627/1/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ሕፃናት ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ-ሥጋ ድፍረት በደል ወንጀል ክስ መስርቶበታል፡፡

### ውሳኔ

በቀረበው ክስ መሠረትም ተከሳሽም ፍ/ቤት ቀርቦ ዓቃቤ ሕግ የተከሳሽን ጥፋተኛነት ያስረዳሉ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች በማቅረብ የተከራከረ ሲሆን ተከሳሽ እንዲከራከር ብይን ቢሰጠውም ጥፋቱን ማስተባበል ባለመቻሉ ፍርድ ቤቱም ጥፋተኛ ብሎታል፡፡

በመጨረሻም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ 7ኛ ወንጀል ችሎት የቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያ ሁኔታዎችን በማየት ተከሳሹ በአስራ አራት ዓመት ከአራት ወር በሚደርስ ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ሲል ወስኖበታል፡፡

# ስኬት

## ለቀጣዩ የግብርናው ዘርፍ ስኬት መንደርደሪያ ሽልማት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

የኢትዮጵያ መንግሥት ግብርና ለሀገሪቱ ምጣኔ ሀብት መሠረት መሆኑን በሚገባ በመገንዘብ በወሰዳቸው አያሌ ርምጃዎች የዘርፍን ምርትና ምርታማነት ማሳደግ እየተቻለ ነው። በዘርፉ የሚለማው መሬት እንዲሁም የሚገኘው በየዓመቱ እየጨመረ እንዲመጣ ማድረግ ተችሏል።

በግብርናው ዘርፍ ካለው እምቅ አቅም፣ ሀገር ከዘርፉ ከምትጠብቀው ሀብት አኳያ ሲታይ ግን ይህ ምርትና ምርታማነት ማደግ እንደሚጠበቅበትና ለእዚህም በግብርናው ዘርፍ ላይ በትኩረት መሥራት እንደሚገባ መንግሥት በተደጋጋሚ ሲያስገነዝብ ቆይቷል።

ይህን ተከትሎም ግብርናውን ከተለመደው አሠራር በማውጣት በዓመት አንዴ በዝናብ ላይ ብቻ ጥገኛ ሆኖ ሲመረትበት ከነበረው ሁኔታ በማውጣት በመስኖ ማልማት ውስጥ ተግብቷል። በመስኖ ማልማት ውስጥ መግባትና የሀገሪቱን የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ብቻም ሳይሆን በመስኖ ስንዴ ልማት ከሀገርም አልፎ ተጠቃሽ ስንዴ አምራች መሆን ተችሏል።

ይህ እውን ሊሆን የቻለው ደግሞ መንግሥት ዘርፉን ለማዘመን፣ የመስኖ ልማትን ለማስፋፋት፣ እንደ ማዳበሪያ ላሉት ግብቶች በየዓመቱ በቢሊዮኖች ብር ድጎማ በማድረግ፣ ለሜካናይዜሽን ትኩረት በመስጠት፣ ለሜካናይዜሽን እርሻ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥረውን የኩታ ገጠም እርሻ ማስፋፋትና በመሳሰሉት ላይ በወሰዳቸው ርምጃዎች ነው። በዚህም ሀገሪቱ በዝናብ ጥገኝነት ብቻ ታምርት ከነበረበት ሁኔታ እየወጣች ትገኛለች። በበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱ እየታየ ያለው ለውጥ ለእዚህ ጉልህ ማሳያ ነው።

የመስኖ ልማቱ የሀገሪቱን ታሪክ መቀየር ጀምሯል። ኢትዮጵያ ውስጥ ለዘመናት መደበኛውን የዝናብ ወቅት ብቻ ጠብቆ ሲሰራ የነበረው የግብርና ሥራ በመስኖ ልማትና በሜካናይዜሽን መታገዝ ጀምሯል። ምርትና ምርታማነቱ በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል፤ ሀገሪቷ በምግብ ራሷን ለመቻል የምታደርገውን ጥረት በማገዝ ምርትና ምርታማነቱን ከእጅ ወደ አፍ ታሪኩ ለማውጣት የበኩሉን ሚና እየተጫወተ ነው። በድርቅና በመሳሰሉት ወቅቶች የርዳታ ስንዴ ፍለጋ ወደ ውጭ ከማማተር ወጥታለች።

ሀገሪቱ ከራሷ አልፋ ለሌሎች መትረፍ የምትችልበትን መንገድ ጠርጋ መጓዝ ጀምራለች። ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ በመመደብ ስንዴ ከውጭ ማስገባቱ ቀርቷል፤ በምትኩ ስንዴ ለውጭ ገበያ ማቅረብ ተጀምሯል።

ይህን ልማት የሚመራው የግብርና ሚኒስቴርም በተለይ በበጋ ስንዴ መስኖ ልማት ባከናወነው ስኬታማ ተግባር በቅርቡ በተከናወነ የስኬት ሽልማት መርሃ ግብር ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሽልማት ተበርክቶለታል። ሚኒስቴሩን ጨምሮ አምስት የኢትዮጵያ ተቋማት የስኬት ሽልማት ከኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በተቀበሉበት ወቅት የሀገሪቱ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ስኬቶች ተዘርዝረዋል። እኛም በዛሬው የስኬት ዓምዳችን የሚኒስቴሩን የስንዴ ልማት ስኬት እንዳስሳለን።

የምግብ ዋስትና ማረጋገጫና የሀገር የኢኮኖሚ መሠረት የሆነው የኢትዮጵያ የግብርና ዘርፍ እያስመዘገበ ያለውን አበረታች ውጤት ሲነሳ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በቀዳሚነት የሚመጣው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ነው። ይህ የግብርናውን ዘርፍ ከስኬታማ ተቋማት መካከል ያቆመው አርአያነት ያለው ታላቅ ተግባር ሀገሪቱ በስንዴ ልማት እውን ሊሆን የቻለው በመንግሥት ቁርጠኛነት ነው።

መንግሥት የበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱን ከጀመረ ወደ አምስት ዓመታት ተቆጥረዋል። ወደዚህ ሀገራዊ ልማት ሲገባም ስትራቴጂክ ዕቅድ ነድፎ ነው። የፌዴራልና የክልል አመራሮች እንዲሁም የዘርፉ ባለሙያዎች በዚህ ሀገራዊ ጉዳይ የጋራ ዕቅድ አውጥተው መክረው ፤ ዘክረው ነው ልማቱ ወደ መሬት ያወረዱት።

ዕቅዱም በቅድሚያ በቆላማ አካባቢዎች የቆላ መስኖ ስንዴ ልማት በሚል ተጀመረ። ይህ ልማት በቀጣዩቹ ዓመታት ቆላ፣ ደጋ ፣ ወይና ደጋ ሳይል በሁሉም ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ተተግብሮ አበረታች ውጤት እያስመዘገበ ይገኛል። በአሁኑ ወቅትም ልማቱ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ተጠናክሮ ቀጥሏል። ሀገሪቱም በዓመት አንዴ እልፍ ቢል ሁለቴ ታምርት ከነበረበት




ሶስቴ ወደ ማምረት ተሸጋግራለች።

የበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱ ሀገሪቱ ስንዴ ከውጭ ሀገር የምታስመጣበትን ሁኔታ አስቀርቷል፤ ለእዚህ ይውል የነበረውን የውጭ ምንዛሬም አድኗል። በመንግሥት ቁርጠኝነት የተጀመረው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ውጤታማነቱ በየዓመቱ እየጨመረ መጥቷል።

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፤ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት በቆላማው የሀገሪቱ ክፍል አሀዱ ተብሎ በተጀመረበት ዓመት 100 ሺ ኩንታል ስንዴ ነበር የተገኘው፤ በ2016 ዓ.ም ደግሞ 120 ሚሊየን ኩንታል ለማግኘት ታቅዶ እየተሠራ ነው።

የስንዴ ፍላጎትን በሀገር ውስጥ ምርት ለመሸፈን በተደረገው ብርቱ ጥረት የተመዘገበው ውጤት የግብርናውን ዘርፍ ስኬታማ አድርጎታል። ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ በይቻላል መንፈስ ስንዴን በመስኖ አልምታ ሕዝቡን ልታጠግብ ከራሷ አልፋም ለሌሎች ልትተርፍ የጀመረችው ጉዞ አበረታች ውጤት አስመዝግቧል። ሀገሪቱ ባለፈው ዓመት የራሷን የስንዴ ፍጆታ ከመሸፈን አልፋ ለጎረቤት ሀገሮች ስንዴ መላክ ጀምራለች።

ባለፉት አራት ተከታታይ ዓመታት እንዲሁም ዘንድሮ እየተካሄደ ባለው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ለተገኘው አመርቂ ውጤት የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከፍተኛ የአመራር ቁርጠኝነት፣ የመንግሥት የተቀናጀ የፋይናንስ ድጋፍና ሀገራዊ የስንዴ የመስኖ ፕሮጀክት አስተባባሪ ጽሕፈት ቤት ተቋቁሞ ወደ ሥራ መግባቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከታቸው በተለያዩ ወገኖች ይጠቀሳል።

እነዚህና መሰል ጥረቶችንና የተመዘገበውን ስኬት የተረዱ ኢትዮጵያውያን፣ ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ተቋማት ልማቱ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀዳሚ ስንዴ አምራች ሀገር መሆን እንድትችል እያደረጋት ስለመሆኑ ምስክርነት ሲሰጡ ይደመጣል።

በአንድ ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትሩ "እንኳን ለራሳችን ለሌሎች የሚተርፍ ስንዴ ማልማት እንችላለን፤ ለዚህም መንገዱን ጀምረነዋል» ሲሉ እንደተናገሩትም ሀገሪቱ በበጋ መስኖ አምርታ ብቻ በብዙ ሚሊዮኖች ኩንታል የሚቆጠር ስንዴ ማምረት ችላለች። ከምርቱም ከሀገራዊ ፍጆታ የተረፈውን ለጎረቤት ሀገሮች መላክም ተችሏል። በየዓመቱ እየጨመረ የመጣው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማትና ምርትም ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉትም ሀገሪቱን ስንዴ ለውጭ ገበያ እስከ ማቅረብ አድርሷታል።

የበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱ የዓለም አቀፍና አህጉራዊ ተቋማት፣ በሀገሮችም አድንቆትን ማትረፍ ችሏል። የአፍሪካ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንት አኪንዉሚ አዴሲና በተደጋጋሚ አድንቀውታል፤ ሀገሪቱ በስንዴ ምርት ራሷን መቻሏን ጠቅሰው፣ በልማቱ የተገኘው ስኬት አፍሪካንም የሚያኮራ መሆኑን አስታውቀዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በጣልያን ሮም ከዓለም ምግብ ድርጅት /ፋኦ/ የተቀበሉት ሽልማትም በግብርናው ዘርፍ የተከናወኑ ተግባሮች ምን ያህል ውጤታማ እንደሆኑ ያመለክታል። አንዳንድ የአፍሪካ ሀገሮች ከፍተኛ ባለስልጣናትም ይህን የኢትዮጵያን የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ጎብኝተው አድናቆታቸውን ሰጥተዋል፤ ተሞክሮም ወስደዋል።

አሀዛዊ መረጃዎችም የስንዴ ልማቱ በመኸር ወቅትና በበጋ መስኖ ልማቱ ምርታማነቱ እየጨመረ መምጣቱን ያሳያሉ። በ2011 ዓ.ም በመኸር ወቅት በስንዴ ዘር የተሸፈነው መሬት አንድ ነጥብ ሰባት አምስት ሚሊዮን ሄክታር ሲሆን፤ ከዚህም 48 ሚሊዮን ኩንታል የስንዴ ምርት ነበር የተገኘው።

በዘንድሮ 2015/16 የምርት ዘመን የመኸር ወቅት በዘር የተሸፈነው መሬት ሶስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር ደርሷል። ከዚህም 134 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል።

በ2011 ዓ.ም በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት 100 ሺ ኩንታል የስንዴ ምርት የተገኘ ሲሆን፣ በ2016 ዓ.ም ደግሞ በዚሁ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት 120 ሚሊዮን ኩንታል የስንዴ ምርት ለማግኘት ታቅዶ እየተሠራ ነው።

በሌላ መረጃ በ2014 በጀት ዓመት በሀገር ደረጃ 60 ሚሊዮን ኩንታል አካባቢ የስንዴ ምርት ማግኘት የተቻለ ሲሆን፤ በ2015 ዓ.ም በሀገር አቀፍ ደረጃ በበጋ መስኖ ከለማው አንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት እንዲሁም ከመኸር የስንዴ ማሳ 153 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለማግኘት ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል።

የግብርና ሚኒስትር ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) በአንድ ወቅት ለመገናኛ ብዙሃን በሰጡት መግለጫ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱ በ2011 ዓ.ም በሶስት ሺ አምስት መቶ ሄክታር መሬት ላይ ማልማት መጀመሩን አስታውሰው፣ በተያዘው 2016 የምርት ዘመን የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ይህ አሀዝ ሶስት ሚሊዮን ሄክታር መድረሱን አስታውቀዋል።

በልማቱም ከፍተኛ ልምድ እንደተገኘበት ጠቅሰው፣ ይህንኑ ልምድ ማዳበርና ማካፈል በመቻሉ በቅርቡ የዓለም ምግብና እርሻ ድርጅት ለኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ዕውቅና ሰጥቷል ሲሉ ገልጸዋል። የዓለም ምግብና እርሻ ድርጅት የሰጠው ዕውቅናም በግብርና ሥራ ውስጥ የተሳተፉ አርሶና አርብቶ አደሮችን ጨምሮ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ የተሰጠ ዕውቅና መሆኑን ነው ያስታወቁት። ከዚህም ባለፈ ኢትዮጵያ የረሃብ ምሳሌ ከመሆን ወጥታ አሁን በትክክለኛው የልማት መንገድ እየተጓዘች መሆኗን እንደሚያሳይም ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ፕሮግራም ባስመዘገበችው ውጤት ከአፍሪካ ቀዳሚዋ ስንዴ አምራች ሀገር ሆናለች። በልማቱ የተገኘው ስኬትም የግብርና ሚኒስቴር ዕውቅና ተቸሮታል።

በቅርቡ የኢትዮጵያ ተቋማት የስኬት ሽልማትን በዓድዋ መታሰቢያ ሙዚየም በተካሄደበት ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፤ ለግብርና ሚኒስቴር፣ ለኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት፣ ለኢትዮጵያ አየር መንገድ እና ለኢትዮ ቴሌኮም የስኬት ሽልማት አበርክተዋል። በስኬት ስማቸው የተጠሩ ተቋማት በሰሩት ሥራ ለምስጋና የበቁት በዋናነት በሀገር ደረጃ ባላቸው ስኬት እንዳልሆነም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጠቅሰው፣ በአህጉር ደረጃ ባላቸው የመወዳደር አቅምና ባስገኙት ውጤት መሆኑንም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገልጸዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ «ስኬት አዳጊ ነው፤ ስኬት አላቂ አይደለም። ስኬት ከአንደኛው ማይልስቶን ወደሚቀጥለው ማይልስቶን በአዳዲስ ትልምና ዕቅድ በአዳዲስ ፍላጎት በየጊዜው የሚያድግ እንጂ የሚቆም አይደለም» ሲሉ አስገንዝበዋል። «ማይልስቶን የሚለው ሃሳብ የመጣው በየመንገዱ ከጅምሩ እስከ ፍጻሜው ስንጓዝ የደረስንበትን ኪሎ ሜትር የሚያሳዩ ድንጋዮችን ታሳቢ በማድረግ ነው። » ሲሉ ገልጸዋል። የተሸለሙት ተቋማትም ከጅምሩ አሁን በደረሱበት ማይልስቶን ያሳኩትን ነገር ዕውቅና ለመስጠት እንጂ ጨርሰዋል ለማለት አይደለም ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት፤ የኢትዮጵያን ግብርና በሚመለከት የዛሬ ሶስትና አራት ዓመታት ኢትዮጵያ ስንዴ ከውጭ ታስገባ ነበር። ኢትዮጵያ በአፍሪካ ውስጥ ከፍተኛ ስንዴ ከሚያመርቱ ሀገራት በዝቅተኛ ደረጃ የምትታይም ነበረች።

«ዛሬ በአፍሪካ አንደኛ ስንዴ አምራች ብቻ ሳንሆን በአፍሪካ ሁለተኛ ስንዴ አምራቾችን በእጥፍ ደረጃ እንበልጣለን። ይህ ትልቅ ድል ነው፤ ነገር ግን ማይልስቶን ነው።» ሲሉ አስታውቀው፣ «ጨረስን ሳይሆን ጉዞ ጀምረን የተወሰነ ኪሎ ሜትር ወደኋላ አስቀርተን ከፊታችን ምን ያህል እንደሚቀረን ለማወቅ ዕድል ሰጠን ማለት ነው» ብለዋል።

ሀገሪቱ ግብርናው ዘርፍ በሩዝ፣ ግብርና በሻይ፣ ግብርና በቡና ከሁሉም በላይ ግብርና በሌማት ትሩፋት በዶሮ፣ በእንቁላል፣ በሥጋ በወተት ከአፍሪካ አንደኛ አምራች የሚለውን ስያሜ እስከምንይዝ ድረስ ይሄኛው ማይልስቶን ለሚቀጥለው ማይልስቶን መሸጋገሪያ እንጂ የመጨረሻው ማለት እንዳልሆነም አስታውቀዋል።

ከሁሉም በላይ ግብርናን ስንሸልም የኢትዮጵያ አርሶ አደሮችን እየሸለምንና ዕውቅና እየሰጠን እንደሆነና ልፋትና ውጤታቸውን የማንዘነጋ መሆናችንን እያመላከትን ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የግብርና ሚኒስትሩ የወሰዱት ሽልማት የመላው የኢትጵያውያን አርሶ አደሮች የመጀመሪያው ማይልስቶን መዳረሻና ዕውቅና መስጫ መሆኑ ሊታሰብ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

በሚቀጥሉት ሁለትና ሶስት ዓመታት በተለያዩ የግብርና ዘርፎች የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች በሙሉ አዳዲስ ድሎችን በማስመዝገብ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ያላትን ደረጃ ከፍ እንደሚያደርጉ ያላቸውን ሙሉ እምነትም አስታውቀዋል።

መረጃዎች እንደሚያመላክተት፤ ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም በርዳታ የምትቀበለውን ስንዴ ጨምሮ በየዓመቱ ከ15 እስከ 20 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ከውጭ ስታስገባ ኖራለች። ለዚህ የስንዴ ግዢም በየዓመቱ ከ600 ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጪ ታወጣም ነበር።

ይሁንና ኢትዮጵያ ከውጭ የምታስገባውን ስንዴ በሀገር ውስጥ ምርት ሙሉ በሙሉ ከመተካት ባለፈ ስንዴን ወደ ውጭ ገበያ ለማቅረብ ችላለች። በተለይም የኩታ ገጠም የግብርና ሥራና የበጋ መስኖ ልማት ሥራዎቿን በማቀላጠፍ የጥረቷን ፍሬ ከራሷ አልፋ ለዓለም ማሳየት ችላለች። የዓለም ምግብ ድርጅት ሽልማት፣ የአፍሪካ ልማት ባንክ የስንዴ ልማቱ አድናቆት ከዚሁ የመነጩ ናቸው ማለት ይቻላል።

# የስንፍና መድኃኒት!

**አስናቀ ፀጋዬ**

በሕይወታችን ውስጥ ‹‹እኔ እኮ ሰነፍ ነኝ! ምንም አልችልም! በቃ እኔ እኮ የተፈጠርኩት ለስንፍና ነው! አልረባም!›› ልንል እንችላለን። ግን ክፍተታችን በጣም ቀላልና ትንሽ ብቻ መድኃኒት የሚያስፈልጋት ልትሆን ትችላለች። ስለዚህ ከታች ከተዘረዘሩት ስድስት ነጥቦች ውስጥ አንዱ የእኛ ክፍተት ሊሆን ይችላል። ልክ እርሱን ስናስተካክል ‹‹ለካ ሰነፍ አልነበርኩም፤ መጀመሪያውኑ አቅም አለኝ›› እንድንል ያደርገናል።

በርግጠኝነት ከነዚህ ስድስት ነጥቦች መካከል አንዱ ክፍተታችን ሊሆን ይችላል። እርሱን ስታስተካክሉ ስንፍናችሁ ይጠፋል። በትምህርት፣ በሥራ ወዘተ ሊሆን ይችላል ስንፍናችሁ! ‹‹እኔ ሰነፍ ነኝ!›› ብላችሁ የምታምኑ ከሆነ ከዛሬ ጀምሮ እንዳልሆናችሁ ታረጋግጣላችሁ። እነሆ ስድስቱ ነጥቦች...

**1ኛ. ኃላፊነት እንውሰድ**

አንዳንድ ጊዜ እድሌ እኮ ነው! እኔ የሚያስጠናኝ ሰው የለም እንጂ ሰነፍ ለመሆን ተፈጥሬ አይደለም! ማን ይርዳኝ እኔን! ቤተሰቦቼ ጥሩ አቅም የላቸውም! አያስተምሩኝም! ጥሩ ትምህርት ቤት አላኩኝም! ደሞም ገንዘብ የላቸውም! የሆነች ነገር እኮ ቢያስጀምሩኝ ጥሩ ቦታ እደርሳለሁ›› እንላለን። የብዙዎቻችን ምክንያት ነው። እኔ በቤተሰቤ ምክንያት ነው፣ በተወለድኩበት ሀገር ነው፣ በምሠራው ሥራ ነው፣ በምውላቸው ሰዎች ነው፣ በተፈጥሮዬ ነው እያልን ሰበብ እንደረድራለን።

ከዛሬ ጀምሮ ግን ኃላፊነት መውሰድ አለብን። ለምን መሰላችሁ? ስንፍና በሆነ ነገር ይደበቃል። ኃላፊነት የማንወስድ ከሆነ ለስንፍናችን ጥሩ ምክንያት አለን። ‹‹እኔ እኮ ጥሩ ነገር ላይ እደርስ ነበር፤ ቤተሰቦቼ እንዲህ ስለሆኑ ነው፣ የሚያስጠናኝ የሚያስረዳኝ ሰው ስለሌለ ነው፣ መጽሐፍ የሚያውሰኝ የለም፣ መጽሐፍ የሚገዛልኝ የለም›› እያልን ምክንያት ልንደረድር እንችላለን። ግን ኃላፊነት ብንወስድስ? በራሴ ምክንያት ነው የሰነፍኩት፣ ስለማልጥር ነው፣ ሥራዬ ላይ ጥሩ ስላልሆንኩ ነው፣ ማንበብ ስለማልወድ ነው፣ ኃላፊነቱ ራሴ እወስዳለሁ ስንል በህይወታችን በርካታ ነገር ይቀየራል።

ምክንያት ማብዛትም ቀላል ነው። ሰውዬው ቁልፍ ይጠፋበታል። ምሽት ነው። እየፈለገ ነው። ኧረ ! ዛሬ የት ነው የማገኘው እያለ እየተተራመሰ ነው። በመንገድ የሚያልፉ ሰዎች ደግሞ አያግዙትም። የሚፈልገው ብርሃን ላይ ነው። እንዴት ቁልፉ እንደጠፋበት አያውቅም ይሁን ብቻ ይፈልጋል። አንድ ጠጋ ብሎ ‹‹ምን አጥተህ ነው?›› አለው። ቁልፍ ጠፋብኝ አለ። እሺ ላፋልግህ ብሎ ማፋለግ ጀመረ። ደቂቃዎች ነጎዱ። ‹‹ይሄ ነገር እዚህ እንደጠፋብህ ርግጠኛ ነህ›› አለው ሰውዬው።

‹‹አይ እሱማ የጠፋብኝ እዛ ጨለማ ጋር ነው፤ ነገር ግን ለመፈለግ የሚመቸው እዚህ ብርሃኑ ጋር ነው›› አለው። አያችሁ! በሕይወታችሁ ውስጥ አንዳንድ ጊዜ ምክንያት ለመፍጠር በጣም ቀላል ነው። ያጠፋነው እኛ ሆነን ጨለማው እኛ ውስጥ ሆኖ ብርሃኑ ግን ቀላል የሆነውን መንገድ ለምክንያት እንጠቀማለን። በቤተሰቤ ነው፣ ትምህርቴ ነው፣ ጓደኛ የለኝም፣ የሚያስረዳኝ ሰው የለም እንላለን። ስለዚህ ምክንያቶች ብቻ ስንፍናችንን ወስደውብናል። ከዛሬ ጀምሮ ኃላፊነት መውሰድ እንጀምራለን።

**2ኛ. የምንመኘውን ማወቅ አለብን**

አንዳንድ ጊዜ ‹‹እኔ እኮ ያው ኑሮ እየከበደ መጣ እንጂ አቅሙ ነበረኝ፤ አሁን ግን ኑሮ ተወደደ›› እንላለን። ነገሮች ቀላልና አልጋ በአልጋ እንዲሆኑ መመኘት የለብንም። እኛ ነን መክበድ ያለብን። ኑሮ እንዲቀል የምንፈልግ ከሆነ መቼም አይቀልም። በሃምሳ ዓመት ልምድ ውስጥ ኑሮ እየተወደደ እንጂ እየረከሰ አልመጣም። ከንጉሡም ዘመን፤ ከደርግም፤ ከኢህአዴግም ጀምሮ እያንዳንዱ ነገር እየጨመረና እየተወደደ መጣ እንጂ አንድም የቀነሰ ነገር የለም።

ስለዚህ ማሰብ ያለብን የእኛን የመግዛት ወይም የገንዘብ አቅማችንን ማሳደግ ነው እንጂ ነገሮች ለምን አይረክሱም፤ ለምን ኑሮ ተወደደ ብለን ምክንያት ማብዛት የለብንም። ከዚህ አንፃር የምንመኘውን ነገር ማወቅ አለብን። በትምህርትም እያደግን ስንመጣ እየከበደ እንጂ እየቀለለ አይመጣም። ‹‹እኔ እኮ በልጅነቴ ጎበዝ ነበርኩ አሁን ነው የሰነፍኩት›› የምንል ከሆነ ራሳችንን እያታለልን ነው።

ስለዚህ ትምህርቱ እስከ ከበደ ድረስ እኛም ትምህርቱን ልናከብደው ይገባል። ለትምህርቱ የሚመጥን አቅም ማዘጋጀት አለብን። ከትምህርቱ ጋር አብረን ማደግ አለብን። ምኞታችንም አብሮ ማደግ አለበት። ኑሮ ሲወደድ እኔ ገቢዬን እጨምራለሁ እንጂ ኑሮ መወደዱ ሊያበሳጨኝ አይገባም ማለት አለብን።



‹‹ ስንፍና በሆነ ነገር ይደበቃል። ኃላፊነት የማንወስድ ከሆነ ለስንፍናችን ጥሩ ምክንያት አለን። ‹‹እኔ እኮ ጥሩ ነገር ላይ እደርስ ነበር፤ ቤተሰቦቼ እንዲህ ስለሆኑ ነው፣ የሚያስጠናኝ የሚያስረዳኝ ሰው ስለሌለ ነው፣ መጽሐፍ የሚያውሰኝ የለም፣ መጽሐፍ የሚገዛልኝ የለም›› እያልን ምክንያት ልንደረድር እንችላለን። ››

**3ኛ. ራሳችንን ስላሳወቅን ነው**

አይታችሁ ከሆነ አንዳንዴ ለራሳችን የምንሰጠው ቦታ ወይም ደግሞ ራሳችን እየሠራነው ያለውን ነገር ካላወቅን ሰነፍ እንደሆንን ልናምን እንችላለን። ስለዚህ መፍትሔው ራስን ማወቅ ነው። ዶክተር ኤለን ላገር የተሰኙት ተመራማሪ ባጠናችው ጥናት በሆቴል ውስጥ 84 ሠራተኞች አሉ። እነዚህ ሠራተኞች አልጋ አንጣፊዎች ናቸው። አንዷ ሠራተኛ በቀን 15 አልጋ ታነጥፋለች። ወይም አስራ አምስት ክፍሎችን ታፀዳለች። እነዚህ 84 ሠራተኞች ተጠየቁ..

‹‹ስፖርት ትሠራላችሁ ወይ? ተባሉ። ሃያዎቹ ‹‹አይ! በፍፁም ሠርተን አናውቅም›› አሉ። የተቀሩት ደግሞ ‹‹ብዙ ጊዜ አንሠራም አንዳንዴ ሲመቸን እንሠራለን›› አሉ። አጥኚዎቹ ምን ብለው መለሱ..‹‹ የሥራ መደቡ መስፈርት እኮ የእናንተን ሥራ ያሟላል። የምትሠሩት ሥራ በሙሉ ቅልጥ ያለ ስፖርት ነው›› አሏቸው። ሠራተኞቹ በጣም ተገረሙ። እነዚህ አጥኚዎች ከወር በኋላ ሲመለሱ አብዛኛዎቹ ሠራተኞች ሁለትና ከዚያ በላይ ኪሎ ግራም ቀንሰዋል። የሚገርም የሰውነት አቋም ይዘዋል።

ከዚያ አጥኚዎቹ ጠየቋቸው ‹‹እንዴት ነው ስፖርት ጀመራችሁ ወይ? የዛሬ ወር መጥተን ካናገርናችሁ በኋላ ስፖርት ጀመራችሁ እንዴ›› ሲሏቸው ኧረ! አልጀመርንም ግን ምንሠራው ሥራ ስፖርት እንደሆነ ስናውቅ ይኸው ይሄ ነገር ተፈጠረ አሉ። አያችሁ! አንዳንድ ጊዜ በሕይወታችን ገቢያችን ጥሩ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ምን ያህል እያስገባን እንደሆነ ካላወቅን ወጪ ላይ ብዙ እያፈሰስን ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ገቢያችንን ስናውቅ ‹‹አሃ! እኔ እኮ ጥሩ ገቢ አለኝ፤ የጨረሰብኝ እኮ እንዲህ ማውጣቴ ነው፣ እንዲህ ማድረጌ ነው ስንል ያለንበትን እናውቃለን። ‹‹እኔ ሰነፍ ስለሆንኩ አይደለም፤ የሆነች ትንሽ ክፍተት ናት፣ ራሴን ስላላወኩ ነው›› ስንል ሕይወታችን መስተካከል ይጀምራል። ስለዚህ ሰነፍ ስለሆንን አይደለም ራሳችንን ስላላወቅን ነው።

**4ኛ. ሥነ ምግባር ማዳበር**

ሥነ ምግባር(ዲስፕሊን) ከሌለን አቅም ቢኖረንም ጥረታችን ሁሉ ያለ ዲስፕሊን ከሆኑ ይበላሻል። ወጥ አይሆኑም። እንደውም ኬንያዊው የማራቶን ሯጭ ኢሉድ ኪፓቾጌ ‹‹ዲስፕሊን ያለው ሰው በጣም ነፃነት አለው። ምክንያቱም ማድረግ ያለበትን ካደረገ በኋላ አይምሮው ነፃ ይሆናል። ግን ዲስፕሊን የሌለው ሰው የስሜቱ ባሪያ ነው። አሁን እኮ ባታጠናስ፣ ባትሰራስ ስለሚለው ያንን ያደርጋል። ተዝናና ሲለው ስሜቱን ይከተልና ይዝናናል። ስለዚህ ስሜቱ ባሪያው አድርጎታል። ዲስፕሊን ያለው ሰው ግን ነፃነት አለው›› ይለናል። ስለዚህ ዲስፕሊን እንዲኖረን ማድረግ ያለብኝን ሳልጨርስ አልዝናናም። ሶሻል ሚዲያ አልጠቀምም፣ እንዲህ አላደርግም... ወዘተ ማለት አለብን።

**5ኛ. ደካማ ጎናችን ላይ ስለምናተኩር**

ደካማ ጎናችን ላይ ስለምናተኩር ይሆናል ሰነፍ እንደሆንን የሚሰማን። ያተኩርንባቸው ነገሮች ጎልተው መውጣት ይጀምራሉ። ድክመታችን ላይ የምናተኩር ከሆነ በቃ! ሙሉ በሙሉ ይቆጣጠረናል። ዛፉን ብቻ የምናይ ከሆነ መኪና እየነዳን ከዛፉ ጋር መጋጨታችን አይቀርም።

ስለዚህ በአንድ ትምህርት ደከም ካልን አይ እኔ እኮ በሁሉም ትምህርት ነው ልንል እንችላለን። በፍቅር ግንኙነታችን፣ ወይ በሥራ አልያም ደግሞ በትምህርት በሆነ አጋጣሚ ድክመት ካለብን እኔ እኮ አልረባም ልንል እንችላለን። ግን ጠንካራ ጎናችን ላይ ብናተኩርስ? ለምሳሌ ትምህርት ካላዋጣን ለምን ቢዝነስ ላይ አናተኩርም። ተግባቢ ከሆንን ከመግባባት ጋር የተገናኘ ሥራ አንሠራም።

ለምሳሌ ኃይሌና ዩዜን ቦልት በመቶ ሜትር ርቀት ሩጫ ሊፋለሙ አይችሉም። ዩዜን ቦልት በርቀቱ አንበሳ ነው። ኃይሌ ደግሞ በ10 ሺ ሜትር አንበሳ ነው። ስለዚህ እናንተም ለምን ጠንካራ ጎናችን አልጎላም ብላችሁ መጨነቅ እንጂ ደካማ ጎናችሁ ላይ በፍጹም አታተኩሩ። የስንፍናህ መነሻው ደካማ ጎንህ ላይ ማተኮርህ ነው። ስለዚህ የስንፍና መድኃኒቱ ጠንካራ ጎንህ ላይ ማተኮር ነው።

**6ኛ. በትናንሽ ስኬቶቻችን እንደሰት**

ትንሽ ነገር ስታሳኩ ‹‹እኔ እኮ ምን ዓይነት ጭንቅላት ነው ያለኝ፣ እንዴት ጎበዝ ነኝ›› እያልን ራሳችንን እናድንቅ፤ ለራሳችን እንንገር። በራሳችን ፊት ራሳችን ግዙፍ እንደሆንን እንዲሰማን እናድርግ። አንዳንዴ በጣም የምናደንቃቸው ሰዎች አሉ። በስፖርት፣ በሙዚቃ ወይ ደግሞ በፖለቲካና በኪነጥበብ ሊሆን ይችላል። አንድ ነገር ግን ይወቁ! እዛ ሰው ውስጥ ያለው ማንነት ወይም ችሎታ እኛም ውስጥ አለ። ማመን ብቻ ነው የሚጠበቅብን።

እንደዚህ ዓይነት እምነት ግን የምናዳብረው በትናንሽ ልፋቶች ነው። በትናንሽ ጥረቶች ነው። ወይም በትናንሽ እምነቶች ነው። ስለዚህ ትናንሽ ነገሮችን ስናሳካ ‹‹አዬ! ቀላል ሰው አድርጋችሁኛል! በጣም ጀግና ሰው ነኝ፣ በጣም ጎበዝ ነኝ›› ስንል ሌሎች ነገሮችንም እንድንሞክር ማንነታችን ይገፋፋናል። ‹‹እንዴ! ባለፈው የሰራኸው ነገር እኮ የሚገርም ነው ይችን ብትሞክራትስ›› ይልሃል። አያችሁ ስንፍና ወደኋላ ያስቀራችሁ ለራሳችሁ የምትሰጡት አድናቆት በማነሱ ነው። ራሳችሁን አድንቁ።

በነገራችን ላይ በጣም ጉረኛ ሰዎች ሕይወታቸው በጣም የተስተካከለ ነው። ያው ጉረኛ ስለሆኑ እኛ ላንወዳቸው እንችላለን። እነርሱ ግን በጎረሩ ቁጥር ‹‹እንዲህ አለኝ እኮ፣ ቀላል ሰው አድርገኸኛል›› እያሉ በባዶ ሜዳ ጎርረው የሆነ ሰዓት ላይ ያ ነገር ወደ ሕይወታቸው ይመጣል። አያችሁ! በራሳቸው ገዝፈው ይታያሉ። ስለዚህ እኛስ? ሰው ፊት ባንጎርር ለራሳችን ለምን አንጎርርም? ራሳችንን ለምን አናደንቅም? እንደምንችል ለራሳችን እየደጋገምን ለምን አንነግረውም ?ትንሽ ነገር ስናሳካ ‹‹ቀላል ሰው አይደለሁም እኔ! ጀግና ነኝ›› እንበል። ከዛ ለውጡ ታዩታላችሁ። ስለዚህ ወዳጆች! ከላይ በተዘረዘሩት ስድስት ነጥቦች መሠረት ሰነፍ ስለሆናችሁ አይደለም፤ ከነዚህ ክፍተቶች መካከል አንዱ በውስጣችሁ ስላለ ነው። እነዚህ ነገሮች የሏችሁም ማለት ግን ሰነፍ ናችሁ ማለት አይደለም። ለምን? ማስተካከል ትችላላችሁ። ስለዚህ ከነመፍትሔው ሕይወታችሁ ላይ መተግበር እንዳትረሱ።

# ማህደረ ጤና

# ትኩረት ያላገኘው የአዕምሮ እድገት ውስንነት

**አስናቀ ፀጋዬ**

የሰው እድገት ተለዋዋጭና ከፅንሰት እስከሞት የሚኖሩትን አካላዊ፣ አዕምሯዊ፣ ማህበራዊና ሥነ ልቦና ለውጦችን ያካትታል። ስለዚህ የሰዎች ዕድገት የለውጥ ሂደት ነው ማለት ይቻላል። ይህ የለውጥ ሂደት ደግሞ በተፈጥሮና በአካባቢ መስተጋብር ላይ የተመሠረተ ነው።

የአንድ ሰው የሕይወት ቆይታ ተለዋዋጭ ነው ተብሎ ይታሰባል። በዚህም የአዕምሮ ግንዛቤ አቅሙ ትርጓሜው በብዙ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። በዋናነት ግን የሰዎች የአዕምሮ ግንዛቤ ሲባል የመማር፣ የማሰብ፣ የማመዛዘን፣ ችግር የመፍታት፣ የማቀድ፣ የመወሰን፣ የማይዳሰሱ ነገሮችን የማሰብና የተማሩትን ነገር የማስተላለፍ፣ ይዞ የማቆየት፣ መረጃዎችን የመተንተን፣ እውቀቶችን መፍጠርና ኑሮን የመቋቋም ወዘተ የመሳሰሉትን ነገሮች ያጠቃልላል።

በዚህ የአዕምሮ ግንዛቤ አቅም ውስጥ ራስን የማስማማትና የማለማመድ ክህሎቶች ይኖራሉ። ይህም ራስን ችሎ ለመኖር አስፈላጊ የሆኑ ችሎታዎች ወይም ክህሎቶችን ለምሳሌ የነገሮችን ፅንሰ ሃሳብ የመለየት አቅም/conceptual skill/፣ ማህበራዊ ክህሎት /social skill/ እና ተግባራዊ ክህሎት /practical skill/ በስሩ ያካትታል። ለሰው እድገት አስፈላጊ የሆኑ አካባቢያዊና ግብዓቶች በመጓደላቸው ምክንያት በግላዊና ማህበራዊ ክዋኔዎች ረገድ መዘግየት ሲፈጠር የአዕምሮ እድገት ውስንነት/intellectual disability/ ይከሰታል።

በኢትዮጵያ በቂ ጥናት ባለመደረጉ ከአዕምሮ እድገት ውስንነት ጋር የሚኖሩ ሰዎች ቁጥር ምን ያህል እንደሆነ በትክክል አይታወቅም። ነገር ግን የዓለም ጤና ድርጅት በአዕምሮ እድገት ውስንነት ላይ ባወጡት መረጃ መሠረት በኢትዮጵያ ካለው 110 ሚሊዮን በላይ ከሚሆን ሕዝብ ውስጥ ከሰባት ሰዎች ውስጥ አንዱ የአዕምሮ እድገት ውስንነት እንዳለበት አመልክቷል። ዩኒሴፍ እ.ኤ.አ በ2018 ባወጣው ሪፖርት መሠረት ደግሞ 7 ነጥብ 8 ሚሊዮን ሰዎች በተለያዩ የአዕምሮ እድገት ውስንነት እንደተጠበቁ አሳይቷል። ይህም ኢትዮጵያ ካላት ሕዝብ ወደ 9 ነጥብ 3 ከመቶ ያህሉ በዚህ ሕመም ውስጥ እንዳለ ያሳያል።

የአእምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ሰዎች በህብረተሰቡ በኩል የሚደርስባቸው መገለልና መድልኦም ቀላል የሚባል አይደለም። ይህንን ተከትሎም በርካታ ወላጆችም ታማሚ ልጆቻቸውን በቤት ለመደበቅ ተገደዋል። ጥቂት ወላጆች ናቸው ዛሬ ላይ ደፍረው ልጆቻቸውን በአደባባይ አውጥተው ከአዕምሮ እድገት ውስንነት ጋር የሚኖሩ ልጆች እንደሌሎች ጤናማ ልጆች መማር፣ መሥራትና አዲስ ነገር መፍጠር እንደሚችሉ ያሳዩት። ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች ከአዕምሮ እድገት ውስንነት ጋር ለሚኖሩ ልጆችና ወላጆቻቸው ብርሃን የሆኑት። እነዚህ ወላጆች ናቸው ዛሬም ድረስ የአዕምሮ እድገት ውስንነት በመንግሥት በኩል ትኩረት እንዲያገኝ ግፊት እያደረጉ ያሉት። እነዚህ ወላጆች ናቸው በአዕምሮ እድገት ውስንነት ዙሪያ ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ እየሰሩ ያሉት።

ከነዚህ ወላጆች ውስጥ ወይዘሮ ምህረት ንጉሴ አንዷ ናቸው። እርሳቸው የፍቅር ኢትዮጵያ የአዕምሮ እድገት ውስንነት ብሔራዊ ማህበር ፕሬዚዳንት ናቸው። ማህበሩን የመሠረቱት ከሌሎች ልጆቻቸው የአዕምሮ እድገት ውስንነት ካለባቸው ወላጆች ጋር በመሆን ነው። የእርሳቸውም ታናሽ ወንድም ከአእምሮ እድገት ውስንነት ጋር ይኖራል።

እርሳቸው እንደሚሉት፣ ማህበሩ ከዛሬ 29 ዓመት በፊት በ1987 ዓ.ም የተቋቋመ ሲሆን አላማውም በአዕምሮ እድገት ውስንነት ዙሪያ ለወላጆች፣ ለመንግሥት አካላት፣ መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ አካቶ ትምህርትን ማስፋፋት፣ በተለያዩ ሙያዎች ማሰልጠን፣ የፊዚዮቴራፒ አገልግሎት መስጠት፣ በኢኮኖሚ ለማብቃት የወላጆችን አቅም ማሳደግ፣ መረጃዎችን ተደራሽ ማድረግ ነው።

ሥራውን በአዲስ አበባ የጀመረው ማህበሩ በስምንት ክልሎች ከ17 በላይ ቅርንጫፎች ከፍቶ ከ15 ሺ በላይ አባላትን በማፍራት አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። ከአካቶ ትምህርት ጋር በተያያዘም ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በቅርበት ይሠራል። ቀደም ሲል በአዲስ አበባ አንድ ብቻ የነበረውን የአካቶ ትምህርት በአሁኑ ጊዜ ከ15 በላይ እንዲሆን የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል። ከ150 በላይ ልጆች በተለያዩ ሙያዎች አሰልጥኗል።

ከዚህ ባሻገር ማህበሩ ከሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በቅርበት እየሠራ የሚገኝ ሲሆን በርካታ የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ልጆች ከቤት እንዲወጡ የበኩሉን ድርሻ ተወጥቷል። ከአዕምሮ እድገት ውስንነት ጋር በተያያዘ ለመምህራን ተከታታይ ሥልጠናዎችን ከመስጠቱም በላይ ለሃይማኖት አባቶች፣ ለፍትህ አካላትና ለሚዲያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ሰርቷል።

ፕሬዚዳንቷ እንደሚያብራሩት የማህበሩ ሃያ ዘጠኝ ዓመታት ጉዞው አልጋ በአልጋ አልነበረም። በተለያዩ ችግሮች ውስጥ አልፏል። በተለይ ከአዕምሮ እድገት ውስንነት ጋር የሚኖሩ ልጆችን ከተደበቁበት የማውጣት ሥራ ላይ አተኩሮ ሲሰራ ስለቆየ ውጣውረዶቹ ቀላል አልነበሩም። ነገር ግን በነዚህ ውጣውረዶች ውስጥ ማህበሩ ያከናወናቸው ሥራዎች ዛሬ ላይ ፍሬ አፍርተዋል። ዛሬ ላይ በማህበሩ ውስጥ ገብተው ትምህርት ያገኙ ከአእምሮ እድገት ውስንነት ጋር የሚኖሩ ልጆች ትልቅ ለውጥ አምጥተዋል። ከዚህም በላይ እገዛ ቢደረግላቸው ደግሞ ትልቅ ቦታ ሊደርሱ ይችላሉ።

የዚህ ዓመት የአዕምሮ እድገት ውስንነት ቀን መሪ ቃል «ፍረጃ ይቁም» የሚል ነው። ይህ መሪ ቃል የመረጠውም ያለ ምክንያት አይደለም። ይህ ጭፍን ፍረጃ ነው በርካታ ከአዕምሮ እድገት ውስንነት ጋር የሚኖሩ ልጆችን እንዲደበቁና ወደኋላ እንዲቀሩ ያደረገው። ፍረጃው ከቤተሰብ፣ አካባቢና ከማህበረሰብ ነው የሚጀምረው። ይሁንና ፍረጃው ሲቀርና አስፈላጊው ድጋፍ ሲደረግላቸው የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ዜጎች ማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል ሊያደርገው የሚችለውን ነገር ሁሉ ማድረግ ይችላሉ።

የአዕምሮ እድገት ውስንነት በመንግሥትም ሆነ በተቀረው የህብረተሰብ ክፍል በኩል ትኩረት ሲያገኝ እነዚህ ልጆች ትልቅ ደረጃ ላይ መድረስ ይችላሉ። ማህበረሰቡ የሚቀበላቸውና የእኛ ልጆች ናቸው ብሎ ከአዕምሮ እድገት ውስንነት ጋር አብረው የሚኖሩ ልጆችን እንዲቀበላቸው ልጆቹ ወደፊት ከፍ ያለ ቦታ እንዲደርሱ የሁሉም ሰው ድጋፍ ያስፈልጋል።

ወይዘሮ ናርዶስ አሰፋ የብሩህ የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ልጆች ማዕከል መሥራችና ዳይሬክተር ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት በልጅነት ጊዜ ልጆች የተለያዩ ራሳቸውን የመቻል እንቅስቃሴዎችን ይጀምራሉ። ከነዚህም መካከል በራሳቸው መመገብ፣ መልበስ፣ መፀዳዳት፣ መሄድና የመሳሰሉት ይገኛሉ። ሆኖም እድሜያቸው ከፍ ሲልና በታዳጊነት የእድሜ ክልል ላይ ሲደርሱ ከጥገኝነት ለመላቀቅ በልጅነት ጊዜ ካገኙት ክህሎት በመነሳት የተለያዩ ክህሎቶችን ያዳብራሉ። እነዚህን ከጥገኝነት የሚያላቅቁ ክህሎቶችና የግል እንክብካቤ ያተኮሩ ተግባራትን የሚፈጥሩበትን እድል ማመቻቸት ያስፈልጋል።

ይህም ለአንድ ግለሰብ በራስ መተማመንና በማህበረሰብ ተሳትፎ የዳበረና ኃላፊነት የሚሰማው ቤተሰብ ለመፍጠር እጅግ የጎላ አበርክቶ ይኖረዋል። የሰብዓዊ መብት በዋናነት ሕፃናትን መንከባከብና በክህሎት አበልፅጎ ማሳደግ ድህነትን የመቅረፍና ማህበረሰቡን ኢኮኖሚ ዋነኛ ቁልፍ ተግባር ነው።


እንደ ዳይሬክተሯ ገለፃ፣ ማዕከሉ ከአዕምሮ እድገት ውስንነት ጋር የሚኖሩ ልጆችን ለመርዳት የተቋቋመ ሲሆን ሥራ ከጀመረ አስራ ስድስተኛ ዓመቱን ይዟል። በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ልጆች በእለት ተእለት እንቅስቃሴያቸው ከጥገኝነት እንዲላቀቁ ለማድረግ ከስድስት በማይበልጡ ልጆች ሥራውን ጀምሮ ለአስራ አምስት ዓመታት ዘልቋል። በአሁኑ ወቅት ደግሞ እድሜያቸው ከስድስት እስከ ሃያ ዓመት ያሉ የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው 39 ልጆችን በስሩ ይዞ እንክብካቤና የክህሎት ማሳደጊያ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል።

የሚንከባከባቸው ልጆች በራሳቸው እንዲመገቡ፣ እንዲለብሱ፣ ጫማቸውን እንዲያደርጉ፣ እንዲፀዳዱና ቀለል ያሉ የቀለም ትምህርቶችንና የሙያ ሥልጠናዎችን እንዲከታተሉ እያደረገ ነው። ከዚህ ባለፈ የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ልጆች ወላጆች ምርታማ እንዲሆኑ በእለት ተእለት እንቅስቃሴያቸው ልጆቻቸውን በቤት ውስጥ በመንከባከብ ከሚያወጡት ጊዜና ድካም እንዲያርፉና በአዕምሯቸው ላይ የሚፈጠረውን ጫና ለመቀነስ በማሰብ ብሎም የማህበረሰብ አሉታዊ ተፅእኖ በመፍራት ሸሽገው ያስቀመጧቸውን ልጆች ግንዛቤ በማስጨበጥ እንዲያወጡ የማድረግ ሥራዎች ይሠራሉ። ከጭንቀትና ከመከራ ስሜት በማውጣት ራሳቸውን እንዲችሉና የገቢ ምንጭ እንዲያገኙ ሥልጠና በመስጠት ረገድም ማዕከሉ ከፍተኛ ሥራ ሰርቷል።

ማዕከሉ እስካሁን ባደረገው ጥረት ህብረተሰቡን በማንቃትና ግንዛቤ በማስጨበጥ የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ልጆች ከቤት ወጥተው እንደ ትምህርትና የጤና አገልግሎቶችን ቀርበው እንዲያገኙና እንዲታገዙ በማድረግ የበኩሉን ድርሻ ተወጥቷል። መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የዚህ ችግር ተጠቂ የሆኑ ሕፃናት ተገቢውንና አቅም የፈቀደውን ትምህርትና ሥልጠና እንዲያገኙ በማድረግ ባለሙያዎችን በማሳተፍ የህብረተሰቡን አቅም በማስተባበርና ድርጅቶችን በማሳተፍ ረገድም የራሱን አስተዋጽኦ አበርክቷል።

የዚህ ችግር ዋነኛ ገፈት ቀማሽ የሆኑትን እናቶችን የእለት ከእለት እንቅስቃሴያቸውንና ማህበራዊ ሕይወታቸውን እንዲመሩና እንዲያስተካክሉ ከማድረግ አንፃርም ማዕከሉ በርካታ ሥራዎችን አከናውኗል። በዚህ ጉዳይ ላይ ከሚሰሩ ተቋማት ጋር ትስስር በመፍጠርና የልምድ ልውውጦችን በማድረግ ጠቃሚና ገንቢ የሥራ እንቅስቃሴዎች እያደረገም ይገኛል።

ይሁንና ማዕከሉ የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ልጆችን ተቀብሎ ለማስተናገድ የሚያስችል ሀብት ያለመኖር፣ ቋሚ የማሰልጠኛና የማስተማሪያ ቦታ ያለመኖር፣ በሙያው የሰለጠኑ ባለሙያዎች እጥረት፣ ለመማር ማስተማርና ማሰልጠኛ ሊሆን የሚችል በቂ የግብዓት አቅርቦት አለመኖር፣ ንቁ የወላጆች ተሳትፎ አለመኖር የመሳሰሉ ችግሮች አሉበት።




‹‹ የዓለም ጤና ድርጅት በአዕምሮ እድገት ውስንነት ላይ ባወጡት መረጃ መሠረት በኢትዮጵያ ካለው 110 ሚሊዮን በላይ ከሚሆን ሕዝብ ውስጥ ከሰባት ሰዎች ውስጥ አንዱ የአዕምሮ እድገት ውስንነት እንዳለበት አመልክቷል። ዩኒሴፍ እ.ኤ.አ በ2018 ባወጣው ሪፖርት መሠረት ደግሞ 7 ነጥብ 8 ሚሊዮን ሰዎች በተለያዩ የአዕምሮ እድገት ውስንነት እንደተጠቁ አሳይቷል። ››

ከዚህ አንፃር ማዕከሉ የአዕምሮ እድገት ውስንነት በመንግሥትም ሆነ በህብረተሰቡ ዘንድ በቂ ትኩረት እንዲያገኝ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች በግልና በመንግሥት ሚዲያዎች በኩል እየተሠሩ ይገኛሉ። የማህበረሰቡን ሁለንተናዊ ተሳትፎ የማሳደግ፣ የወጡ የመንግሥት ፖሊሲዎችንና ስምምነቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ እየተሠራ ነው።

በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የአካል ጉዳተኞች ጉዳይ መሪ ሥራ አስፈፃሚ ተወካይ አቶ መሰለ ተስፋ በበኩላቸው እንደሚናገሩት፣ በአካል ጉዳተኞች ዙሪያ ሶስት አካላት ወሳኝ ሚና አላቸው። አንደኛው መንግሥት ሲሆን በመንግሥት ደረጃ መሥራት የሚገባውን የሕግ ማዕቀፎች ከማውጣት፣ የአሠራር ሥርዓት ከመዘርጋት፣ አደረጃጀቶች ከመፍጠር አንፃር የድርሻውን መወጣት አለበት።

ሁለተኛው ማህበረሰቡ ሲሆን የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸውን ዜጎች ከሌሎች ዜጎች ባልተለየ ሁኔታ ሊንከባከባቸውና ሊደግፋቸው ይገባል። ግንዛቤውም በዛው ልክ ማደግ ይኖርበታል። ግንዛቤውን ለማሳደግ ደግሞ በተለይ የሚዲያ አካላት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው። በሶስተኛ ደረጃ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ወገኖችን የሚረዱ ማዕከላትን በማገዝና ከጎናቸው በመቆም፤ ለሚሠሩት ሥራም ድጋፍና እውቅና በመስጠት አጋርነታቸውን ማሳየት አለባቸው። እስካሁን ድረስ በዚህ ጉዳይ ላይ ያልሰሩ ድርጅቶችም ካሉ ተቀላቅለው ሥራውን ሊደግፉ ይገባል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን በአዋጅ ቁጥር 676 በማፅደቅ ወደ ሥራ ተገብቷል። ነገር ግን ሥራው በአጥጋቢ ሁኔታ መሬት ላይ ውርዷል ማለት አይቻልም። የወጡ አካታች ፖሊሲዎች አሉ። ሆኖም አተገባበራቸው በሚፈለገውና ለውጥ ሊያመጣ በሚችል መልኩ ተተግብሯል ለማለት አይቻልም።

ስለዚህ በመንግሥት በኩል የወጡ አዋጆችን ተግባራዊ በማድረግ፣ የወጡ ፖሊሲዎችን ወደ መሬት በማውረድ ከዜጎች ጋር በመሆን ወደፊት የሚሰራበት እድል አለ። ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል ግን ከአዕምሮ እድገት ውስንነት ካለባቸው ዜጎች ጋር አብሮ መሆንና መደገፍና መንከባከብ አለበት።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ምርታማነት ለማሻሻል

**በኃይሉ አበራ**

ለማንኛቸውም መሰረተ ልማቶች መሰረት የሚጥለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ነው። በጤናና በትምህርት ተቋማት፣ በኢንዱስትሪ፣ በመስኖና ግድብ ግንባታዎች እና በሁሉም ዘርፎች የሚሰሩ ግንባታዎች በዋነኛነት የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን የሚጠይቁ ናቸው። የግብአቶቹ አቅርቦት መሳለጥና አለመሳለጥ፣ በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋልና አለመዋል በመሰረተ ልማት ግንባታዎቹ ወጪ፣ በተያዘላቸው ጊዜ መጠናቀቅና አለመጠናቀቅ ላይ ተጽኦኖ ያሳድራሉ፤ በአጠቃላይ በዘርፉ ምርታማነት ላይ የራሳቸውን ተጽእኖ ያሳርፋሉ።

በኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ዘርፉን ለማሻሻል እና ኢንዱስትሪውን ለማዘመን ከ20 ዓመታት በፊት የተደረጉ ጥናቶች እስካሁን ተግባራዊ እየተደረጉ መሆኑን መረጃዎች ያመላክታሉ። እነዚህ ጥናቶች አሁን ሊጠቅሙ ቢችሉም፣ ተጨማሪ ጥናቶችን ማድረግ እንደሚገባ ታምኖበታል፡፡

በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ዘርፉ ምርታማነት ላይም በየጊዜው ለውጦች ይታያሉ። በተለይም በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ከውጭ የሚመጡ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እና በሀገር ውስጥ የሚፈጠሩት የተሻሻሉ አሰራሮችና በየጊዜው የሚታዩ ለውጦች በኮንስትራክሽን ምርታማነት ላይ ያላቸውን ለውጥ በተመለከተ በየጊዜው ጥናቶች ይደረጋሉ። ጥናቶቹም ሳይት ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች ከተቀመጠው ስታንዳርድ አንፃር የመፈፀም አቅማቸውን በማየት የግንባታ ተቋሞቹ ምን ላይ እንደሚገኙ እና ውጤታማነታቸውን እንዲለኩ የሚያግዙ ናቸው።

በኮንስትራክሽን ዘርፍ የሰው ኃይል እና የማሽነሪ እንዲሁም የግብዓት አቅርቦት፣ የፈረቃ ስራ የመሳሰሉ ለኮንስትራክሽን ዘርፉ ምርታማነት መሻሻል የራሳቸው ሚና አላቸው። ዘርፉን ለማሳደግ ቁልፍ ሚና ካላቸው ነገሮች አንዱ የሰው ኃይል አደረጃጀት እና ተገቢ የስራ ሰዓት ቁጥጥር መሆኑም መረጃዎች ያመላክታሉ። እየጨመረ በሚሄደው የግንባታ ግብዓት ዋጋ ምክንያትም የግንባታ ባለቤቶች ለተጨማሪ ወጪ ከመዳረጋቸው ይልቅ በቂ የሰው ኃይል በመመደብ እና 24 ሰዓት በማሰራት ምርታማነቱን ማሻሻል ያስችላል። በቂ የሰው ኃይል መድቦ እና ፕሮጀክቱን በፈረቃ መስራት ፕሮጀክቶች ሲቆዩ ከሚመጣው የዋጋ እና የግብዓት ጭማሪ አኳያ ወጪ የሚቀንስ ስለመሆኑም የዘርፉ ባለሙያዎች ይጠቁማሉ፡፡

በኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት የአሰራር ሥርዓት ማሻሻያ ዳይሬክተር ኢንጂነር አበራ አውግቸው እንዳሉት፤ የኮንስትራክሽን ዘርፉ ምርታማነት አንድ ስራ ከተከናወነ በኋላ የተገኘው ውጤት ስራውን ለመስራት ጥቅም ላይ ከዋለው ግብዓት ጋር የሚነፃፀርበት ነው። የፕሮጀክቶችን ምርታማነት ለማሻሻል እና በጊዜ ከማጠናቀቅ አኳያ ስራዎችን በፈረቃ መስራትም ወጪ ብቻ እንዳለው በአንዳንድ ወገኖች ይታሰባል። ነገር ግን በፈረቃ መስራት ስራዎችን በፍጥነት በማጠናቀቅ አሁን ከሚታየው ከዋጋ ግሸበት አንጻር የሚገኝ ትርፍ አለ። እንዲሁም የሰው ኃይሉን እና ማሽነሪውን ሌላ ስራ በማዋል ኮንትራክተሩ ተጨማሪ ስራዎችን ለማግኘት ያስችለዋል። እነዚህን ታሳቢ አድርጎ ሙያዊ የሆኑ እይታዎችን በመስጠት የመስራት ክፍተት እንዳለም ዳይሬክተሩ ያመላክታሉ።

አንድን ግንባታ ለማጠናቀቅ ጥቅም ላይ የዋለው ካፒታል፣ የሰው ኃይል፣ ኢነርጂ፣ አገልግሎቶች፣ ማቴሪያሎችን በመጠቀም የተገኘውን ወይም የተመረተው የአንድ የኮንስትራክሽን ውጤት የሚነፃፀርበት ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ከዚህ አንፃር የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የምርታማነት ደረጃ ለማሻሻል ውስጣዊ ምክንያት የሆነው የሰው ኃይሉ እና የውጫዊ ምክንያቶች የሆኑት ካፒታል፣ ኢነርጂ፣ አገልግሎቶች፣ ማቴሪያሎችን የመሳሰሉት የየራሳቸው ሚና አላቸው። ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ምርታማነት ተፅዕኖ ካላቸው መካከል ዋንኛዎቹ የሰው ኃይሉ እና የማሽነሪ አቅርቦት መሆናቸውን ያመላክታሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ ኢንስቲትዩቱም በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ዋነኛ ሚና የሚጫወቱ



መረጃ ሰብሳቢዎች በሥራ ላይ

ኩባንያዎችና የፕሮጀክት ባለሙያዎችን አቅም መገንባት ላይ አተኩሮ ይሰራል። የኮንስትራክሽን የስራ ሂደት እና የምርታማነት ደረጃ ምን እንደሚመስል ጥናት ማድረግ እና ጥናቱ ላይ ተመርኩዞ ለኢንዱስትሪው መነሻ የሚሆን የምርታማነት መመሪያ ሰነድ ያዘጋጃል። በቅርቡም በኢንስቲትዩቱ የኮንስትራክሽን ምርታማነት ከማሳደግ አኳያ በተለይም የሰው ኃይል እና የማሽነሪ ምርታማነት ላይ ያተኮረ ጥናት ተካሄዷል።


በጥናቱም መጀመሪያ እንደ ግብ ተይዞ የተሰራው ከኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው አንፃር ምርታማነት የሚታቀድ እና የሚለካ ራሱን የቻለ ቁልፍ ተግባር ለማድረግ እንዲሁም አሁን ያለው የሠራተኛው ምርታማነት፣ አማካይ የሰው ኃይሉ፣ የማምረት ደረጃ የሚፈተሸበት ነው። ሠራተኛው ስራ ላይ በተሰማራበት ወቅት ምን ያህሉን የስራ ሰዓት ቀጥታ ለምርት አስተዋፅኦ ባለው መልኩ አውሎታል የሚለውን የስራ ናሙና በመውሰድ በጥናቱ ለማወቅ እየተሰራ መሆኑን ያስረዳሉ።

በተጨማሪም ጥናቱ ያስፈለገበት ዋነኛ ምክንያት በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ምርታማነት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮችን ለመለየት እና በጉዳዮቹ ላይ ክትትል በማድረግ፣ እርምጃ በመውሰድ ምርታማነቱን ለማሻሻል መሆኑንም አመላክተዋል።

በጥናቱ በአንድ ጊዜ ይሄን ያህል ማምረት ይቻላል ወይም ደግሞ ከኪራይ ሰብሳቢነት ወይም ከካሳ ጥየቃ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ሲነሱ ለመፍታት ስላለው ፋይዳም አብራርተዋል። ጥናቱ ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ፣ የፕሮጀክት አመራር ለማሳደግ፣ ዘመናዊ አሠራርን ለማስፈን፣ የካሳ እና የክስ ጉዳዮች የመሳሰሉትን ለመዳኘት ጠቀሜታዎች መሆኑን ዳይሬክተሩ ያመላክታሉ። በአጠቃላይ ጥናቱ ኢንዱስትሪውን ተወዳዳሪ እና አቅሙ የጎለበተ ለማድረግ እና ሁልጊዜም አፈጻጸሙን እየለካ ለመሄድ የሚያስችል መሆኑን ገልጸው፤ የምርታማነት ዓላማ ካልተቀመጠ እና ካልተለካ ወዴት እንደሚሄድ የማይታወቅና የቁጥጥር ስራ ለማከናወንም የማያስችል በመሆኑ የተመላከተ ሲሆን፤ ጥናቱ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ መፍትሔ የሚሰጥ መሆኑን አስገንዝበዋል።

ዳይሬክተሩ፤ ጥናቱ በኮንትራክተሮች ዘንድ በዋጋ ዝግጅት ጊዜ የሚፈለግ አንዱ ቁልፍ ግብዓት ነው። ለአብነት ‹‹አንድ ሜትር ኪዩብ ለማምረት ስንት ሠራተኞች ያስፈልገኛል? እነኚህ ሰራተኞች ደግሞ በሰዓት ምን ያህል ያመርታሉ? የሚለውን አንድ ኮንትራክተር ወይም የፕሮጀክት ባለቤት ካላወቀ የፕሮጀክት ዋጋውን መስራት አያስችለውም›› ይላሉ።

ኢንጂነር አበራ እንደገለፁት፤ እ.ኤ.አ በ1995 ዓ.ም ‹‹Ethiopian Construction Production Norm (ECPN)3 እንዲሁም እ.ኤ.አ በ1999 ዓ.ም አካባቢም (ECPN)5 በሚል ጥናቶች ተደርገዋል፤ እነዚህ ሰነዶች እስካሁንም በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ጥቅም ላይ እየዋሉ ናቸው። ሰነዶቹ በአማካይ ከሃያ ዓመት በላይ የሆኑ ሲሆን፣ ነገር ግን ምርታማነት ደግሞ በየወቅቱ በፕሮጀክት ትግበራ ላይ በተዘረጉ የተለያዩ የአሰራር ስርዓቶች እና የቴክኖሎጂዎች ግብዓት ይቀየራል።በመሆኑም ከዘመኑ ጋር አብሮ ለመጓዝ




የብረት ሥራ ሙያተኞች የሰዓት አጠቃቀም የሚያሳይ ናሙና

ያስችል ዘንድ በየጊዜው ጥናቶች እየተጠኑ ወቅታዊ ይደረጋሉ። ከዚህ ቀደም የተደረጉት ጥናቶችም እስካሁን እያገለገሉ እና ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳደረጉ መዘንጋት የለበትም።

ቀደም ብለው የተጠኑት እና አሁን ደግሞ በኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት አነሳሽነት እየተካሄደ ያለው የምርታማነት ጥናት የአጠናን ስልቱም የተለየ መሆኑን ዳይሬክተሩ ያመላክታሉ። የቀደሙት በአብዛኛው ከኮንትራክተሮች በተሰበሰበ መረጃ፣ ከጨረታ እና ከመሳሰሉ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ተመርኩው የተካሄዱ መሆናቸውን አንስተው፤ የአሁኑ ግን ዘመናዊ እና ሳይንሱ የደረሰበት የኮንስትራክሽን ምርታማነት የሚለካበትን ስርዓት ለመከተል የመረጃ ሰብሳቢዎች የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጭ ከሳይት ላይ ቆመው የሚሰበስቡበት እንደሆነ አስረድተዋል።

ይህም ሰፊ እና ትልቅ ሀብት የሚፈልግ ስራ መሆኑን ጠቅሰው፣ በዋናነት ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ የሚገኘውም ጥቂት ሆነው ነገር ግን ድርሻቸው እና ተፅኖአቸው የ80 በመቶ ድርሻ ያላቸውን ተግባራት በመምረጥ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ጥናቱም በሰው ኃይሉ እና በማሽነሪ ምርታማነት ላይ እየተካሄደ መሆኑን ገልጸዋል።

እስካሁን ባለው የጥናቱ ፕሮጀክት ሂደትም በ2011 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ በሙከራ ደረጃ ተከናውኗል። ይህም የፕሮጀክት ስልቱ የመጀመሪያ መሆኑና አገራዊ ተደርጎ ሲሰራ ለሚመጡ ችግሮች ቀደም ብሎ መፍትሄ ለማስቀመጥ ስለሚያስችል ይህን መሰረት ነው ብለዋል።

በመቀጠልም በ2012፣ 2013ዓ.ም ኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት ኮረናን ታሳቢ ያደረገው አሰራር የሚተገበር በመሆኑ የተነሳ፤ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ላይ ያሉትን በመተው የአርክቴክቸር እና የኢንጂነሪንግ ምርታማነት፤ የምህንድስናው ዘርፍ ላይ ያተኮረ እንደነበረ አመላክተዋል።

እንደ እሳቸው ማብራሪያ፤ በ2013 ዓ.ም በተደረገው ጥናትም በዋነኛነት የምህንድስና ስራዎች፣ የአርክቴክቸር እና የኢንጂነሪንግ ስራዎችን መለካት የሚቻል መሆኑን ለማወቅ ተሞክሯል። እነዚህ ስራዎች ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮችንም ለመለየት ጥረት ተደርጓል። የጥናቱ ሁለተኛው ክፍልም በዋናነትም በአርክቴክቸር እና በኢንጂነሪንግ የማማከር ስራዎች ላይ ለተሰማሩ ተቋማትም በተመሳሳይ አሰራራቸውን የመፈተሽና በቀጣይ የዘርፉን ምርታማነት ለማሻሻል ምን ማድረግ እንደሚገባ ያሳየ መሆኑን ይገልጻሉ።

ይህን ተከትሎም በ2014 እና 2015 ዓ.ም በሰባት ከተሞች ሀገር አቀፍ የህንፃውን ዘርፍ ምርታማነት ጥናት በማድረግ ሀገር አቀፍ የህንፃው ዘርፍ ጥናትን ለመስራት መሞከሩን ይናገራሉ። እሳቸው እንዳሉት፤ይህን ማድረግ ያስፈለገበት ምክንያትም የኮንስትራክሽን ዘርፉ ምርታማነት በሰው ኃይል፣ በተቋማዊ አደረጃጀት እና አካባቢያዊ በሆኑ ጉዳዮች እና የአሰራር ልምዶች ተፅዕኖ ውስጥ የወደቀ በመሆኑ ነው።

በመሆኑም በሀገር አቀፍ ደረጃ በአዲስ አበባ የተሰራው የምርታማነት ጥናት ሰመራ፣ ጅማ፣ አርባ ምንጭ፣ መቀሌ እና ባህርዳር ላይ ለሚተገበሩ ፕሮጀክቶች በቀጥታ መጠቀም ተገቢ ላይሆን ይችላል። ምክንያቱም የኮንስትራክሽን ምርታማነት ስራዎች በአካባቢያዊ ጉዳዮች፣ በአሰራር ልምዶች እና ስልቶች ተቋማዊ በሆኑ እና ሰዋዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተወሰነ ነው። በሌሎችም ቦታ ተግባራዊ ለማድረግ በየቦታው እነዚህ ነገሮች ታሳቢ አድርጎ መውሰድ አስፈላጊ ስለሆነ ከ2014 እና 2015 ዓ.ም በሰባት ከተሞች አገር አቀፍ የህንፃው ዘርፍ ምርታማነት ጥናት ተደርጓል።

ጥናቱ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት አማካሪነት የተሰራ ነው። በተለይም ከአዲስ አበባ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣ ከሀዋሳ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣ ከባህርዳር የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣ ከድሬዳዋ እና ከአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ፣ ከአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ እና ከሰመራ ዩኒቨርስቲ ጋር በጋራ የተሰራ መሆኑን አመላክተዋል።

ጥናቱም ዩኒቨርሲቲዎችን ከሚገኙበት አካባቢ ጋር በማገናኘት የተካሄደ ሲሆን፣ በሀዋሳ ከተማና በዙሪያው ከሀዋሳ ዩኒቪ.ርስቲ፤ በጅማ እና አካባቢውም ከጅማ ዩኒቨርስቲ፤ በድሬዳዋ አካባቢ ከድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ፤ አፋር አካባቢ ከሰመራ ዩኒቨርስቲ፤ በባህርዳር አካባቢው ከባህርዳር ዩኒቨርስቲ እንዲሁም በአዲስ አበባ ከአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመሆን ብዙ ቦታዎችን ባማከለ መልኩ የሀገር አቀፍ የምርታማነት ጥናት መካሄዱን ጠቁመዋል።

የጥናቱ ዋነኛ ግብ ሠራተኞች ሳይት ላይ በሚውሉበት ሰዓት ምን ያህል የስራ ሰዓቱን ሥራው ላይ ያውላሉ የሚለው የተካተተበተ ነው። ይህም በአንድ ፈረቃ ሲሰራ ስምንት ሰዓት ይሰራል ተብሎ የሚታሰብ ቢሆንም ከስምንት ሰዓቱ ውስጥ ቀጥተኛ አስተዋፅኦ ያለው ስራ መስራት፣ የማቴሪያል ግብዓቶችን ማጓጓዝ፣ ያለስራ መንቀሳቀስ፣ ተጨማሪ ስራዎችን ለመስራት የሚያስችሉ መረጃዎችን መጠየቅ በሚሉ ዘርፎች የተከፋፈሉ ቼክሊስቶች ያሉት ነው። በእነዚህ ቼክሊስቶች ውስጥም አንድ ሠራተኛ ይጠናል። በዚህ መሰረት ኢንስቲትዩት በሙከራ ደረጃ ባደረገው ጥናት በአማካይ 40 በመቶ ብቻ ቀጥተኛ ውጤት ባለው ስራ ላይ ይውል እንደነበር መታየቱን ጠቁመዋል። ይህም በቀጣይ የሠራተኞች አካባቢ በመፈተሽ ቀጥተኛ ውጤት ያለው ስራ እንዲጨምር በማድረግ የግንባታ ሂደቱን ምርታማነት ማሻሻል ያስችላል።

አሁን ላይ ጥናቱ ያለበትን ደረጃ በተመለከተ ዳይሬክተሩ እንደገለጹት በየምዕራፉ የተሰራ መሆኑን ነው። እሳቸው እንዳሉት፤ የሙከራ ጥናቱ ተሰርቶም ከባለድርሻ አካላት ጋር ለምክክር ቀርቧል። የተገኘው ጠቅላላ ውጤት ለኢንዱስትሪው ተደራሽ ተደርጓል። የአገር አቀፉ የህንፃ ስራዎች ጥናትም በማጠናቀቅ ከባለድርሻዎች ጋር ምክክር በማድረግ እና ተጨማሪ ግብዓት በማከል የጥናቱ ሰነድም በዋናነት ለኮንስትራክሽን ስራዎች ቁጥጥር ባለሥልጣን እና ለሚኒስትር መስሪያቤቱ በመላክ ለሁሉም የኢንዱስትሪው ተጠቃሚዎች ተደራሽ የሚሆንበት ሂደት ደርሷል። ስራዎቹ በየደረጃው በተጠናቀቁ ቁጥርም ለኢንዱስትሪው ተደራሽ የሚደረጉ መሆኑን ጠቁመዋል።

ይህንን ጥናት ተከትሎም የመንገዱን ዘርፍ ለማጥናት እና የመነሻ ሰነዶችንም ለማዘጋጀት በዋነኛነትም ፕሮጀክቱ የሚመራው በመንገዶች አስተዳደር ስር በመሆኑ እና በእነሱም በኩል ተነሳሽነት እንዳለ ዳይሬክተሩ ይገልጻሉ። የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር በከተማ እና መሰረተ ልማት ስር አቻ ተጠሪ ተቋም በመሆኑ ይህንን ስራ ቢያከናውኑት ይሻላል በሚል የመንገዱን ዘርፍ መነሻ ጥናቱን ለመንገዶች አስተዳደር መስጠቱን አመላክተዋል።

የውሃ ነክ ስራዎች ጥናትንም በ2016 እና 2017 ዓ.ም ለመስራት በሂደት ላይ መሆኑን ጠቁመው፤ ይህንን በማድረግም ቢያንስ የህንጻውን የውሃ እና የመንገድ ዘርፉን ያማከለ ሀገር አቀፍ የኮንስትራክሽን ምርታማነት የሰው ኃይል እና የማሽነሪ ምርታማነት ማሻሻል የሚረዳ ጥናት ታሰቦ እየተሰራ መሆኑን ጠቁመዋል። አሁን የተጀመሩት የውሃ ስራዎች ዘርፍ ጥናቱም ሲጠናቀቅ በተመሳሳይ ለኢንዱስትሪው ተደራሽ የሚደረግ መሆኑን ዳይሬክተሩ ተናግረዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የዓባይ ግድብን ስናስብ - ስኬቱን ማሳቅ፣ ምስጋና የሚገባቸውንም ማመስገን ይገባል!

መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም በኢትዮጵያውያን ልብ ውስጥ ከፍ ያለ ስፍራ ከሚሰጣቸው ዕለታት አንዱ ነው። ምክንያቱም ቀኑ ኢትዮጵያውያን አስበው የሚቀሩ ሳይሆን ያሰቡትንም ማድረግ እንደሚችሉ የገለጡበት፣ ማድረግ መቻላቸውም በሰው ትከሻ ሳይሆን በራሳቸው አቅም መሆኑን ያረጋገጡበት ክስተት የተፈጸመባት በመሆኑ ነው።

ይሄውም ዓባይን ከስደተኝነት ወደ ቤተኝነት የለወጠ፣ ለሀገሩ ልጆች ብርሃንን እንዲያበረክት ያስገደደ፣ የቀደሙት መሪዎች ሕልምና ምኞትን ወደ ተጨባጭ እውነት እንዲቀየር ያደረገው - የዓባይ ግድብ ግንባታ የመሠረተ ድንጋይ ተቀምጦ ሥራው የተጀመረበት ዕለት በመሆኑ ነው።

ዓባይ ከወንዝነት ወደ መብራትነት እንዲቀየር ታስቦም፣ ታቅዶም፣ ለሥራው የሚሆን በርካታ ዝግጅት ተደርጎም የነበረው በቀደመው ጊዜ ነበር። በተለይ አፄ ኃይለሥላሴ በአሜሪካ ባለሙያዎች አስጠንተውና ዲዛይን አሠርተው ወደ ተግባር ለመግባት ባቀዱበት ወቅት፣ አጋዥና ደጋፊ የሚሆን የውጪ አጋር በመጥፋቱ ሀሳባቸው ሳይሰምር ቀረ።

በኋላም በራስ አቅም ለመገንባት ሕዝቡን አስተባብሮ አቅም ለመፍጠር ሞክረውም ነበር። ይሄም በወቅቱ በነበረው የኢኮኖሚ አቅም የሚሞከር ባለመሆኑ አልተሳካም። እናም ሀሳብና ንድፋቸው እንዳይባክን፣ ከፍ ያለ መሻታቸውን ትውልድ በጊዜው ጊዜ እንዲፈጽም በጥንቃቄ እንዲቀመጥ አዘዙ።

በኋላም በደርግ ዘመን ይሄው ታስቦ የነበረ ቢሆንም በወቅቱ ዘርፈ ብዙ ችግር ምክንያት ሳይሳካ ቀረ። በዘመነ ኢሕአዴግም ከብዙ ቆይታ በኋላ ጉዳዩን መተግበር ወደሚያስችል ዝግጅት ተገባ። እናም የአባቶች አደራ፣ የመሪዎች የዘመናት መሻት ወደ ተጨባጭ እውነት ተቀየረ።እናም በዓባይ ወንዝ ላይ የዓባይ ግድብን ገንብቶ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት የሚደረገው ጉዞ ጅማሮውን አደረገ።

ይሄ የመጀመር ወቅት ነው። ሃሳብንና ንድፍን ወደ ተግባር የመለወጥ ጊዜ። በኋላም ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ ፕሮጀክቱ በልዩ ትኩረት እንዲከናወን አቅጣጫ (በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) አማካኝነት) ተቀመጠ። በዚህ ወቅት ታዲያ ግድቡ በተጀመረበትና ከግማሽ በላይ ግንባታው በተከናወነባቸው ከለውጥ በፊት ዓመታት የነበሩ መልካም ነገሮች እንዲቀጥሉ የተደረገበት ብቻ አልነበረም።

ይልቁንም የነበሩ ችግሮች በተለይም የፕሮጀክቱ አፈጻጸም ላይ ከፍ ያለ ጫና ሲያሳደሩ የነበሩ አካሄድና አሠራሮችን አርሞ የማስተካከል እርምጃም የተወሰደበት ነበር። በዚህም ፕሮጀክቱን የነበሩበት ችግሮች ተፈትተው ወደተሟላ መስመር እንዲገባ ማድረግ ተችሏል።

ከዛም በላይ ለዘመናት ይናፈቅ የነበረው የውሃ ሙሌት፣ እንዲሁም የተርባይኖች ገጠማና ኤሌክትሪክ የማመንጨት ሥራዎች በተከታታይ ተሠሩ። በዚህም ዛሬ ላይ የግንባታው አጠቃላይ አፈጻጸም 94 በመቶ መድረስ ከመቻሉም በላይ፣ በቀጣይ ሰባት ወራት ውስጥ ግንባታው የሚጠናቀቅ ስለመሆኑም ነው የተገለጸው። በመሆኑም ይሄኛው ዘመን የመጨረስ/የማጠናቀቅ ዘመን ነው ማለት እንችላለን።

በዚህ ሁሉ ሂደት ሁለት ነገሮችን በልዩነት ማንሳት ይገባል። አንዱ የማድረግ አቅምና ስኬታማነት የተገለጠበት እውነት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ለስኬታማነቱ ዋጋ የከፈሉ አካላት በመኖራቸው እነዚህን አካላት ስለ ሁሉም አበርክቷቸው ክብርም፣ ዕውቅናና ምስጋና መስጠት የተገባ መሆኑን ነው።

ከማድረግ አቅምና ስኬታማነት አኳያ፣ ኢትዮጵያ በዘመናት ጉዞ ውስጥ ያላትን ነፃነትና ሉዓላዊነት የሚመጥን የኢኮኖሚ አቅም በእጅጉ ያስፈልጋት ነበር። ከዚህ አኳያ የዓባይ ግድብ ከፍ ያለ ትርጉም ያለው ነው። ምክንያቱም አይችሉም ሲባል መቻልን፣ አይፈጽሙም ሲባል ፈጽሞ ማሳየትን፣ አይጨርሱም ሲባል ጨርሶ ማሳፈርን፣... ለወዳጅም ለጠላትም በሚታይ መልኩ መግለጥ ችለናል።

በዚህም ኢትዮጵያውያን ለነፃነታቸው ምሉዕነት ያላቸውን ቁርጠኝነት፣ ያላቸውን አቅምና የማድረግ ልክ በዓባይ ግድብ አማካኝነት አሳክተው አሳይተዋል። እናም የዓባይ ግድብ የኢትዮጵያውያን የማድረግ አቅም መለኪያ፣ ሀሳብን ለተግባር፣ ተግባርንም ለፍጻሜ የማብቃት የውጤት ሰገነት ሆኖ የሚነገር ነው። በመሆኑም ይሄንን ውጤት በልኩ መግለጥም፣ በሌሎች ላይ አልቆ መድገምም የቀጣይ የቤት ሥራ አድርጎ መውሰድ ይገባል።

በሌላ በኩል ለግድቡ ለዚህ ስኬት መብቃት በርካታ አካላት የበኩላቸውን አበርክተዋል። መሪዎች ሀሳብ አመንጭቶ እስከ ማስፈጸም የደረሰን ተግባር በየዘመናቸው ከውነዋል። ሕዝቦች ያላቸውን ሳይሰስቱ ሰጥተዋል። ዲፕሎማቶች ከፍ ያለ የዲፕሎማሲ ሥራን ከውነዋል። ተደራዳሪዎች በሀገር ፍቅርና እውቀት ታግዘው የኢትዮጵያን ጥቅም ያስከበረ ተግባርን ፈጽመዋል። ምሑራን፣ ታዋቂና ተፅዕኖ ፈጣሪ ዜጎች ስለ ሀገራቸው ድንበርና የፖለቲካ እሳቤ ሳይበግራቸው ተሟግተዋል። ባለሃብቶች ያለ ስስት ካዝናቸውን ከፍተዋል። ሌሎች በሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖችን የቦታው ሀሩር ሳይበግራቸው ላብና ደማቸውን ጭምር ሰጥተው ግድቡን ገንብተዋል።

በዚህ ሁሉ ሂደት ሃሳብና ድካማቸው ለሀገርና ሕዝብ ከፍታ እንደመሆኑ፣ ሀሳብና ንድፍ አኑረው ላለፉም፣ ሃሳብና ንድፉን ተቀብለው ላስጀመሩም፣ ጅምሩን አርመውና አልቀው ወደ ፍጻሜው ጫፍ ላደረሱም መሪዎች ምስጋና መቸር የተገባ ነው። ከዚህ ባለፈ፣ በሃብት ማዋጣት፣ በዲፕሎማሲው፣ በድርድሩም፣ በሚዲያና ኮሙኒኬሽኑም፣ እንዲሁም በብዙ ፈተና ውስጥ ሆነው በቀጥታ በግንባታው ሂደት ለተሳተፉ ሁሉ ምስጋና የተገባ ነው።

ምክንያቱም ውጤታማነትን መግለጽና አልቆ ማስቀጠል አንድ ተግባር ሆኖ፣ ይሄንን ማስቀጠል የሚቻለው ውጤት ለመገኘቱ ምክንያት የሆኑትን ሁሉ ማክበር፣ ማመስገንና እውቅና መስጠት ሲቻል ነው። በመሆኑም ስለ ዓባይ ግድብ ስናነሳም፣ 13ኛ ዓመቱን ለማክበር ስንሰናዳም፣ በዘመናት ሂደት ውስጥ ለግድቡ ከሃሳብ እስከ መፈጸም አበርክቶ የነበራቸውን አካላት እያመሰገንን፣ ለላቀ ኃላፊነትም እያበቃን ሊሆን ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ:- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ለመሞሸር እየተዘጋጀች ያለች ከተማ

**ምሕረት ሞገስ**

ሰማይ ጠቀስ ሕንፃዎች ጎልተው ያስዋቧትን የዓለም ምርጧን ከተማ ማየት ከምንም በላይ ያስደስታል፡፡ በተንጣለሉት ፓርኮቿ መዝናናት ማንንም የሚማርክ ነው። በዓለም ያለ ሰው በሙሉ ሊመለከታት ይጓጓል፡፡ በዓለም ላይ ከሚገኙ ምርጥ ከተማዎች መካከል የአንደኝነት ደረጃን ተቆናጥጣለች። የአሜሪካዋ ኒዮርክ ከተማ (New York City)። ስምንት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ሕዝብ ይኖርባታል። ነገር ግን የሰዎች ብዛት ሲያስጨንቃትና ሲተራመስባት ፈፅሞ አይታይም፡፡

የዓለም ትልልቅ ግብይቶች እና የፋይናንስ እንቅስቃሴዎችም ይደረጉባታል። አኗኗራቸው እጅግ ዘመናዊነትን የተላበሱ ሰዎች መቀመጫ ነች። ኒዮርክ እአአ በ1898 እንደተመሠረተች መረጃዎች ይጠቁማሉ ፡፡ ከኒዮርክ ቀጥሎ በዓለም ካሉ ምርጥ ከተማዎች ከሚጠቀሱት መካከል የምትመደበው ደግሞ የዩናይትድ አረብ ኤሜሬትሿ ዱባይ ነች። እአአ በ1971 ከብሪታኒያ ቅኝ ግዛት ተላቃ እንደተመሠረተች መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ከሁለቱ ከተማዎች በተጨማሪ ለንደን፣ ፓሪስ፣ ቶኪዮ እና ሌሎችም ከተሞችም በተለያየ መልኩ በምርጥ ከተማነት ተመራጭ ናቸው፡፡

በተቃራኒው የኢትዮጵያ ዋና ከተማና የአፍሪካ መዲና የሆነችው አዲስ አበባ ከተቆረቆረች አንድ ክፍለ ዘመን ተሻግራ ሁለተኛውን አጋምሳለች። ይሁን እንጂ ለዘመናት ባረጁና በዛጉ (በተለምዶ ቸኮሌት ቀለም የያዙ የሚል ስያሜ ያላቸው) ጥቋቁር ቆርቆሮዎች አናታቸውን የተሸፈኑ የጭቃ ደሳሳ ጎጆች ታጭቃ ዕድሜዋን ገፍታለች፡፡ ከፕላን ውጪ በተሠሩ መኖሪያዎች፣ ምቹ ባልሆኑ መሠረተ ልማቶች እንዲሁም በሌሎች ውስብስብ ጉዳዮች ለዘመናት ዘመናዊነትን ሳትላበስ ቆይታለች። በዚህ እና በሌሎች ምክንያቶች ሳቢያ ለጉብኝት የማትመች ከተማ ተብላ ተቀምጣለች፡፡ በመግቢያችን ላይ ካነሳናቸው ዘመናዊና ቅንጡ ከተሞች አንፃር አዲስ አበባ ብዙ ዘመናትን ወደኋላ እንደቀረች መገመት አይከብድም።

የዓለም ጎብኚዎች ለሚያካሂዱት ጉብኝት ቅድመ ዝግጅት ሲያደርጉ ያላቸው የገንዘብ መጠን ላይ ተመሥርተው ከተሞችን ሲመርጡ፣ አመራረጣቸው ምርጦቹን ከአስቀያሚዎቹ የሚለይ መረጃን በመሰብሰብ ሲሆን፣ ንጹሑን ከቆሻሻው፣ የሚያስደስተውን ከሚያስጨንቀው ለይተው ለጉብኝት ሲሰናዱ አስቀድመው አዲስ አበባን እንደሚሰርዙ ይነገራል፡፡

ምንም እንኳ በገንዘብ እጥረትም ሆነ በአጋጣሚ አዲስ አበባን መርጠው ቢመጡም ቆይተው ብዙ ቀናትን ለማጥፋት ፍላጎት የላቸውም፡፡ አስደሳች እና ውብ አካባቢን እንጂ አስቀያሚ እና የታጨቀ ልክ እንደ አዲስ አበባ የተጨናነቀ በየጥጋ ጥጉ ቆሻሻ የሚተኛበትን ከተማ ለመቆየት ቀርቶ ለማየት አለመምረጣቸው አያስወቅሳቸውም፡፡

ለመዝናናት የሚመች ጥራት ያለው ፓርክ እና የሚጎበኝ ሐይቅ፣ መሠረተ ልማት ሳይሟላ እና አስተማማኝ የጤና አገልግሎትም ሆነ ምቹ መንገድ ሳይኖር፣ ቀንም ሆነ ማታ የደህንነት ስጋት የሚያንዣብብበት ከተማ ምንም እንኳ የአየር ሁኔታው የተመቸ ቢሆንም ተመራጭ እንደማይሆን አያጠያይቅም፡፡

የእኛዋን አዲስ አበባ ከተቆረቆረች 139 ዓመታትን ማለትም ከአንድ ምዕተ ዓመት በላይ ብታስቆጥርም ከምርጦቹ ከተሞች ውስጥ መቆጠር ቀርቶ፣ ለመጎብኘት የምትበቃ ሳትሆን ቆይታለች፡፡ ዘመናትን ከማስቆጠር ባሻገር ምርጥ የአየር ሁኔታ ያላት እንደሌሎች ከተሞች አብዝታ የማትሞቅ አብዝታም የማትቀዘቅዝ ለሰው ልጅ የሚመች የአየር ሁኔታ ባለቤት የሆነችዋ አዲስ አበባ ለመጎብኘት እምብዛም የማትመረጥ ለነዋሪዎችም ምቾት የምትነሳ ከተማ ሆና ቆይታለች፡፡

ከሰሞኑን ግን አዲስ አበባ ቀን እየወጣላት ልትሞሸር መሆኑን የሚያመላክቱ መጠቆሚያዎች እየታዩ ናቸው፡፡ ለሦስት አስርት ዓመታት አካባቢ ያለምንም ሥራ በቆርቆሮ ታጥሮ የነበረው የአዲስ አበባ እምብርት አሁን ግን የአባት አርበኞችን ተጋድሎ የሚዘክር የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም ተገንብቶበት ለጉብኝት በሚያመች መልኩ የአዲስ አበባ መገለጫ ለመሆን በቅቷል፡፡

ከሙዚየሙ በተጨማሪ በወንዝ ዳር ልማትም የአዲስ አበባ ከተማ ቆሽሾ እንዲታይ፣ ሰዎችም በቆሻሻ ቦታ ላይ በመኖር ሕይወታቸውን በበሽታ እየተሰቃዩ እንዲያሳልፉ የሚያስገድዱ አካባቢዎችም እየፀዱ ነዋሪዎቹም ወደ ፅዱ አካባቢዎች እንዲንቀሳቀሱ እየተሠራ ነው፡፡ ይህ አንዳንድ

> **ለውጥ ለአንዳንዶች ደስታ ለአንዳንዶች ደግሞ ጊዜያዊ ጭንቀት ቢኖረውም ጊዜው የሚመጥነውን ለውጥ ተከትሎ ራስን ማዘጋጀት ደግሞ የግድ ነው**

አካባቢን ብቻ ሳይሆን ከተማን የማፅዳት እና ውብ የማድረግ ሥራ የከተማው ሕዝብ ላይ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የሀገር ገፅታ ግንባታ ላይ የሚፈጥረው በጎ ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው፡፡

የከተማዋ መሞሾርም ሆነ መዋብ በጎብኚዎች ተመራጭ እንድትሆን ማስቻሉ መንግሥትን ብቻ ሳይሆን በዋናነት የከተማዋን ነዋሪ ተጠቃሚ የሚደርግ ነው፡፡ ጎብኚዎች መጥተው ለእያንዳንዱ አገልግሎት ማለትም ሆቴል እና የእንግዳ ማረፊያ ማከራየትን ጨምሮ ምግብ እና መጠጥ የመሳሰሉትን አገልግሎት በከተማው ውስጥ መሸመታቸው፣ የትራንስፖርት አገልግሎት እና ሌሎችም የመዝናኛ አገልግሎቶችን የሚያቀርቡ የከተማዋ ነዋሪዎች ገንዘብ እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

የገንዘብ መገኘት የከተማዋን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ለማሳደግ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡ ይህ የከተማው ሕዝብ ገቢ የማግኘት ሁኔታ የነዋሪው የሕይወት ደረጃ ከፍ እንዲል የሚያግዝ ይሆናል፡፡ ገቢው ያደገ ሕዝብ በምቹ ሁኔታ የመኖር ዕድሉ ሰፊ ነው፡፡ በመሆኑም አሁን ላይ የከተማ አስተዳደሩም ሆነ የፌዴራል መንግሥት አዲስ አበባን ለማስዋብ እያደረገ ያለው ጥረት በነዋሪው ሕዝብ የሚደገፍ እንደሆነ አያጠያይቅም፡፡ የተዋበ እና ምቹ ገቢን የሚሳድግ እና ማኅበረሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርግ አካባቢን ማን ይጠላል?

ቀደም ሲል አዲስ አበባ በተለይም አራት ኪሎ አካባቢ ምን ይመስል እንደነበር የኖረበት ብቻ ሳይሆን ሲያልፍ የጎበኘ ሰውም ብዙ ሊል ይችላል፡፡ ምቹ የሆነ መፀዳጃ ቤት እንኳ በቅጡ የማይገኝበት፣ በአንድ ክፍል ቤት ውስጥ ቆጥ ተሠርቶ አምስት እና አሥር ሰው ታጭቆ የሚኖርበት፣ መራመጃ መላወሻ ያልነበረበት አካባቢ ነበር።

አሁን ግን አብርኆትን የመሰለ ትልቅ ቤተ መጽሐፍት እና ወዳጅነትን የመሰለ ፓርክ ተገንብቶበት የድሮው ቦታ ፍፁም ተቀይሯል። በተጨማሪም የልጆች መጫወቻን ያካተተ አካባቢ ሆኖ ለከተማዋ ውበትም ለነዋሪው ምቾት ሆኗል። እንደቀድሞ አካባቢውን አይቶ መጨነቅ ሳይሆን መንፈስን ማደስ ከተጀማመረ ቆይቷል፡፡

ሰሞኑን ደግሞ ፒያሳ ዶሮ ማነቂያ አካባቢን ጨምሮ፣ አራት ኪሎ አካባቢ እና ሌሎችም በወንዝ ዳርቻ አካባቢዎች ያሉ መንደሮችን በማፅዳት በአዲስ መልክ የማስዋብ ሥራ እየተከናወነ ነው፡፡ ይህ ሥራ ምንም እንኳ ያለምንም እንከን እየተከናወነ ነው ብሎ በድፍረት ለመናገር ቢያስቸግርም፣ በከፍተኛ ጥረት እና ቅንጅት ሃያ አራት ሰዓት የሥራ ዘመቻ በማካሔድ በፍጥነት አካባቢዎቹ እጅግ የተዋቡ እንዲሆኑ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ በእዚህ ሒደት የከተማ አስተዳደሩ በቻለው አቅም ከአካባቢው ላይ የሚነሱ ነዋሪዎችን ምትክ ለመስጠት እያደረገ ያለው ጥረት በተመለከተ ብዙዎች መልካም መሆኑን በመግለፅ ላይ ይገኛሉ፡፡

ለውጥ ለአንዳንዶች ደስታ ለአንዳንዶች ደግሞ ጊዜያዊ ጭንቀት ቢኖረውም ጊዜው የሚመጥነውን ለውጥ ተከትሎ ራስን ማዘጋጀት ደግሞ የግድ ነው፡፡ ጊዜያዊ ጭንቀትን በመፍራት ሁሉም ነገር ዘለዓለም እንደነበረ እንዲቀጥል መፈለግ፣ መመኘትም ሆነ ባለፈ ጊዜ ላይ ተጣብቆ መታደስ የለበትም ማለት ሞኝነት ነው፡፡

መንግሥት ከዓለም ጋር ተወዳዳሪ ሆኖ የዓለምን ትርፍ በቱሪዝምም ሆነ በሌላ መንገድ ለማግኘት የሚደርገውን ጥረት ለማደናቀፍ መሞከርም ‹‹ኢትዮጵያዊ ነኝ ሀገሬን እወዳለሁ ›› ከሚል ዜጋ የሚጠበቅ አይደለም፡፡ በእኔ በኩል አሁን የተጀመረው የልማት ሥራ ሲገባደድ ከተማችን እጅግ ያማረችና በጎብኚዎች ተመራጭ የሚያደርጋት ገፅታን እንደሚያላብሳት አምናለሁ። ሰላም!

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተተገሩት ያዝናሉ፤ ካሳቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

# ያልፈዘዘው የሕይወት ንቅሳት

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

ማንም በዓይነ ህሊናው ዓመታትን ወደኋላ ቢቃኝ በዘመኑ የነበራቸውን ድንቅ ውበት መገመት ይቻለዋል።ዛሬም ከዕድሜ ማምሻቸው ቆመው ይህ አይፈዜ ውበት ከእሳቸው ጋር ነው። ከዚህ ማንነት ጀርባ ደግሞ መልካም አንደበትና በግልጽ የሚስተዋል ብርታት መገለጫቸው ሆኗል።

ዛሬ ዕድሜ ከሕመም ተባብረው ቢፈትኗቸውም ሴትየዋ የዋዛ አይደሉም። ንግግራቸው በምክንያት፣ ጨዋታቸው፣ በለዛ ነው።ሁሌም ላመኑበት ጉዳይ በቀላሉ እጅ አይሰጡም።ስሜታቸው አይሸሽግም።ግልጽነታቸው፣ ቁጣ ሳቃቸው ከፊታቸው ይነበባል።

አሁን ትናንትን በነበሩበት ሕይወት ላይ አልቆሙም። ‹‹ነበር›› ይሉት ታሪክ ዘመናትን ደራርቦ ከኋላቸው ቀርቷል። ዛሬም ግን ለሚወዱት ሙያና ለእናት ሀገራቸው የሚሰጡት ክብር በእጅጉ ከፍ ያለ ነው። በእነዚህ እውነታዎች ውስጥ ደግሞ ብዙ ሀቆች አሉ። በእነዚህ ሀቆች ውስጥ ጥንካሬና ብርታት፣ ደስታና ሀዘን፣ መውደቅና መነሳት ደምቀው ተስለዋል።

ከሲስተር የትናየት በቀለ ጋር የነበረኝ ቆይታ በልዩ፣ መደመም የተሞላ ነበር። በውስጠታቸው ካየሁት ብርታት ባሻገር ከአንደበታቸው የሰማሁት እውነት በእጅጉ አስገርሞኛል። ድንቅ የሀገር ታሪክና አይረሴ ትዝታዎችን ተረኩልኝ።ውቧን ወይዘሮ አለማድነቅ አልቻልኩም። ለስንብት በክብር እጄን እስከዘረጋ በአድናቆት አብሬያቸው ልዘልቅ ግድ አለኝ።

**1930 ዓ.ም በኬንያ ሰማይ ስር ...**

ወቅቱ ወራሪው የኢጣሊያ ጦር ወደ ኢትዮጵያ የገባበት ክፉ ዘመን ነው። የዛኔ ሀገራቸውን ከጠላት የሚታደጉ ጀግኖች በዱር በገደሉ፣ በጫካ በዱሩ በቆራጥነት ይዋደቁ ነበር።‹‹እምቢኝ›› ባይነታቸው፣ ነፃነታቸውን እስኪያነጋ መከራን የከፈሉ፣ የሞት ጽዋን የተጎነጩ፣ ሙሉ አካላቸውን አጥተው ሀብት ንብረታቸውን የበተኑ ዕልፍ ናቸው።

1930 ዓ.ም የኢጣሊያ ጦር በማን አለብኝነት ኢትዮጵያን ይዞ ግዛቱን ሊያሰፋ፣ የሚሮጥበት ወሳኝ ጊዜ።ሁለት ዓመታትን ያስቆጠረው ተጋድሎ ትግሉ ተፋፍሞ ቀጥሏል። እነዚህን የጭንቅ ጊዚያት ለመሸሽ አጋጣሚውን ያገኙ ጥቂቶች ሀገር ጥለው ተሰደዋል።ባህር ቆርጠው፣ ወንዝ ተሻግረው ርቀዋል።

አቶ በቀለና ቤተሰቦቻቸው ቤት ንብረታቸውን ትተው የኬንያ ምድርን በስደት ይኖሩባት ከያዙ ጊዚያት አስቆጥረዋል።የሰው ሀገር ሕይወት እንደራስ አይሆንም።ትዝታው፣ ናፍቆቱ ይፈትናል።ሀገር፣ ወገን በጦርነት ሲያዝ፣ በጠላት ሲወጋ ደግሞ ሕመሙ ከባድ ነው።

በሰው ሀገር ደርሶ ሆድ ይብሳል፣ ሳቅ ፈገግታ ብርቅ ነው።ደስታና ፌሽታ ሩቅ ነው።ሁሌም ልብ ካለበት ኮብልሎ ይሄዳል፣ ዓይን ዕንባን ይሞላል።የሀገር ምድር ችግር ፣ የወገን እልቂት ጥቃቱ ያስቆጫል፣ ደም ያስነባል፣ ይህ እውነት ለመላው ቤተሰብ አይሽሬ ቁስል ከሆነ ውሎ አድሯል።

ከቀናት በአንዱ በኬንያ ሰማይ ስር እንዲህ ሆነ።ሐምሌ 30 ቀን 1930 ዓም። ነፍሰ ጡሯ የአባወራው ሚስት በድንገቴ ምጥ ተያዙ።አሁን ሌላ የሰው ሀገር ሰው ሊታከል ነው።ደቂቃ ሰዓታት ተቆጠሩ።ምጥ በረታ።ወዳጅ ዘመድ ጭንቅ ገባ። ጥቂት ቆይቶ ፣ ሃሳብ በዕልልታ ተተካ። ይህችን ዓለም በለቅሶ የተቀበለች አንዲት ቆንጆዬ ጨቅላ የአቶ በቀለን ቤተሰብ በእንግድነት ተቀላቀለች።

የአዲሷ ልጅ መወለድ በቤተሰቡ ዘንድ ታላቅ ደስታ አሰፈነ። ዘመኑ ለኢትዮጵያውያን የጦርነትና፣ የመከራ ጊዜ ነው።በዚህ መሀል የመጣው የምስራች ስጋት፣ ሀዘኑን አሸንፎ እፎይታን አላብሷል። በሰው ሀገር ለዛውም በስደት ለተወለደችው ድንቅዬ ስጦታ ወላጆቿ ስም መረጡ፣ አማረጡ።



ፎቶ፡- ገበዙ ገብሬ

ሲስተር የትናየት በቀለ

ከስያሜዎቹ መሀል አንደኛው ሚዛን ደፍቶ አሸነፈ። ሀገር ምድሯን ርቃ በባዕዳን መሀል የተወለደችው ብላቴና ‹‹የትናየት›› ተብላ ተሰየመች። ትንሽዋ የትናየት በኬንያዋ ‹‹ታቤታ›› ምድር ‹‹ዳዬ›› ብላ ልጅነቷን ጀመረች። ወላጆቿ በስስት እያዩ እስከ ሶስት ዓመት አሳደጓት። ከሶስት ዓመታት በኋላ ወራሪው የኢጣልያ ጦር ከኢትዮጵያ ምድር በሽንፈት ተዋርዶ መባረሩ ተሰማ።ይህ በመላው ዓለም የተዳረሰ አኩሪ ዜና ለጥቁር አፍሪካውያን ኃያል ብርታት ሆነ።ኬንያን ጨምሮ ሌሎች ሀገራትን ለነፃነት ትግል አነሳሳ።

የየትናየት ቤተሰቦች ከድል ማግሥት ሀገራቸውን ናፈቁ።ጊዜ አልፈጁም። በስደት የቆዩባትን ኬንያን ተሰናብተው ወደ እናት ምድራቸው አመሩ።ሕይወት በአዲስ መልክ ተጀመረ። ‹‹ጨርቄን፣ ማቄን›› ሳይሉ የሀገራቸውን ምድር ረገጡ። በወቅቱ የየትናየት አያት ወደ ሀገራቸው ሲገቡ ብቻቸውን አልሆነም።ስደተኛውን የመድኃኔዓለም ታቦት አስከትለው ነበር።

አዲስ አበባ ሲደርሱ ስድስት ኪሎ እቴጌ መነን ትምህርት ቤት አካባቢ ከሚገኝ ቦታ ታቦቱን በክብር አስቀመጡ።ቦታው የንጉሳውያን ቤተሰቦች ርስት የነበረ ሰፊ ሜዳ ነው።ውሎ አድሮ በዚሁ ስፍራ ቤተክርስቲያን ታነጸ ። ‹‹ምስካየ ኅዙናን ›› መድኃኔዓለም የሚል ስያሜ ተችሮትም ምዕምናንን አሰባሰበ።ዛሬም ድረስ ያንን ክፉ ዘመን የሚዘክረው የስደተኛው መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን በክብር እንደቆመ ይገኛል።

**ሕይወት ከድል ማግስት ...**

የየትናየት ወላጆች ከድል ማግስት በአዲስ አበባ ኑሮን ቀጥለዋል።አባት ለዘመኑ ሥልጣን ቅርብ ነበሩና በሹመት ወደ ሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት ሊሄዱ ተዘጋጁ።ቀሪው ቤተሰብ በቤት መቆየት ነበረበት። የአባወራው ባለቤት ከእናታቸው ጋር አዲስ አበባ እንዲቀመጡ ሆነ።የትናየት ከአባቷ መነጠል አልፈለገችም። እሳቸውን ተከትላ ሐረር ለመሄድ ጓዟን ሸከፈች።

የትናየት ለአባቷ የተለየ ፍቅርና አክብሮት አላት።በየደረሱበት አብራቸው ብትሄድ፣ ኑሯቸውን ብትጋራ ትወዳለች።በወቅቱም ይህ ውሳኔ ከእሷ ነበር።ሐረርጌ አባቷን ተከትላ ሃሳቧን መፈጸም።አባትና ልጅ ከልብ ይዋደዳሉ። እሳቸው ሥራ ውለው ሲገቡ ዓይኗን ማየት ይናፍቃሉ፣ በሰስት እያስተዋሉ ራሷን ይዳስሷታል።ይህ የዘወትር ልምዳቸው ነው።

ሐረርና የትናየት ዓመታትን በአብሮነት አሳለፉ። በከተማዋ የልጅነት ዓለሟን ቀጨች። የወጣትነት ዕድሜዋ አብቦ እስኪታይ ሕይወቷን በነፃነት ተራመደች።አባት በተሻለ ሹመት ዳግም አዲስ አበባ እስኪመለሱ ከጎናቸው አልራቀችም።የሐረርን ብርቱካን ከአባቷ ጣፋጭ ፍቅር ጋር እያጣጣመች አብራቸው ዘለቀች።

አባት አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ የአፄ ኃይለሥላሴ ዓይን አረፈባቸው። ንጉሡ። ለምክርና ለአስፈላጊ ሥራዎች ሁሉ ከጎናቸው ቢሆኑ ምርጫቸው ነው።ይህ ዓይነቱ አጋጣሚ ከቤታቸው እያራቀ ጊዚያቸውን መሻማቱ አልቀረም። ይህ ዘመን ለሴቶች ቀርቶ ለበርካታ ወንዶች ጭምር ትምህርት ብርቅ የሆነበት ጊዜ ነበር።

የትናየት ግን ሴትነቷ አላሸነፍትም። በዘመኑ በነበረው እቴጌ መነን፣ ትምህርት ቤት ገብታ በጥንካሬ መማር ጀመረች። ጥቂት ቆይታ ደግሞ ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት መዛወርን ፈለገች። ከሴቶች አዳሪ ትምህርት ቤት ለመውጣት የከለከላት አልነበረም።

በወቅቱ እናቷና አያቷ ዘንድ መቀመጥ ምርጫዋ ሆነ። በትምህርት ቤቱ እስከ አስረኛ ክፍል የዘለቀችው የትናየት ከዚህ በኋላ የነበራት ጊዜ ለሌላ ታላቅ ዓላማ አዘጋጃት።

**1950 ዓ.ም**

በልዕልት ፀሐይ መታሰቢያ ሆስፒታል /የአሁኑ ጦር ኃይሎች/ ለነርሲንግ ትምህርት የታጨችው ወጣት ዕድሉን ባገኘች ጊዜ በአግባቡ ተጠቀመችው። ሙያና ፍላጎት ተጣምረው የውስጧን ዕውቀት ገለጡ።ዕለት በዕለት ጠንክራ በብርታት ሙያውን ቀሰመች። ያሰበችው ተሳካ፣ ዕቅድ ዓላማዋ ዕውን ሆነ።

1950 ዓ.ም የተጀመረውና በውጭ ሀገር ዜጎች የታገዘውን የነርሲንግ ትምህርት በ1953 ዓ.ም በስኬት አጠናቃ ለምርቃት በቃች። ከዚህ በኋላ የነበረው ጊዜ ለእሷ ሥራውን ፍቅዳ ለገባችው ወጣት የተለየ ነበር። የዛኔ አይደለም በሴት ልጅ በብዙኃኑ ወንዶች የማይደፈረው የሕክምና ሙያ በነሲስተር የትናየት መተግበሩ ብርቅ የሚያሰኝ ነበር።

በልዕልት ፀሐይ መታሰቢያ ሆስፒታል ሙያዋን በጥሩ ሥነ ምግባር ያስመሰከረችው ወጣት ውሎ አዳሯን ከልብ ወደደችው። ያለ እንዳች መሰልቸትና መዘናጋት ጊዜና ዕውቀቷን ሰጥታ በሥራዋ አተኮረች። ይህ እውነት ሌላውን ዕድል ለመከፈት አልዘገየም። መልካም ዓይኖች በሲስተር የትናየት ላይ አተኮሩ። የሙያ ፍቅሯና የሥራ ብርታቷ ሚዛን ደፍቶ ይታይ ያዘ።

**እንግሊዝ ለንደን ...**

ሲስተር የትናየት ወርቃማዎቹን የሥራ ዓመታት እንደዘለቀች በአስተዳደሩ ዘርፍ ሙያዋን የሚያጠናክር የትምህርት ዕድል አገኘች። ይህ አጋጣሚ ለእንግሊዝ ሀገር ጉዞ ከታጩት ጥቂት ሴቶች መሀል አንዷ አደረጋት።በዘመኑ ይህ ዓይነቱ ዕድል እንደቀላል የሚታይ አይደለም።ሀገር ቆርጦ፣ ባህር ተሻግሮ፣ ዕውቀትን መቅሰም፣ ለጥቂቶች፣ በጥቂቶች ብቻ የሚሆን እንጂ።

ወጣቷ የትናየት የውጭ ሀገሩን የትምህርት ዕድል ባገኘች ማግሥት በሙሉ ልብና ወኔ ጓዟን ሸክፋ ተነሳች። ከታሰበው ጥግ ለመድረስም ሀገሯን ተሰናብታ ወደ እንግሊዝ ለንደን አቀናች። የእንግሊዝ ሀገር ቆይታዋ መልካም የሚባል ነበር።ከእሷ መሰል የውጭ ሀገራት ዜጎች ጋር ሙያዋን አዳበረች፣ ሰፊ ልምድም ቀሰመች።

በለንደን ከአንድ ዓመት በላይ ያስቆጠረ ቆይታዋ በመልካም እንደ ተቋጨ ከሀገሯ የወሰደ እግሯ መልሶ ወደ እናት ምድሯ አገባት። 1958 ዓ.ም በተሻለ ልምድና ዕውቀት የዳበረ ማንነቷ ዳግም ከልዕልት ፀሐይ ሆስፒታል ሊያደርሳት ግድ አለ።እስከ 1959 ዓ.ም በሆስፒታሉ ሙያዋን በብቃት ተወጣች።ቀጣዩ የሲስተር መንገድ ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል አመራ።

ጥቁር አንበሳ ሆስፒታልና ሲስተር የትናየት ከ1966 ዓመታት ጀምሮ በጥምረት ዘለቁ። ከደርግ መንግሥት እስከ ኢህአዴግ ለውጥ ድረስ ያለመታከት የሠራችው ባለሙያ ዓመታት በጨመሩ ቁጥር ስለሥራዋ፣ ማሰቧ አልቀረም። ያለፈችበት መንገድ ለሙያዋ ክብር የሚሰጥ ፣ ለሕሙማን ሕይወት አብዝቶ የሚጨነቅ ነው።

ከ1959 ዓ.ም በኋላ የየትናየት ሙያ ከነበረችበት ተሻግሮ ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ደረሰ። በስፍራው ተገኝታ የነርስነት ሙያዋን በብቃት ተወጣች። እስከ 1966 ዓ.ም ጥቁር አንበሳ ሆስፒታልና ሲስተር የትናየት ዓመታትን በጥምረት ዘለቁ።

**ትዳርና ልጆች...**

ሲስተር የትናየት ከምንም በላይ ስለሙያዋ ትታገላለች፣ ለእሷ ሕይወቷ ለሰዎች መድረስ፣ ሕሙማንን መፈወስ ነው። እንዲህ መሆኑ ስለግል ሕይወቷ እንዳታስብ ምክንያት ሆኗል። ባልንጀሮቿ በዕድሜያቸው ሲዳሩ ሲኳሉ እሷ እስከ አርባኛ ዓመቷ መዳረሻ ትዳር ይሉትን አላሰበችውም። ውሎ አድሮ ግን ከትዳር አጋሯ ተጣምራ ሶስት ልጆችን አከታትላ ወለደች።

ትዳሯ ብዙ አልዘለቀም። በ1978 ዓ.ም ለፍቺ ብትበቃ የብቸኝነት ሕይወት ግድ አላት።ልጆቹን አባታቸው ዘንድ ትታ ትኩረቷን ሙሉ ሥራዋ ላይ ጣለች።የቤት ኪራይን ሕይወት አየችው። በውጣ ውረዶች ተመላለሰች። እንዲያም ሆኖ አልከፋትም። ትኩረቷ ሁሉ በምትወደው ሥራ ላይ ሆነ። በዚህ መሀል ላፈራችው ቤት ንብረት መታገሏ አልቀረም። አስራ ሶስት ዓመታትን በፍርድ ቤት ምልልስ አሳለፈች። በትዳር መሀል የፈራቸው ሀብት ንብረት ከፍቺና ከባለቤቷ ሞት በኋላ በብዙ አሟገታት።

የትናየት በፍርድ ሂደቱ ደስተኛ አይደለችም። ሚዛናዊ እንዳልሆነ ታምናለች። በእሷ ዕምነት ከአባት ጋር ያደጉት ልጆቿ ጥሩ ነገር ሲሰሙ አልኖሩም። ይህ እውነታም ከእናታቸው ሲያጨቃጭቃቸው ቆይቷል።ከደርግ መንግሥት እስከ ኢህአዴግ ለውጥ ድረስ ያለመታከት የሠራችው ባለሙያ ዓመታት በጨመሩ ቁጥር ስለሥራዋ፣ መጨነቅ ያዘች።

ያለፈችበት መንገድ ላለችበት ሙያና ሙያተኛ ክብር ይሰጣል።በዚህ ዘርፍ ያለፉ አብዛኞች ስለሰው ልጆች መኖር ይጨነቃሉ። ምንጊዜም የእነሱ ግብና ርካታ የታማሚውን ጤና መጠበቅ፣ ሕይወቱን ማትረፍ ላይ ነው።ይህ ዓይነቱ ሀቅ በሲስተር የትናየትና መሰል ባልደረቦቿ ልቦና ውስጥ ደምቆ የተነቀሰ ማህተም ሆኗል።

ሲስተር አንዳንዴ የምታስተውለው ድርጊት ከማንነቷ አልስማማ፣ ከሙያ ቃልኪዳኗ ጋር አልሰምር እያላት ትፈተናለች።ብዙ ጊዜ ውስጧ እየታዘበ ፣ ህሊናዋ እየቆሰለ ልትታገለው ሞከረች። እንዲያም ሆኖ ሥራዋን አልበደለችም።እየቆረቆራትም ቢሆን በመንገዷ ቀጠለች።

አሁን ሲስተር የትናየት በሥራ ደክማለች።የዕድሜዋ መግፋትና የኑሮ አለመመቸት ጤናዋ ላይ ችግር እያመጣ ነው። የትናንቷ ብርቱ፣ የቀድሞዋ ቆንጆ፣ ከሀገሪቱ የመጀመሪያዎቹ ነርሶች ከፊት የምትሰለፈው ጠንካራ ዛሬ እጅ እየሰጠች ነው።ደጋግሞ የሚጎበኛት የእግር ሕመም ፋታ እየሰጣት አይደለም።በየጊዜው ያማታል።

ከቀናት በአንዱ በድንገት ወድቃ ተሰበረች።ሕመሙ በእጅጉ አሰቃያት። በሆስፒታል ተመላልሳ ታከመች፣ ‹‹መንዝ›› ድረስ ሄዳ በወጌሻ ታሸች። ሕመሙ በቀላሉ የሚተዋት አልሆነም።ሲስተር በሕክምናው ሙያ ዓመታትን ዘልቃለች።በራሷ ላይ ያገኘችው ውጤት ግን በተለይ በመንግሥት ሆስፒታሎች እሷ የምታውቀውን ያህል ፍሬማ አልሆነላትም።በዚህ ከልቧ ታዝናለች ።

**ሕይወት በሌላ መንገድ ...**

‹‹የወደቁትን አንሱ›› በተባለው የነዳያን መርጃ ማዕከል ተገኝቻለሁ። ሕይወት በአንድ መንገድ ያገናኛቸው በርካታ ሰዎችን እያየሁ ነው። በአንድ ዊልቸር ላይ የተቀመጡትን መልከ መልካም ወይዘሮ እንደዋዛ አይቼ ማለፍ አልተቻለኝም። ቆንጆ ናቸው። ዕድሜ ቢጫናቸውም ውበታቸው አልተደበቀም። ለሰማንያ ሰድስት ዓመቷ አዛውንትን ቀርቤ በአክብሮት ሰላምታ አቀረብኩ። ‹‹ሲስተር የትናየት በቀለ›› ሲሉ ራሳቸውን አስተዋወቁኝ።

ከሲስተር ጋር ብዙ አወጋን። ጤናቸው በመጠኑም ቢሆን ጥሩ መሆኑን ነገሩኝ። ያለፉበት የኑሮ መንገድ ሻካራማና ጠመዝማዛ ነው። የሕይወት ክፉ አጋጣሚ ከትናንት አሻግሮ ዛሬ ላይ ቢያደርሳቸው በዚህ ስፍራ ሊገኙ ግድ ብሏል።

ከአፄው ዘመን እስከ ደርግ መንግሥት፣ ብሎም እስከ ኢህአዴግ ለውጥ ድረስ ያለመታከት የዘለቀ ጉዞ፣ ሰላሳ ስድስት ዓመታት ፣ ለሙያ ፍቅር የታገለ ማንነት፣ ባሕር ተሻግሮ ዕውቀት የቀሰመ ባለውለታ አዕምሮ፣ እነሆ! ዛሬ በችግሮች ተፈትኖ ከዚህ ተገኝቷል።

# ማረፊያ/ ትዝብት

## የመንገድ መዘጋት ለታክሲዎች ያመቻል!

**ዋስልኝ ልየለ**

ሰሞኑን በብዙ የአዲስ አበባ አካባቢዎች የመንገድ ማስፋፊያ ሥራዎች እየተሠሩ ስለሆነ መንገዶች ተቆፋፍረዋል። በዚህም ምክንያት የትራንስፖርት መጉላላት ተፈጥሯል። በእንዲህ አይነት አጋጣሚዎች የእኛ ሕዝብ ሕገ ወጥ ሥራ ለመሥራት ሰበብ ይፈልጋል። ‹‹የገበያ ግርግር ለሌባ ያመቻል›› እንዲሉ፤ በየሰበብ አስባቡ ዋጋ የሚጨምሩት ባለታክሲዎች ከሰሞኑ ምንም አይነት አግባብነት የሌለው የዋጋ ጭማሪ እያስደረጉ ነው።

አንድ የሥራ ባልደረባዬ የነገረኝን ገጠመኝ እንደ ማሳያ ላድርግ። ከላምበረት መነኻሪያ ወደ አራት ኪሎ ለመምጣት ታክሲ ሲያጣ በአውቶብስ ተራ ታክሲ ገባ። ከላምበረት አውቶብስ ተራ የተለመደው የታክሲ ሒሳብ 25 ብር ነው። ረዳቱ 30 ብር ነው የምትከፍሉት አለ። ለምን? ሲባል አራት ኪሎ መንገድ እየተቆፋፈረ ስለሆነ አለ። ‹‹እና ቢቆፋፈር ርቀቱ ጨምሯል? ወይስ ዳገት ተጨምሮበታል?›› ተብሎ ሲጠየቅ በምኒሊክ ሆስፒታል እንደሚሄድ ተናገረ። ይሄ መስመር ማለት ግን ወደ አውቶብስ ተራ ለመሄድ ብዙ ጊዜ የሚጠቀሙት (እንዲያውም እንደ አቋራጭ የሚጠቀሙት) መንገድ ነው። ግን ማሳበቢያ ይፈለጋል። በዚያው እየተገነባ ባለው መንገድ ላይ እየሄዱ ልክ እንደተለየ ነገር ያዩታል። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ደንብ አስከባሪዎች ምንም አይሏቸውም። ባለታክሲዎችም ሕግ አያከብሩም።

ልብ ብላችሁ ከሆነ፤ ተራ አስከባሪውን ለማናደድ ብለው ወዳላሰቡበት መስመር ይሄዳሉ። ለምሳሌ ከመገናኛ አራት ኪሎ ለመሄድ ያሰበው ታክሲ፤ ተራ አስከባሪውን ያናደደ መስሎት ‹‹አልሄድም›› ይላል፤ ወይም ወደሌላ ቦታ ይጠራል። ሰው ረጅም ሰልፍ ተሰልፎ እያዩ በድብቅ መጫን ያስደስታቸዋል። ከሰልፉ ላይ ቢጭኑ ምን ችግር አለው? ለእነርሱስ ቶሎ ለመሙላት በሥርዓት የተሰለፈው ሰው አይሻልም? ይሄ ብዙ ቀን የታዘብኩት ነው። ለምሳሌ ከአራት ኪሎ ወደ መገናኛ ለመሄድ ሥላሴ ጋ ረጅም ሰልፍ ካለ ሰልፉ ጋ አይጭኑም። ሰልፉን አልፈው ሄደው ይጭናሉ። ከሰልፉ ላይ አንዴ ከመሙላትና አንድ አንድ ሰው ከማንጠባጠብ የቱ ይሻል ነበር?

> ልብ ብላችሁ ከሆነ፤ ተራ አስከባሪውን ለማናደድ ብለው ወዳላሰቡበት መስመር ይሄዳሉ። ለምሳሌ ከመገናኛ አራት ኪሎ ለመሄድ ያሰበው ታክሲ፤ ተራ አስከባሪውን ያናደደ መስሎት ‹‹አልሄድም›› ይላል፤ ወይም ወደሌላ ቦታ ይጠራል

አንዳንዶቹ ደግሞ ቅርብ ቦታ ይጠራሉ። ለምሳሌ ከአራት ኪሎ መገናኛ መሄድ እየቻሉ ‹‹ቀበና›› እያሉ ይጠራሉ። ቀበና ካስገቡ በኋላ ግን የመገናኛ ሒሳብ ተቀብለው ይሄዳሉ፤ ወይም ከቀበና እንደ አዲስ የመገናኛ ይቀበላሉ። የዚህ ታክሲ አሠራር ጥቅም ሊገባኝ አልቻለም። ምናልባት ሰልፍ ሳይዙ የቆሙ ሰዎችን ለመጥቀም ይሆን? እንደ እኔ ተሰፋ ቆርጠው በእግር ለመሄድ ላሰቡት ተብሎ ይሆን? የታክሲ ተራ አስከባሪውስ ይሄን ምስጢር ያውቅ ይሆን? በዚህ ሁሉ ውስጥ ባለታክሲው የሚጠቀመው ነገር ሊገባኝ አልቻለም፤ እንዲያውም የሚባክን ጊዜ ነው ያለው። ቀበና እያለ አንድ አንድ ሰው በማንጠባጠብ ያን ሁሉ ደቂቃ ከማባከን ከሰልፉ ላይ ቢጭን ቶሎ ይሄድ ነበር። ምናልባት ቀበና ከሆነ ለተራ አስከባሪው የምትከፈለዋን 10 (መጠኑን እርግጠኛ አይደለሁም) ብር ለማስቀረት ይሆን? ምክንያቱ እሱ ሳይሆን አይቀርም!

በነገራችን ላይ እነዚህ ነገሮች የሚሆኑት በባለታክሲዎች ጥፋት ብቻ አይደለም፤ በራሳቸው በተራ አስከባሪዎችም ጭምር ነው። የተራ አስከባሪዎች የመከልከል ሥልጣን እስከምን ድረስ እንደሆነ ባላውቅም ባለታክሲዎች እንዲህ አይነት ሥራ መሥራታቸውን ግን በሚገባ ያውቁታል።

እንዲያውም በተራ አስከባሪዎች አስተባባሪነት የሚፈጸም ጥፋት ሁሉ አለ። ለምሳሌ፤ ከመገናኛ ወደ ላምበረት እና 02 የሚጭኑ ታክሲዎች የተለመደው ቦታ ይታወቃል። ዳሩ ግን ይህ የሚሆነው መንገደኛ በሚበዛበት የሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት ላይ ብቻ ነው። ከረፋድ 4፡00 አካባቢ በኋላ ታክሲዎች የሚጭኑት ከተለመደው ፌርማታ ውጭ ነው። ይህ ማለት ትራንስፖርት ባለሥልጣን ከፈቀደው ቦታ ውጭ የታክሲ መጫኛ ሲሆን ደንብ አስከባሪ የተባሉት ዝም ይላሉ ማለት ነው። መንገደኛውም ብዙ ርቀት በእግር ለመሄድ ይገደዳል ማለት ነው። ደንብ አለማስከበራቸው ሳያንስ ይባስ ብሎ ‹‹እዚህ መጫን አይቻልም፤ ክልክል ነው›› እያሉ ያልተፈቀደ ቦታ ድረስ ርቀው እንዲሄዱም ያደርጋሉ፤ ይህ የሚስተዋለው ብዙ ጊዜ ከመደበኛ የሥራ መግቢያና መውጫ ውጭ ባለው ነው። ጠዋት ሲጫንበት የነበረ ቦታ ከረፋድ በኋላ የሚከለከልበት ምክንያት ምንድነው? ባለታክሲዎችስ ተሻግረው ስለጫኑ የሚያገኙት ጥቅም ምን ይሆን? ሒሳቡ ተመሳሳይ ነው። ምናልባት የሚያገናኛቸው ጥቅም ይኖር ይሆን?

ከዚህ ሁሉ በላይ ግን ችግር የሆነው ሰበብ እየፈለጉ ዋጋ መጨመር እና ለዋጋ ጭማሪ ሲሉ መደበኛውን መስመር ትተው ውስጥ ለውስጥ ረጅም ጊዜ የሚያባክኑት። የሥራ ቦታዬ አራት ኪሎ ስለሆነ ምሳሌዎቹ ከአራት ኪሎ ይበዛሉ። ለምሳሌ ከአራት ኪሎ መገናኛ ለመሄድ መንገድ ተዘጋግቷል በሚል ሰበብ ‹‹በ.... ነው የምንሄድ›› ብለው ይናገራሉ። መንገደኛውም አማራጭ ስለሌለው ከታሪፍ ውጭ የተባለውን ከፍሎ ይገባል። ችግሩ ግን ገንዘቡ ብቻ አይደለም። መንደር ለመንደር ሲሽሎከለክ በዋናው መንገድ ቢሄድ ከሚወስደው ሰዓት በላይ ይወስዳል። መንገደኛውም ‹‹በዚያው ይሻል›› ነበር እያለ ከመጉላላት ውጭ አማራጭ የለውም። እንደዚያ መንደር ለመንደር ሲያንከራትት ቆይቶ ዋናው መስመር ሲገባ፤ ከተገነጠለበት ቦታ ብዙም ራቅ ያላለ ይሆናል። ሲሄድ የቆየው ተጨማሪ ኪሎ ሜትሮች ነበር ማለት ነው። በዚህ ሁሉ ውስጥ የብዙዎች ውድ ጊዜ ሲባክን ቆይቷል ማለት ነው።

ይህ አካሄድ ሕገ ወጥ ነው። ምናልባትም የትራፊክ ፖሊስ ለመሸሽም ሊሆን ይችላል። ዋናው ምክንያት ግን ተጨማሪ ለማስከፈል ነው።

እንዲህ በትንሽ ትልቁ ሰበብ የሚፈልጉ ባለታክሲዎች አሁን ደግሞ ሠርግና ምላሽ ሆኖላቸዋል። እንደ እውነቱ ከሆነ እየተሠራ ያለው የመንገድ ማስፋፋት ሥራ ያን ያህል ጉዞ አስተጓጎለ የሚባል አልነበረም። ዳሩ ግን ሰበብ የሚፈልጉት ባለታክሲዎች ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ መጉላላቱን አጣደፉት። ሲፈልጉ በተከለከለ መንገድ ላይ ይሄዳሉ። ሲፈልጉ ደግሞ ያልተከለከለውን መንገድ እንደተከለከለ አድርገው ተጨማሪ ለማስከፈል በሚያመች ሁኔታ ያደርጉታል። በጣም ባስ ሲል ደግሞ ያንኑ መንገድ (መደበኛውን ማለት ነው) አጠገቡ የሆነች ነገር እየተቆፈረች ስለሆነ ብቻ ያለምንም ይሉኝታ ተጨማሪ እናስከፍላለን ይላሉ። ለምን ሲባሉ ያቺን እየተሠራች ያለች ነገር ይጠቅሳሉ። ነገርየው እኮ ከታክሲው ጉዞ ጋር ምንም የማይገናኝ፣ ከተለመደው መዘጋጋት ውጭ ምንም ተጨማሪ ችግር ያልፈጠረ ሊሆን ይችላል።

ስለዚህ ግንባታው ሲሠራ የባለታክሲዎች ነገርም ቁጥጥር ይደረግበት!

# ዓለም አቀፍ

## በዘር ማጥፋት የተጠረጠረው ትውልደ ሩዋንዳዊ በአሜሪካ በቁጥጥር ሥር ዋለ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር 1994 ላይ በሩዋንዳ በተፈፀመው የዘር ማጥፋት ወንጀል ተሳትፏል የተባለ የሩዋንዳ ተወላጅ በአሜሪካዋ ኦሃዮ ግዛት በቁጥጥር ሥር ዋለ።

የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ፣ ኤሪክ ታባሮ ሺሚዬ የተባለውን ግለሰብ ሰዎች እንዲገደሉ ማድረግን ጨምሮ በጅምላ ግድያ የነበረውን ተሳትፎ በመደበቅ ከሶታል።

ሺሚዬ በአሜሪካ በሐሰት ስደተኛ ሆኖ እንዲቆይ ፈቃድ በማግኘቱ ከአውሮፓውያኑ 1995 ጀምሮ በኦሃዮ ኑሮውን ማድረጉን ዐቃቤ ሕግ አስታውቋል።

ግለሰቡ ቀደም ብሎም በዘር ማጥፋት መሳተፉን አስተባብሏል።

ቦስተን በሚገኘው የፌደራል ፍርድ ቤት ይቀርባል ተብሎ ይጠበቃል።

የሀገር ውስጥ የወንጀል ምርመራ ልዩ ወኪል ማይክል ክሮል በመግለጫቸው እንዳሉት ሺሚዬ በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ አሳዛኝ ክስተት ከሆኑት መካከል አንዱ በሆነው የዘር ጭፍጨፋ ያለውን ተሳትፎ ለመሸፈን በመዋሸቱ ነው የተከሰሰው።

ሺሚዬ በ2019 የዘር ጭፍጨፋ በመፈፀም ጥፋተኛ በተባለው ጂን ሊዮናርድ ቴጋንያ የፍርድ ሒደት ላይ ምስክርነቱን ሰጥቷል።

የፍርድ ቤቱ የክስ መዝገብ እንደሚያስረዳው ከሆነ ሺሚዬ ቱትሲዎች ምስማር ባለው እንጨት ጭንቅላታቸውን በመምታትና በስለት በመግደል በግሉ ተሳትፏል።

ሺሚዬ ሩዋንዳን ለቆ የወጣው በ1994 አጋማሽ ላይ ሲሆን በቀጣዩ ዓመት ወደ አሜሪካ ለመግባት የሀገሪቷን የኢሚግሬሽን ባለሥልጣናት ዋሽቷል ተብሎ ወደተከሰሰበት ኬንያ ተጉዟል።

በዚህም በማጭበርበር፣ መረጃዎችን በመደበቅ እና በመሸፋፈን፣ ፍትሕን በማደናቀፍ እና በዳኞች ፊት በሐሰት ምስክርነት በመስጠት ክስ ቀርቦበታል።

የሺሚዬ ተከላካይ ጠበቃ ዴቪድ ጆንሰን በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ለመጠየቅ ቢቢሲ ስልክ ቢደውልላቸውም ምላሽ አልሰጡም።

እንደ አውሮፓውያኑ 1994 በሩዋንዳ በተፈፀመው የዘር ጭፍጨፋ በ100 ቀናት ውስጥ በሁቲ ጽንፈኞች በተፈፀመው ግድያ ወደ 800 ሺህ የሚጠጉ ሰዎች ተገድለዋል።

የዘር ጭፍጨፋው በቁጥር አነስተኛ የሆኑትን የቱትሲ ማኅበረሰቦችን እንዲሁም የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን እና በአጋጣሚ የተገኙ ሰዎችን ዒላማ ያደረገ ነበር።

በተያያዘ ከአስርታት ዓመት በፊት ሩዋንዳ ውስጥ የተፈጸመውን የዘር ማጥፋት በገንዘብ ደግፏል ተብሎ የተከሰሰው የ88 ዓመቱ አዛውንት በጤና ችግር ምክንያት ፍርድ ቤት ለመቆም ብቁ አይደለም ሲል የተባበሩት መንግሥታት ፍርድ ቤት ከወራት በፊት መወሰኑ የሚታወስ ነው።

የተከሳሹ ግለሰብ ፊሊሺዬን ካቡጋ ጠበቃ ከዕድሜ መግፋት ጋር በሚያጋጥም የአዕምሮ ችግር እንዳለበት በመግለጽ ፍርድ ቤት አቤቱታውን አቅርቦ ነበር።

ግለሰቡ የዘር ማጥፋቱ ከተፈጸመ በኋላ ለ26 ዓመታት ተሰውሮ በምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ ሲንቀሳቀስ ቆይቶ ከሦስት ዓመት በፊት ነበር ፓሪስ ውስጥ የተያዘው።

ካቡጋ 800 ሺህ የሚሆኑ ቱትሲዎችን እና ለዘብተኛ ሁቱዎችን ጨፍጭፈዋል የሚባሉትን የሁቱ ጎሳ ሚሊሻዎችን በገንዘብ ደግፏል ተብሎ ቢከሰስም፣ እሱ ግን ክሱን አስተብብሏል።

በሩዋንዳ በተፈጸመው የዘር ማጥፋት ወንጀል ውስጥ ተሳታፊ የነበሩ ተጠያቂዎችን ለፍርድ ለማቅረብ ለአስርተ ዓመታት በተደረገው ጥረት ውስጥ ፍርድ ቤቱ እንዲህ ያለውን ውሳኔ ሲሰጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው።

ችሎቱ የፊሊሺዬን ካቡጋ የጤና ሁኔታ እንዲመረመር ዕድል ለመስጠት ባለፈው መጋቢት ወር ላይ ሂደቱ እንዲቆም ማዘዙ ይታወሳል።

የፍርድ ቤቱ ሰነዶች እንደሚያሳዩት የተከሳሹ 88 ዓመት እንደሆነ የተገለጸ ሲሆን፣ ነገር ግን በትክክለኛው ዕድሜው ላይ አንዳንድ አለመግባባቶች አሉ።

ፊሊሺዬን ካቡጋ በአውሮፓውያኑ በ1970ዎቹ በሻይ እርሻ ልማት ላይ ተሰማርቶ ከፍተኛ ሃብትን ያገኘ ሲሆን፣ በዘር ማጥፋቱ ወቅት ለሁቱ ገዳይ ቡድኖች አባላት ገጀራ ለመግዛት የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል ተብሎ ተከሷል።

የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ይነዛ የነበረው አርቲኤልኤም (RTLM) ራዲዮ ጣቢያ ባለቤትም ነበር።

ፊሊሴ ካቡጋ በዘር ማጥፋት ወንጀል ከሚፈለጉት ሰዎች ቁጥር አንዱ ብቻም ሳይሆን አየሁት ለሚል 5 ሚሊዮን የሚያሸልም ውድ ወንጀለኛ ነበር።

በተጨማሪም ይህ ሃብታም ነጋዴ በነበረው የሬዲዮ ጣቢያ አማካይነት ሁቱዎች ቱትሲዎችን እንዲገድሉ የሚያነሳሱ ጥቃት አባባሽ የጥላቻ ንግግሮችን በማሰራጨት የዘር ማጥፋቱን አበረታቷል ተብሎ ተከሷል።

# ስፖርት





## የኢትዮጵያ ቡና የቤተሰብ ሩጫ ለሰባተኛ ጊዜ ይካሄዳል

ዓለማየሁ ግዛው

ዘነኛው የእግር ኳስ ስፖርት ክለብ ኢትዮጵያ ቡና በየዓመቱ የሚያዘጋጀው የቤተሰብ የጎዳና ላይ የሩጫ ውድድር ዘንድሮ ለ7ኛ ጊዜ ይካሄዳል። ሩጫው በአዲስ አበባ መስቀል አደባባይ የሚካሄድ ሲሆን የመወዳደርያ ቲሸርት ህትመት መጀመሩም ተጠቁሟል።

የኢትዮጵያ ቡና ስፖርት ክለብ ህዝባዊ ክለብ እንደመሆኑ በተለያዩ መንገዶች በሚያገኛቸው የገቢ ምንጮች የክለቡን ፋይናንስ ይደጉማል። ከእነዚህም መካከል የክለቡን ደጋፊዎች በአንድነት የሚያሰባስበው የቤተሰብ ሩጫ የሚገኝበት ሲሆን ውድድሩ ዘንድሮ ለ7ኛ ጊዜ ይካሄዳል። ውድድሩን ለማካሄድ የሚያስፈልገው ቅድመ ዝግጅትም መጠናቀቁን የሩጫው አዘጋጅ ኮሚቴ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ አስታውቋል።

የዘንድሮው የሩጫ ውድድር ግንቦት 11/2016 ዓም «ቡንዬ የኔ» በሚል መሪ ሃሳብ ለማካሄድ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች እየተደረጉ ሲሆን፣ እስከ 35 ሺ ሰው ለማሳተፍ እንደታቀደም ተጠቅሷል። አስገዳጅ የሆኑ ሁኔታዎች ካላጋጠሙ በስተቀር ውድድሩ በተያዘለት ጊዜም ይካሄዳል። በዚህም መሰረት በተጠቀሰው ዕለት ጠዋት ሩጫው መነሻና መድረሻውን መስቀል አደባባይ በማድረግ ይካሄዳል። ለዚህም ፍቃድ ለማግኘት ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽሕፈት ቤትና ለሚመለከታቸው አካላት በደብዳቤ ማሳወቁን ኮሚቴው ጠቁሟል።

7ኛውን የቤተሰብ ሩጫ ለማካሄድ በክለብ ስራ አመራር ቦርድ አማካኝነት አባላት፣ ከደጋፊ ማህበርና ከጽህፈት ቤት የተውጣጣ ኮሚቴ ተዋቅሮ ለሶስት ወራት የቅድመ ዝግጅት ስራን ሲያከናውን መቆየቱ ተገልጿል። በ2017 ዓ.ም የክለቡን ጠንካራነትና ተፎካካሪነት ለማስቀጠል፤ የፋይናንስ አቅም ማሳደግ ስለሚገባ የመሮጫ ቲሸርቱን የመሸጫ ዋጋን፣ በስራ አመራር ቦርዱና በኮሚቴው 800 መቶ ብር እንዲሆን እንደተወሰነ ለማወቅ ተችሏል። ከዚህ ቀደም የነበሩ እጥረቶችና መሰል ችግሮች እንዳይገጥሙም ህትመቱን በፍጥነት ለማስጀመር መታቀዱም ተጠቅሷል።




በውድድሩ እስከ 35 ሺ ሰው ለማሳተፍ እንደታቀደ ተጠቁሟል፣

የመሮጫ ቲሸርቱን ለማቅረብ በቡና ባንክ ቅርንጫፎች፣ በክለቡ ስም በተደራጁ እድሮችና በደጋፊ ማህበሩ በተመረጡ እና በተለያዩ አካባቢ በሚገኙ ደጋፊዎች አማካኝነት ይሆናል። የመሮጫ ቲሸርት ሽያጩም እንደ ከዚህ ቀደሙ እስከ ውድድሩ ቀን እንደማይሆንና ቀኑ የተገደበ መሆኑም ታውቋል። በዚህም የቲሸርት ህትመቱ ከወዲሁ የሚጠናቀቅ በመሆኑ በሩጫው መዳረሻ ጊዜና በዕለቱ ሽያጭ አይኖርም። የትኬት ሽያጩ ከመጋቢት 13 እስከ ሚያዝያ 13/2016 ዓም ድረስ ይሆናል።

የቤተሰብ ሩጫው በ2007 ዓ.ም መካሄድ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ሳይቋረጥ ለ 5 ጊዜ በጎዳና ላይ እና አንድ ጊዜ ደግሞ በኮቪድ 19 ወረርሽኝ መከሰት ምክንያት ደጋፊዎች በያሉበት በመሆን በማህበራዊ ድረ ገጽ ማካሄድ ችሏል። ከስድስቱ ውድድሮች የተወሰዱትን መልካም ተሞክሮዎች በማስቀጠል፣ በሰባተኛው ውድድር የተሻሻሉ ነገሮችን በማካተት ሙሉ ቅድመ ዝግጅት ተደርጓል። በተጨማሪም ከሩጫው በኋላ የደጋፊዎቹን አብሮነት ለማስቀጠል የሙዚቃ ድግስን ለማድረግ ታቅዷል።

ሩጫው ዓላማ አድርጎ የተነሳው ክለቡ የካምፕ መስሪያ ቦታን በማግኘቱና እሱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ማሰባሰብ ነው። ለዚህም በተለያየ መንገድ ገቢን ለመሰብሰብ ታቅዶ ነበረ ሲሆን፣ ከእነዚህም ወስጥ የገቢ ማሰባሰቢያ የእራት ፕሮግራም፣ የሙዚቃ ኮንሰርትና የሩጫ ውድድር በዋናነት ለገቢ ማሰባሰቢያ ታስበው የነበሩ የክለቡ የገቢ ማግኛ መንገዶች ውስጥ ናቸው። በሩጫውና በተጠቀሱት የገቢ ማግኛ መንገዶች የታቀደው የተጫዋቾች ካምፕ እውን መሆኑንም የክለቡ ስራ ስኪያጅ አቶ ገዛኸኝ ወልዴ ገልጸዋል።

የዘንድሮውም ውድድር በዋናነት ሁለት ዓላማዎችን አንግቦ የሚካሄድ ሲሆን፣ እነዚህም የክለቡን የገቢ አቅም ማጠናከርና በክለቡ በደጋፊዎች መካከል ቤተሰባዊ ትስስርን ማጠናከር መሆኑም ተገልጿል። አቶ ገዛኸኝ ወልዴ ክለቡ ህዝባዊ መሰረት ያለው ትልቅ ክለብ መሆኑን ተናግረው፣ የገቢ ምንጩን በተለያየ መንገድ ከህዝቡ በሚያገኘው ገንዘብ የሚደጉም መሆኑን ገልፀዋል። ክለቡ በዋናነት ገቢ የሚያገኘው ከቡና ሴክተር፣ ከስፖንሰር እና ከደጋፊዎች ሲሆን፤ በተጨማሪም ክለቡ ለሽያጭ ከሚያቀርባቸው የተለያዩ ቁሳቁሶች፣ ከስታዲየም መግቢያ ትኬቶችና ከሩጫው በሚያገኘው ገቢ የዓመቱን በጀት እንደሚሸፍን አስረድተዋል። በዚህም ክለቡ በዋናነት የፋይናንስ ገቢውን ከህዝቡ በተለያየ መንገድ በመሰብሰብ ጠንካራ ክለብ ለመገንባት ጥረት እንደሚቀጥል ጠቁመዋል።


## የጨረታ ቁጥር DCE/EM/31/2024 እና DCE/EM/32/2024

የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ለጃንሜዳ ስታፍ ኮሌጅ እና ለድሬዳዋ አፓርትመንት ፕሮጀክቶች አገልግሎት የሚውሉ lighit fitting እና Transformer ግዥ ለመፈፀም ተጫራቾችን በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

| No | የዕቃው ዓይነት | ፕሮጀክት | የጨረታ ቁጥር | የጨረታው መዝጊያ ቀን እና ሰዓት | የጨረታው መክፈቻ ቀን እና ሰዓት | የጨረታ ማስከበሪያ በብር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | lighit fitting | ለጃንሜዳ ስታፍ ኮሌጅ | DCE/ EM/31/2024 | ሚያዚያ 4/2016 ከቀኑ 8፡00 | ሚያዚያ 4/2016 ከቀኑ 8፡15 | 50,000 በብር |
| 2 | Transformer | ለድሬዳዋ አፓርትመንት | DCE/ EM/32/2024 | ሚያዚያ 9/2016 ከጠዋቱ 4፡00 | ሚያዚያ 9/2016 ከጠዋቱ 4፡15 | 200,000 በብር |

ስለሆነም፡-

1. ተጫራቾች በዘርፉ የተሰማሩ፤ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸው፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉ እና ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገቡበትን ማስረጃ እና በጨረታ ለመወዳደር የሚያስችላቸው ከግብር ሰብሳቢው ባለስልጣን የተሰጠ የታደሰ ታክስ ክሊራንስ ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡

2 ተጫራቾች ከላይ በሰንጠረዡ በተገለፀው መሰረት ለእያንዳንዱ ጨረታ የብር መጠን የጨረታ ማስከበሪያ ቦንድ (Bid Bond) 120 ቀን ፀንቶ የሚቆይ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ የጨረታ ማስከበሪያው እንደ ተጫራቹ ምርጫ በቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ በባንክ ዋስትና (Unconditional Bank Guarantee) ወይም በባንክ የተሰጠ የተረጋገጠ ቼክ (CPO) መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ የመድን ድርጅቶች ዋስትና ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

3. አንድ ተጫራች መወዳደር የሚችለው በአንድ ዓይነት ምርት (ብራንድ) ብቻ ነው፡፡ በአማራጭ የቀረበ ዋጋ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

4. ተጫራቾች ለእያንዳንዱ ጨረታ የጨረታ ሠነዱን የማይመለስ ብር 200.00 /ሁለት መቶ ብር/ ለእያንዳንዱ ጨረታ በመክፈል ዘወትር በሥራ ሰዓት ወሎ ሰፈር አካባቢ በሚገኘው የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ዋናው መ/ቤት ግዥ ቡድን ቢሮ መግዛት ይችላሉ፡፡

5. ተጫራቾች የሚያቀርቡት ዋጋ በጨረታ ሰነድ በተያያዘው ዝርዝር እና ብዛት መሰረት መሆን ይኖርበታል፡፡

6. ኢንተርፕራይዙ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡

**አድራሻ፡- የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ**
**የቀጥታ ስልክ ቁጥር፡- 0114-40-34-34**
**ማዞሪያ 0114-42-22-70/71/72**
**ፖ.ሳ.ቁ 3414 ፋክስ ቁ.0114-40-04-71/0114-42-07-46**
**ወሎ ሰፈር የቀድሞው ኖሬላ ግቢ**
**ድህረ ገፅ – www.dce.et.com**
**ኢሜል፡-INFO@dce-et.com**

## የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ



## ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ

የሚ/አ/ከ/አስ/ር ፋይ/ኢ/ል/ጽ/ቤት ለሚ/አ/ከ/ዋና ማዘጋጃ ቤት የደሃ ደሃ ቤት ግንባታ ሥራ ማህበራትን በጨረታ አወዳድሮ ግዥ መፈፀም ይፈልጋል፡፡

በዚሁ መሰረት በጨረታው መወዳደር የምትፈልጉ ተጫራቾች የሚከተሉትን መስፈርቶች በማሟላት መወዳደር ይችላል።

1. ተጫራቾች በተሰማሩበት የሥራ መስክ የዘመኑን ግብር የከፈሉና የታደሰ ንግድ ፈቃድ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

2 የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ መሆን አለባቸው፡፡

3. በተሰማሩበት የሥራ ዘርፍ የአቅራቢነት ምዝገባ ሰርተፍኬት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

4. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ተመዝጋቢ መሆን አለባቸው።

5. ግብር ስለመክፈላቸው ከገቢዎች መ/ቤት ክሊራንስ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

6. የጨረታ ሰነድ ከግዥ ኬዝ ቲም የሥራ ሂደት ቢሮ በመቅረብ ሰነዱን 500/ አምስት መቶ ብር/ ከፍለው በመውሰድ መወዳደር ይችላሉ፡፡

7. የጨረታ ሰነዱ ሞልተው ሲመልሱ ቴክኒካሉን 1 ኦርጅናልና 2 ኮፒ ፋይናንሻሉን 1 ኦርጅናልና 2 ኮፒ በአንድ ፖስታ በማድረግ ለዚሁ በተዘጋጀ የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡

8. የጨረታ ማስከበሪያ 50,000 /ሃምሳ ሺ ብር/ በጥሬ ገንዘብ/በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ለሚ/አ/ከ/አስ/ር ፋይ/ኢ/ል/ጽ/ቤት ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

9 ጨረታው ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ21 ተከታታይ ቀናት አየር ላይ የሚቆይ ሆኖ 22ኛው ቀን ከቀኑ በ3፡30 ታሽጎ በዚያው ቀን በ4፡00 ሠዓት ላይ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት የሚከፈት ሆኖ የሚታሸግበትም ሆነ የሚከፈትበት ቀን የስራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለዉ የስራ ቀን ይሆናል፡፡

10. ሰነዱን ሞልተው ወደ ጨረታ ሳጥን ለማስገባት ሲመጡ ተመዝግበውና ፈርመው ማስገባት አለባቸው

11.መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

**ለበለጠ መረጃ፡- 047 336-0124**

## ሚዛን አማን ከተማ አስተዳደር
## ፋይናንስ ጽ/ቤት